የመጥፎ ጉጉት መዘዝ
ገጽ 11

ያልጠለቀች ጀንበር ...
ገጽ 16

በኃይል ቁጠባ መታገዝ ያለበት
የኤሌክትሪክ
ልማትና ተደራሽነት ማስፋፋት ጥረት
ገጽ 17

ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
84ኛ ዓመት ቁጥር 018 መስከረም 18 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# የግብጽ የመሣሪያ ድጋፍ ለሶማሊያ ወይስ ለአልሸባብ?

ቃልኪዳን አሳዬ

ዜና ትንታኔ

ባሳለፍነው ሳምንት ግብጽ ለሶማሊያ የተለያዩ የጦር መሣሪያዎችን ለሶማሊያ መላኳ ይታወሳል። ሆኖም ይህ ራሷን ለመከላከል በቂ አቅም ለሌላት ሶማሊያ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝን እየተነገረ ነው። እንዲህ አይነት የመሣሪያ ድጋፍ በቀላሉ በአልሸባብ እጅ ሊገባና ሶማሊያ ሙሉ ለሙሉ በአልሸባብ እጅ ልትወድቅ ብሎም ለቀጣናው ሰላም ስጋት ሊሆን እንደሚችል ምሁራን ይገልጻሉ።

የሰላምና ደህንነት ባለሙያና የኢንተራክሽን ፎር ቼንጅ ኢን አፍሪካ ዳይሬክተር ወርቁ ያዕቆብ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፤ ሶማሊያ ክልሎቿን እንኳን በማዕከላዊ

የግብጽ የመሣሪያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## በሶስት ዓመታት ውስጥ የምርጥ ዘር ሽፋኑን ሃምሳ በመቶ ለማድረስ እየተሠራ ነው

ገጽ 2

# የገበያ ማዕከሉ አቅርቦት ምን ይመስላል?

ማርቆስ በላይ

በመዲናዋ ሸማቹ ጥራት ያለው ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ የሚያስችሉ የገበያ ማዕከላት ተገንብተው ወደ ሥራ ገብተዋል። በተለይም በከተማዋ የሚታየውን የዋጋ ንረት በእጅጉ ለመቀነስ እንደሚያስችልም ይገለጻል።

ለመሆኑ እነዚህ የገበያ ማዕከላት በአሁኑ ወቅት እየሰጡ ያለው አገልግሎት ምን ይመስላል፤ ገበያን ከማረጋጋት አንጻርስ ምን እየሠሩ ነው? ከማዕከላቱ መካከል አንዱ የሆነውን የለሚ ኩራ የግብርና ምርቶች ማከማቻና መሸጫ ማዕከል እንቅስቃሴ ቃኝተናል።

የገበያ ማዕከሉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የዓለም ቅርሱ ደመራ

ቃልኪዳን አሳዬ

የመስቀል በዓል ደመራ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በየዓመቱ የሚከበር ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ሲሆን በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና ባህል ተቋም(ዩኔስኮ) በማይዳሰስ የዓለም ቅርስነት መመዝገቡ ይታወቃል።

የመስቀል ደመራ በዓል ንግሥት እሌኒ ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍቅር ሲል መስዋዕትነትን የከፈለበትና ጠፍቶ የነበረውን መስቀል ለመፈለግ ያከናወነችውን ሥርዓት ለማሰብ የሚከበር መሆኑን የሃይማኖቱ አባቶች ይገልፃሉ።

በዓሉ ከኢትዮጵያ አልፎ የዓለም ቅርስ በመሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካል ሃይማኖታዊ ሥርዓቱንና ትውፊቱን ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ እንደሚገባ የሃይማኖት አባቶች ይጠቁማሉ።

የዓለም ቅርሱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ሊቀልሳናት መምህር የኋላወርቅ ኃይለሥላሴ

ፎቶ - ዳኜ አበራ


መምህር ኃይለማርያም ቦንሳ


መምህር አሮን ሱፋ



# በሶስት ዓመታት ውስጥ የምርጥ ዘር ሽፋንን ሃምሳ በመቶ ለማድረስ እየተሠራ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በሶስት ዓመታት ውስጥ አጠቃላይ የምርጥ ዘር ሽፋንን ሃምሳ በመቶ ለማድረስ እየተሠራ መሆኑን ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።



በግብርና ሚኒስቴር የሰብል ልማት መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ኢሳያስ ለማ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የእርሻ የመሬት ሽፋንን በመጨመር እና በሄክታር የሚገኘውን ምርት በማሳደግ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ይቻላል። የምርጥ ዘር አጠቃቀም ምርትና ምርታማነት ከማሳደግ ጋር ያለው ግንኙት ቀጥተኛ ነው። ሆኖም እንደሀገር ያለው የምርጥ ዘር ሽፋን ግን ከሃያ በመቶ አይበልጥም።

በዘንድሮ ዓመት ባለፉት ዓመታት የነበረው የምርጥ ዘር አጠቃቀም ሂደትን በመገምገም የሶስት ዓመት እቅድ ተዘጋጅቷል ያሉት አቶ ኢሳያስ፤ በዚህም በሶስት ዓመታት ውስጥ አጠቃላይ የምርጥ ዘር ሽፋንን ሃምሳ በመቶ ለማድረስ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ለዚህም የፌዴራልና የክልል ተቋማትን ያካተተ ሀገራዊ ኮሚቴ በሚኒስቴሩ የተቋቋመ መሆኑን ያነሱት አቶ ኢሳያስ፤ ዋና ዋና የምግብ ሰብሎች የምንላቸውን እንደጤፍ፣ ስንዴና በቆሎ ያሉ ምርቶች ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራ ተናግረዋል።

በእቅዱ መሠረት በነዚህ ሰብሎች ላይ ከፍተኛ ምርት መሰብሰብ አለበት በሚል ተነሳሽነት ተግባራዊ ይደረጋል። ሌሎች ሰብሎች ላይም እቅዱ ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጸው በሶስት ዓመት ውስጥ በተለዩ ምርቶች ማለትም በስንዴ፣ በጤፍና በበቆሎ ምርት ላይ የምርጥ ዘር ሽፋንን መቶ ፐርሰንት ለማድረስ ታቅዷል ነው ያሉት።

ከምርምር ተቋማት የሚወጣ መነሻ ዘር መጠን ዝቅተኛ ነው። ይህንን መጠን ማሳደግ የሚቻልባቸው መንገዶች በእቅዱ ተካቷል ያሉት አቶ ኢሳያስ፤ ባለፉት ዓመታትም በክልልና በፌዴራል ተቋማት የምርጥ ዘር አተገባበር ላይ ክፍተት የታየ ሲሆን ይህንንም ችግር እቅዱ እንደሚፈታ ተናግረዋል።

ከዚህ በፊት በየዓመቱ ከሃያ እስከ ሰላሳ ሺህ ሄክታር በምርጥ ዘር በመሸፈን ሁሉንም የጥራት ቁጥጥር አልፎ የሚወጣው ዘር ከአንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ኩንታል ያነሰ እንደነበር አንስተው፤ በዚህ ዓመት ሰፊ መሬትን በምርጥ ዘር መሸፈን እና ለሚቀጥለው ዓመት ደግሞ ብዙ የመነሻ ዘር ማባዛት ላይ ትኩረት እንደሚደረግ ገልጸዋል።

ዘንድሮ ወደ 148 ሺህ ሄክታር መሬት ለመሸፈን ታቅዷል። እስከ አሁን ድረስ ወደ 75 ሺህ ሄክታር በግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን፣ በክልሎችና በዘርፉ በሚገኙ አካላት ተሸፍኗል ያሉት አቶ ኢሳያስ፤ ካለፉት ዓመታት አንፃር የዘንድሮ ዓመት የምርጥ ዘር ሽፋን በምርትና ምርታማነት ላይ ትልቅ ለውጥ እንደሚያመጣ ተናግረዋል።

በዘንድሮ ዓመት የመነሻ ዘር ብዜት ከአንድ ሺህ 200 ሄክታር በላይ የተሸፈነበት ሲሆን ዘንድሮ የሚገኘው የመነሻ ዘር የዘር ብዜትን እንደሚያሳድግ ተናግረው፤ የመነሻ ዘሩ የሚባዛው በምርምር ተቋማትና ጥሩ የምርጥ ዘር ማልሚያ ግብዓት ባላቸው ድርጅቶች መሆኑን ገልጸዋል።

# በበጀት ዓመቱ ከባህር ትራንስፖርት አገልግሎት 104 ነጥብ 14 ቢሊዮን ብር ለማግኘት ታቅዷል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት ከስምንት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ቶን በላይ እቃ በማጓጓዝ 104 ነጥብ 14 ቢሊዮን ብር ለማግኘት መታቀዱን የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት አስታወቀ።



በኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት የኮርፖሬት ኮምኒዩኬሽን መምሪያ ኃላፊ አቶ ደምሰው በንቲ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በበጀት ዓመቱ ከባህር ትራንስፖርት አገልግሎት 104 ነጥብ 14 ቢሊዮን ብር ለማግኘት ታቅዷል።

በተያዘው በጀት ዓመት ስምንት ሚሊዮን 250 ሺህ ቶን የወጪና ገቢ ንግድ በማጓጓዝ 104 ነጥብ 14 ቢሊዮን ብር ለማግኘት ታቅዷል ያሉት አቶ ደምሰው፣ በዚህም 14 ነጥብ 30 ቢሊዮን ብር የተጣራ ትርፍ ለማስመዝገብ ውጥን መያዙን ጠቁመዋል።

በ2016 በጀት ዓመት ከባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት 51 ነጥብ 01 ቢሊዮን ብር ለማግኘት ታቅዶ 57 ነጥብ 14 ቢሊዮን ብር በማግኘት ስምንት ነጥብ 86 ቢሊዮን ብር የተጣራ ትርፍ መገኘቱንም ነው አቶ ደምሰው የገለጹት።

ዘንድሮ የታቀደው የጭነት የማጓጓዝ እቅድ በ2016 በጀት ዓመት የሀገሪቱን ወጪ ገቢ ንግድ ከማጓጓዝ አኳያ ከነበረበት ሰባት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ቶን ላይ አስር በመቶ ጨማሪ ያለው እንደሆነ ተናግረዋል።

አቶ ደምሰው አክለውም፣ አገልግሎቱ ከሚሠራቸው ሥራዎች መካከል የተሳለጠ የሕዝብና የጭነት ትራንስፖርት እንዲሁም የወደብና ተርሚናል አገልግሎት መስጠት ነው ያሉ ሲሆን ከ94 በመቶ በላይ የሀገሪቱ የገቢና ወጪ ንግድ በአገልግሎቱ በኩል እየተሳለጠ ይገኛልም ብለዋል።

ባለፈው በጀት ዓመት በቀይ ባህር አካባቢ ካጋጠሙ የደህንነት ችግሮች ጋር በተያያዘ በአገልግሎቱ ላይ ጫና አሳድሮ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ደምሰው፤ በቅንጅት በመሠራቱ ችግሩን ለመፍታት እንደተቻለ አብራርተዋል።

እንደ አቶ ደምሰው ገለጻ፣ በቀይ ባህር ላይ በተፈጠረው ችግር በተለይ ከቻይናና ከሩቅ ምስራቅ ሀገራት የተለያዩ ሸቀጦች ለማጓጓዝ በኪራይ የሚሠሩ መርከቦች ወደ ጅቡቲ ወደብ አንሄድም በማለታቸው ችግሩን ለመቅረፍ ሳውዲ አረቢያና ኦማን አካባቢ ያሉ ሁለት ወደቦች ድረስ አድርሰው በሀገር ውስጥ መርከቦች እንዲጓጓዝ ተደርጓል። ይህ ርምጃ ባይወሰድ በሀገሪቱ በንግድ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያሳድር ነበር።

አቶ ደምሰው ሀገሪቷ ካላት መርከበቦች በተጨማሪ መርከቦች በመከራየት እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው በ2017 በጀት ዓመትም የስድስት አዳዲስ የመርከቦች ግዢ ለመፈጸም ቅድመ ሥራዎች መጀመራቸውን አስረድተዋል።

በ2016 በጀት ዓመት ከጅቡቲ ወደብ በተጨማሪ የላሙ ወደብም መጠቀም ተችሏል ያሉ ሲሆን ሀገሪቷ ካላት ከፍተኛ የቆዳ ስፋትና የሕዝብ ብዛት በርካታ ወደቦች ለመጠቀም መንግሥት እየሄደበት ካለው ጎን ለጎን የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ።

የኢትዮጵያ መርከቦች ከ346 በላይ በሚሆኑ ዓለም አቀፍ የወደብ መዳረሻዎች አገልግሎት በመስጠት ለሀገር ከሚያስገኙት ጠቀሜታ ባሻገር የሀገሪቱን ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለቡ ለሀገር አምባሳደር በመሆናቸው የተቋሙን አቅም ለማሳደግ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሊተባበሩ እንደሚገባ አመላክተዋል።



አቶ ፍሰሃ ግርማይ

# ክልሉ 800 ኪሎ ግራም ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ ለማቅረብ እቅድ ተይዟል

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል በተያዘው በጀት ዓመት 800 ኪሎ ግራም ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ ለማቅረብ አቅዶ እየሰራ መሆኑን የክልሉ መሬት እና ማዕድን ቢሮ አስታወቀ።

የክልሉ የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ፍስሃ ግርማይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ በተያዘው በጀት ዓመት 800 ኪሎ ግራም ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ ለማቅረብ እየተሠራ ነው። የማዕድን ምርት በሕጋዊ መንገድ እንዲሠራ ሕግ እና አሠራር ተዘርግቷል።

በክልሉ ከፀጥታ ጋር በነበረው ችግር ምክንያት ከማዕድን መገኘት የነበረበት ገቢ ሳይገኝ መቆየቱን በመጥቀስ፤ የነበረው ክፍተት በማስተካከል እና ሥርዓት መዘርጋት ውጤታማ ሥራ ለመሥራት መቻሉን ተናግረዋል። በዚህም በአዲሱ በጀት ዓመት 800 ኪሎ ግራም ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ ለማቅረብ እንዲሁም ስልሳ ኪሎ ግራም የሳፋየር ማዕድን ወደ ገበያ ለማቅረብ ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በክልሉ ከማዕድን 35 ሚሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ የታቀደ ሲሆን ገቢው የሚገኘውም ለኮንስትራክሽን ግብዓት፣ ከኢንዱስትሪ እና ለጌጣጌጥ የሚውሉ ማዕድናት መሆኑን አስረድተዋል። ከፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ወዲህ ከቀድሞ ታጣቂዎች በክብር የተሸኙ አባላት ወደ ዘርፉ በሥርዓት ተሠማርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል።

የማዕድን ዘርፍ ከበፊቱ የተሻለ ገቢ ለማግኘት የነበሩት የአሠራር ድክመቶች በማሻሻል ጥሩ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ የሀገር ኢኮኖሚ ከፍ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

ቢሮው ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማግኘት ጥያቄ ሲያቀርቡ የሚስተናገዱበት ደንብ መቀመጡን ጠቅሰው፤ በደንቡ መሠረት ሥራን ሲያከናውን ከዘርፉ የታሰበውን ገቢ ለማግኘት ያግዛል ብለዋል።


የ2017 በጀት ዓመት ከማዕድን ዘርፍ ከፍተኛ ገቢ ለማግኘት እቅድ መያዙን ጠቅሰው፤ለወጣቱ የሥራ ዕድል በመፍጠር ያለውን አቅም መጠቀም እንደሚገባ አመልክተዋል። በተጨማሪም ሌሎች የማዕድን ቦታዎችን በማጥናት ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ወጣቶች እንዲሳተፉ ይደረጋል ብለዋል።

በክልሉ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ለማምጣት የማዕድን ዘርፉ ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳለው በመግለፅ፤ ለበርካታ ወጣቶች ተስፋ የሚሰጥ እንዲሁም ቤተሰቦቻቸውም መርዳት እንዲችሉ ታስቦ እየተሠራ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

ዜና



ወንጪ ሪዞርት



# ሆቴልና ሪዞርቶች ለኢሬቻ በዓል ቅናሽ እያደረጉ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ሆቴልና ሪዞርቶች ለዘንድሮው የኢሬቻ በዓል ቅናሽ ማድረጋቸውን የኢትዮጵያ ቱሪዝምና ሆቴል ማርኬት ማህበር አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ቱሪዝምና ሆቴል ማርኬት ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ጌታሁን አለሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለኢሬቻ በዓል ታዳሚዎች ሆቴልና ሪዞርቶች ከ30 በመቶ ጀምሮ ቅናሾችን አድርገዋል።

በተያዘው ወር ለኢሬቻ በዓል ሆቴሎች የራሳቸውን ቅድመ ዝግጅት አድርገዋል ያሉት አቶ ጌታሁን፣ ለኢሬቻ በዓል ታዳሚዎች ሆቴልና ሪዞርቶች ከ30 በመቶ ጀምሮ ቅናሾችን አድርገዋል ብለዋል።

በዓሉን ለመታደም ለሚመጡ እንግዶች በወንጪ ሪዞርትና በሸራተን ሆቴል የቅናሽ አገልግሎት እንደሚያገኙ ጠቅሰው፣ ሌሎች ሆቴሎችም በኢሬቻና በመስቀል በዓል ላይ የተለያዩ ጥቅሎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ መዘጋጀታቸውን ገልጸዋል።

በአደባባይ በዓላቱ የዓለም አቀፍና የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች እንደሚሳተፉ በመግለጽ፣ በዓላቱን ተከትሎ ሆቴሎች ገቢአቸውን ለመጨመር የራሳቸውን ጥቅሎች እንደሚያዘጋጁ ጠቁመዋል።

ለኢሬቻ በዓል የተለያዩ የኦሮሞ የባህል ምግቦችን የሚያዘጋጁ ሆቴሎች መኖራቸውንም ጠቅሰው፣ የአደባባይ በዓላት ለሆቴሉ ዘርፍ ገቢን በማሳደግ ከፍተኛ መነቃቃት እንደሚፈጥሩ ተናግረዋል።

የስካይላይት ሆቴል የሽያጭ ክፍል ኃላፊ አቶ አየሁ ገሰሰ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በሚያስተዳድረው የወንጪ ሪዞርት ላይ ለኢሬቻ በዓል ከ35 እስከ 45 በመቶ ቅናሽ ተደርጓል።

ለኢሬቻ በዓል በወንጪ ሪዞርት መኝታ ቀድመው መያዝ እንደሚችሉ ጠቅሰው፣ በሪዞርቱ በሚሰጡ የመኝታ፣ ምግብና መጠጥ አገልግሎቶች ላይ ከመደበኛ ዋጋ ከ35 እስከ 45 በመቶ ቅናሽ መደረጉን ገልጸዋል።

የበዓሉ ታዳሚዎች የቅናሽ አገልግሎቱ ተጠቃሚ ለመሆን ቀድመው መመዝገብ እንደሚጠይቅ በመግለጽ፣ የዋጋ ቅናሹ ከመስከረም 13 ጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ ሲሆን እስከ በዓሉ ዕለት ድረስ እንደሚቆይ ጠቁመዋል።

ለኢሬቻ በዓል በስካይላይት ሆቴል ባህላዊ ሬስቶራንቶች ላይ በዓሉን የሚገልጹ ምግብና መጠጥ አገልግሎቶች እንደሚቀርቡ የገለጹት ኃላፊው፣ በዓሉ ባህላዊ ሬስቶራንቶች ላይ የተለያዩ ዝግጅት የተደረገ ሲሆን አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል ብለዋል።

በደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚከበሩትንም የዘመን መለወጫ በዓላት ላይም የተለያዩ ልዩ መርሃግብሮች መዘጋጀታቸውን ጠቅሰው፣ የመስከረም ወር በርካታ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች፣ የአደባባይ በዓላት የሚካሄዱበት በመሆኑ በሆቴል ገበያው ላይ መነቃቃት መፍጠሩን ገልጸዋል።

# "በዓለም አቀፍ ተቋማት ፍትሃዊ ውክልና እንዲሰፍን በሚደረጉ ጥረቶች የብሪክስ ማዕቀፍ ጉልህ ሚና ይጠበቅበታል"

\- አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**





አዲስ አበባ፡- በዓለምአቀፍ ተቋማት ፍትሃዊ ውክልና እንዲሰፍን በሚደረጉ ጥረቶች የብሪክስ ማዕቀፍ ጉልህ ሚና ይጠበቅበታል ሲሉ አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ ገለጹ። በኒውዮርክ እየተካሄደ ከሚገኘው 79ኛው የተመድ ጠቅላላ ጉባዔ ጎን ለጎን የብሪክስ አባል ሀገራት ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ ተካሂዷል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ በስብሰባው ላይ ባደረጉት ንግግር በዓለም አቀፍ ተቋማት አስተዳደር እና በዓለም አቀፍ ጉዳዮች ዙሪያ ፍትሃዊ ውክልና እና ተሰሚነት እንዲሰፍን በሚደረገው የማሻሻያ ጥረት የብሪክስ ማዕቀፍ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል የሚል ተስፋ እየጨመረ መምጣቱን ገልጸዋል።

አምባሳደር ታዬ የባለብዙ ወገን ዓለም አቀፍ ተቋማቱ አሳታፊ እና ጠንካራ እንዲሆኑ የተጀመሩ የማሻሻያ ጥረቶች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው አንስተዋል።

ሚኒስትሩ የተመድ የጸጥታው ምክር ቤት ማሻሻያን በተመለከተ ባደረጉት ንግግር ማሻሻያው ቅድሚያ ለአፍሪካ ውክልና መስጠት እንደሚገባው እና ታማኝ እና ፍትሃዊ ሆኖ መቀጠል አለበት ብለዋል።

አምባሳደር ታዬ በጸጥታው ምክር ቤት ማሻሻያ ላይ ኢትዮጵያ የምታራምደው አቋም የአፍሪካ አቋም ነው፤ "ለአፍሪካ ሕጋዊ እና ታሪካዊ ጥያቄ እና ኢ-ፍትሃዊ እና ግማሽ ምላሽ ሊሰጠው አይገባም" ብለዋል።

ሚኒስትሩ ውክልናው መልከዓ ምድርን፣ የብሪክስን የጋራ ዕሴቶች እና በብሪክስ ማዕቀፍ አባል ሀገራት መካከል ያለውን ግንኙነት እና የተመድን ቻርተር ባማከለ መልኩ መከናወን እንዳለበትም ጠቁመዋል።

እነዚህ መርሆዎች ብሪክስ በዓለም አቀፍ ተቋማት ማሻሻያ እና ፍትሃዊ ውክልና እንዲኖር የሚጫወተውን ሚና የበለጠ ያጠናክሩለታል ማለታቸውን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመለክታል።





ወይዘሮ አያልነሽ አሰፋ



# አካል ጉዳተኞችን ለመደገፍ የተዘረጋ እጅ

**አማን ረሺድ**

**ዜና ሀተታ**

አያልነሽ አሰፋ ትባላለች። የምትኖረው በአዲስ አበባ ከተማ ልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት ሲሆን የሶስት ልጆች እናት ናት። በልጅነቷ ወድቃ በእግሮቿ ላይ ጉዳት በመድረሱ እንደልቧ መንቀሳቀስ የማትችል ስትሆን፤ በዚህም ልጆቿን ለማሳደግ እጅ እንዳጠራት ትገልጻለች። ወረዳው አካል ጉዳተኛ ዜጎች እገዛ እንዲያገኙ ለማድረግ ሰዎችን ሲመዘግብ በዚያ ምክንያት መመዝገቧን ገልጻለች።

በአጋጣሚ አካል ጉዳተኛ ወገኖችን የሚደግፍ ካይማ ፋውንዴሽን በኢትዮጵያ ከአውስትራሊያ ኤምባሲ የሚደገፍ የዳፕ ፕሮጀክት እንዳለ እንደተነገራት አውግታናለች።

በዚህም ፋውንዴሽኑ ከአምስት ወር በፊት ዘመናዊ የዶሮ መኖርያ ቤት፣ 25 ዶሮዎችና ለ2 ወር የሚቆይ የዶሮ መኖ እንደተሰጣት ትናገራለች። በተደረገላት ድጋፍ ዶሮዎችን በማሳደግ ገቢ እያገኘች ነው። አሁን ላይ ችግሯ በከፊል እንደተቀረፈላት ጠቁማለች።

ለአካል ጉዳተኛ ዜጎች ድጋፍ ማድረግ ከተቻለ መሥራትና እራሳቸውን መቀየር ይችላሉ የምትለው ወይዘሮ አያልነሽ፤ ለአካል ጉዳተኞች የሚደረጉ መሰል ድጋፎች ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ሊቀጥል ይገባል ብላለች። በዚህም ደስተኛ መሆኗን ገልጻ፤ ለተደረገላት ድጋፍም አመስግናለች።

ሌላኛው የድጋፉ ተጠቃሚ የሆኑት አቶ ቸርነት ደምሴ ይባላሉ። የሚኖሩት በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 በሚገኘው የጦር ጉዳተኞች ካምፕ ሲሆን በካምፑ ለበርካታ ዓመታት እንደቆዩ ይናገራሉ። በጦርነት ምክንያት እጃቸው ላይ ጉዳት በመድረሱ እንደፈለጉት መሥራት እንዳይችሉ እንዳደረጋቸው ገልጸዋል።

ካይማ ፋውዴሽን አካል ጉዳተኛ የሆኑ በዶሮ እርባታ መሳተፍ ፍላጎት ያላቸውን እንደሚደግፍ ሲነገር ሰምተው በወረዳው አማካኝነት በካምፑ የሚኖሩ 10 ግለሰቦች በማህበር ተደራጅተው ሥራውን መጀመራቸውን ያስረዳሉ። በማህበሩ ውስጥ ያሉት የተለያየ የአካል ጉዳት ተጠቂዎች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ፋውንዴሽኑ 100 ዶሮዎችን፣ የዶሮ መኖ እንዲሁም የዶሮ እርባታ ሥልጠና ድጋፍ ማግኘታቸውን ገልጸው፤ በዚህም የሥራ ተነሳሽነት እንዲጨምርና ከመቀመጥ በተገኘው እድል ተጠቃሚ መሆናቸውን ጠቁመዋል። ህብረተሰቡ ለአካል ጉዳተኞች ያለው የአመለካከት ሁኔታ እንዲቀየር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጥ ይገባል ብለዋል።

የካይማ ፋውዴሽን ካንትሪ ዳይሬክተር ታዲዮስ ሀብቴ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ካይማ ፋውንዴሽን በኢትዮጵያ የአውስትራሊያ ኤምባሲ ስር ከሚገኝ የዳፕ ፕሮጀክት ጋር በትብብር እንደሚሠራ ገልጸው፤ በአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ብር ወጪ በአዲስ አበባ ለሚገኙ ሴቶችንና አካል ጉዳተኞችን ኑሮ እንዲሻሻል የቤተሰብ የዶሮ እርባታ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል ብለዋል። የፕሮጀክቱ ዓላማ ለችግር ተጋላጭ ማህበረሰብ አባላትን የኑሮ እና የአመጋገብ ፍላጎት ለማሻሻል መሆኑን አስረድተዋል።

በተጨማሪም መንግሥት ያስጀመረውን የሌማት ትሩፋት ፕሮግራም ውጤታማ እንዲሆን የተለያዩ የዶሮ እርባታ ቴክኖሎጂ ፓኬጆችን በመጠቀም የንግድ የዶሮ ዝርያዎችን፣ ምግብን እና የጤና አስተዳደርን ማሳደግን ጨምሮ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

በፕሮጀክቱ ለ17 አባወራዎችና 10 ግለሰቦች በስሩ ላቀፈ አንድ ማህበር 90 ቀናት የሆናቸው 25 ዶሮዎች፣ ዘመናዊ የዶሮ ቤት እና ከ60 ቀናት የሚሆን መኖ እገዛ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል።

ከወረዳው የተመረጡ በርካታ ሰዎች በማህበረሰብ የዶሮ እርባታ ክትባት ሠልጥነው ከካይማ ፋውንዴሽን የምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸዋል ብለዋል። በተጨማሪም ፋውንዴሽኑ የሠለጠነ የማህበረሰብ አቀፍ ክትባቶች በልደታ ከተማ ለሚገኙ ከ700 በላይ ዶሮዎችን ክትባት መሰጠቱን አመላክተዋል።

እንደ ዶክተር ታዲዮስ ገለጻ፤ ድጋፍ የተደረጉት ዶሮዎች በሁሉም ቤተሰብ ውስጥ እንቁላል መጣል የጀመሩ ሲሆን የተሻለ ለውጥ አሳይቷል።

በቀጣይ ፕሮግራሙን አዲስ አበባን ጨምሮ ወደ ሌሎች አካባቢዎች ለማስፋፋት መታቀዱን ገልጸው ሥራውን በሚፈለገው መጠን ለማስኬድ የገንዘብ ድጋፍ ያስፈልጋል ብለዋል።

# የግብጽ የመሣሪያ ድጋፍ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

*መንግሥት የማስተዳደር አቅም አጥታለች፤ እንዲሁም ከግብጽ መንግሥት ጋር ያደረጋቸውን ወታደራዊ ስምምነት የፓርላማ አባላትም ተቃውመውታል። በዚህ ሁኔታ ላይ እያለች የግብጽ መንግሥት ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን መስጠቱ መሣርያዎቹ በቀላሉ በአልሸባ እጅ እዲወድቁ በማድረግ ለቀጣናው ሰላም ስጋት ሊሆን ይችላል።*

በቀጣናው ግብጽ፣ ሶማሊያ፣ ኢትዮጵያና ኤርትሪያ የየራሳቸው ውስጣዊ ችግሮች ያሏቸው በመሆኑ ሰጥቶ የመቀበል መርህን በመከተል በጋራ መልማት ተመራጭ ነው። እነኚህ ሀገራት ቆም ብለው በችግሮቻቸው ዙሪያ በማሰብ ዲፕሎማሲያዊ አማራጮችን በመጠቀም ከጠብ አጫሪ ንግግሮችና ተግባራት መቆጠብ እንዳለባቸውም ዶክተር ወርቁ ይገልጻሉ።

ግብጽ በአሁኑ ወቅት ጠብ አጫሪ ተግባር በማከናወን ኢትዮጵያን የመክበብ አይነት ሁኔታ ውስጥ እየገባች ነው። ከህዳሴው ግድብ ጋር ተያይዞ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለረጅም ጊዜ ስትከስ መቆየቷን የሚያነሱት ባለሙያው፤ ይህንንም በዲፕሎማሲ ማሸነፍ ሲያቅታት ሰሞኑን በኢትዮጵያ ዙሪያ የምታደርገው እንቅስቃሴና የምታወጣው መግለጫ በሃይልና በውክልና ጦርነት ነገሮችን ለማሳካት ፍላጎት እንዳላቸው ማሳያ ነው ይላሉ።

እንደ ዶክተር ወርቁ ገለጻ፤ ግብጽ ኢትዮጵያን ለጦርነት ለማነሳሳት አደገኛ አካሄድ እየሄደች በመሆኑ ኢትዮጵያ በተቀናጀ ዲፕሎማሲያዊ አካሄድ ግብጽ እያደረገችው ካለው ጠብ አጫሪ ተግባር እንድትቆጠብ ማድረግ ያስፈልጋታል። እንዲሁም ይህን ተግባር ለዓለም አቀፉ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብና ሚዲያዎች ማስረዳት፣ የግብጽን እንቅስቃሴ ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ መከታተልን ይሻል።

ኢትዮጵያ በታሪኳ የትኛውም ባዕድ ሀገር ሊያሸንፋትና ሊያንበረክካት እንደማይችል ይታወቃል። ግብጽ በአሁኑ ወቅት ለሶማሊያ አይዞሽ እኔ አለሁሽ ጨዋታ እየተጫወተች ነው። ግብጽ ይህን እያደረገች ያለው ኢትዮጵያ ከህዳሴው ግድብ በሙሉ አቅሟ ሃይል ማመጨት ስትጀምር ኢኮኖሚያዊ አቅሟን ከማሳደግ ባለፈ ለሌሎች ሀገራትም ሃይል በማቅረብ የቀጣናው ተጽዕኖ ፈጣሪነቷ እንዳያድግ በሚል ስጋት መሆኑን ዶክተር ወርቁ ያመላክታሉ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህርና በአፍሪካና የኤሲያ ጥናት ሶስተኛ ዲግሪያቸውን በመከታተል ላይ ያሉት ዳዊት መዝገበ ጸጋዬ በበኩላቸው እንደሚሉት፤ የሶማሊያ ፖለቲካ ጎሳን መሠረት ያደረገና የተከፋፈለ ነው። በዚህም ግብጽ የሰጠችው የጦር መሣሪያ ለአልሸባብ አይደርስም ብሎ ማሰብ ከሞኝነት ያለፈ ነው። አልሸባብ መኖር የቻለው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሶማሊያ መንግሥት ፍላጎት ነው።

ግብጽ በአፍሪካ ቀንድ ፖለቲካ ውስጥ የምትፈልገው በየትኛውም አጋጣሚ የኢትዮጵያን ፖለቲካና የውስጥ ሰላም ማደፍረስ ነው። ከዓባይ ወንዝ ጋር ተያይዞ ግብጽ ስለኢትዮጵያ ያላት የጠላትነት አመለካከት ዛሬ የጀመረ ሳይሆን አባይ ከኢትዮጵያ እንደሚመነጭ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ ነው የሚሉት መምህሩ፤ ግብጽ ለሶማሊያ የጦር መሣሪያ መስጠቷ የሚያስከትለው ተጽዕኖ በአፍሪካ ቀንድ ብቻ ይወሰናል ብሎ ማሰብ ገርነት ነው ይላሉ።

እንደ መምህር ዳዊት ገለጻ፤ ለዩክሬን የተሰጠው የጦር መሣሪያ ኦዲት የማይደረግ በመሆኑ በጥቁር ገበያዎች እየወጣ በመሸጡ ላልተገባ ተግባር ውሏል፤ የዚህም እጣ ፈንታ ተመሳሳይ ሊሆን የሚችል በመሆኑ ይህም ለመላው ዓለም ስጋት የሚደቅን ነው።

ግብጽ ከሰሞኑ በሶማሊያ ወታደሮቼን አሰፍራለሁ ማለቷ የሚያስደንቅ ነው። ሰላምን አጥብቃ የምትሻ ከሆነ የበርካታ ዜጎች እልቂት ባለበት በጋዛ፣ በሱዳን፣ በሶሪያና በሌሎች ሀገራት ልታሰፍር እንደምችል የሚጠቁሙት መምህር ዳዊት፤ ከልቧ ቢሆን የሶማሊያን ውስጣዊ ችግር በመፍታት ኢኮኖሚያዊ መረጋጋትን መፍጠር ትችል ነበር፤ እንዲሁም ቀደም ሲል ሶማሊያን ከአልሸባብ ለመታደግ በተደረጉ ጥረቶች ተሳትፎ ማድረግ ትችል እንደነበር ያነሳሉ።

ግብጽ ከቅኝ ግዛት ነጻ ከወጣችበት ጊዜ ጀምሮ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዋንም ጨምሮ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የኢትዮጵያን ሰላም መንሳት ነው፤ በዚህ የግብጽ ፍላጎት የአፍሪካ ቀንድ ሰላምን ማደፍረስ በመሆኑ የግብጽን የፖለቲካ አካሄድ በማጤን ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰላም ግንባታና ፖለቲካ ጉዳዮች ረዳት ዋና ፀሐፊ ሮዝማሪ ዲካርሎ ጋር በተወያዩበት ወቅት" በሶማሊያ ባልተረጋጋ የደህንነት ሁኔታ ውስጥ በውጭ ሃይላት የሚደረግ የጦር መሣሪያ አቅርቦት በመጨረሻ ሀገሪቷ አሸባሪዎች እጅ ላይ እንድትወድቅ በር ሊከፍት ይችላል " ሲሉ ስጋታቸውን መግለጻቸው የሚታወስ ነው።

# የገበያ ማዕከሉ አቅርቦት ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ



የለሚ ኩራ የግብርና ምርት የገበያ ማዕከል በርካታ ቁጥር ያላቸው አምራቾች፣ ነጋዴዎችና አቅራቢዎች በተዘጋጁላቸው መሸጫ ቦታዎች ላይ የሽንኩርት፣ ቲማንቲም፣ ጤፍ፣ ዱቄትና የመሳሰሉት ምርቶች እያቀረቡ እንደሚገኝ ተዘዋውረን ተመልክተናል።

ታዲያ የግብርና ምርቶች ማከማቻና መሸጫ ማዕከሉ አሁን ምን እየሠሩ ነው፤ ስንል አቅራቢዎችና ሸማቾችን አነጋግረናል።

የቶኩማ አትክልትና ፍራፍሬ አቅራቢው አቶ ዋቅቶላ ሴንጦ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በለሚ ኩራ የግብርና ምርቶች ገበያ ማዕከል ላይ ከውጪ ገበያ 15 በመቶ ቅናሽ በማድረግ እያቀረቡ እንደሚገኝ ይናገራል።

በመቂ የእርሻ ማሳ የቲማንቲም፣ ፓፓያ፣ ሽንኩርት፣ ፎሶሊያና ቃሪያን በማምረት ወደ ገበያ እንደሚያቀርቡ የገለጸው አቶ ዋቅቶላ፣ በገበያ ማዕከሉ ከሚመጡት ሸማቾች በተጨማሪ በሱቅ ለሚሸጡ ነጋዴዎች በተመጣጣኝ ዋጋ እንደሚያቀርቡ ይገልጻል።

በለሚ ኩራ የግብርና ምርት መሸጫ ገበያ ማዕከል የተለያዩ የግብርና ምርቶችን ከውጪ ገበያው 15 በመቶ ቅናሽ በማድረግ እያቀረቡ እንደሚገኝ ጠቅሰው፣ ድንች በኪሎ 25 ብር፣ ቲማንቲም 40 ብር፣ ሽንኩርት 95 ብር፣ አቡካዶ 25 ብር ድንች ስኳር 25 ብር ጥቅል ጎመን 20 ብር ፣ብርቱካን 100 ብር፣ አናናስ 40 ብር እያቀረቡ እንደሚገኝ ያስረዳል።

በገበያ ማዕከሉ ይስተዋሉ የነበሩ የመብራት፣ የውሃና የግብርዓት ችግሮች እየተቀረፉ እንደሚገኝም ይገልጻል።

በገበያ ማዕከሉ እየቀረቡ ያሉ ምርቶች በዋጋ ተመጣጣኝ በመሆናቸው ተጠቃሚ ሆነናል የሚሉት ደግሞ ከአያት አካባቢ የቤት አስቤዛ ለመሸመት የመጡት ወይዘሮ ሰብለ ተስፋዬ ናቸው።

በተለይም ፍራፍሬዎች ፍሬሽና ጥራታቸው የጠበቁ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ለጤናም ተስማሚ መሆናቸውን አንስተዋል።

የገበያው ማዕከሉ በአቅራቢያቸው መገንባቱና ምርት ማቅረቡ ጊዜያቸውንና ወጪያቸውን እንደቆጠበላቸው በመግለጽ፣ ጥራት ያለው ሽንኩርት በኪሎ 100 ብር፣ ድንች 25 ብር፣ ቲማንቲም 50 ብር መግዛታቸውን ይገልጻሉ።

የግብርና ውጤት እህል ምርቶችን ለሚያቀርበው አቶ ማረኝ ጀማነህ እንደሚናገረው፣ በገበያ ማዕከሉ በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ በቆሎ፣ ነጭ፣ ቀይና ሰርገኛ ጤፍን ጨምሮ የተለያዩ ሰብሎችን እያቀረቡ እንደሚገኝ ይናገራል።

ነጭ ጤፍ በኩንታል 13 ሺህ 500 ብር፣ ቀይ ጤፍ 11 ሺህ 400 ብር፣ በቆሎ 3 ሺህ 600 ብር እያቀረቡ እንደሚገኝ ጠቅሰው፣ የገበያ ማዕከሉ የደላሎችን ሚና ያስቀረ በመሆኑ ውጪ ላይ ለገበያ ከሚቀርበው ዋጋ 15 በመቶ ቅናሽ በማድረግ እየሸጡ እንደሚገኙ ያስረዳሉ።

የአካባቢው ህብረተሰብ በተለይም በበዓላት ወቅት በብዛት ምርቶችን እየሸመተ እንደሚገኝ በመግለጽ፣ ከአዲስ ዓመት በዓል በኋላ ግን መቀዛቀዝ ማሳየቱን ይገልጻል።

ለሸማቹ ምስር፣ ማካሮኒ፣ የሀገር ውስጥ ሩዝ፣ ዱቄት፣ የተለያዩ የጥራጥሬ ምርቶችን እያቀረቡ እንደሚገኝ ጠቅሰው፣ አተር ክክ በኪሎ 130 ብር ፣ሩዝ 115 ብር፣ የሽሮ እህል 115 ብር፣ ድፍን ምስር 158 ብር ማካሮኒ 110 ብር እያቀረቡ መሆናቸውን ያስረዳል።

በማዕከሉ የመብራት እየቀረበላቸው መሆኑን በመግለጽ፣ ነገር ግን የውሃ ችግር አሁንም እንዳለባቸውም ይገልጻል። በገበያ ማዕከሉ ሽንኩርት፣ ቲማንቲም፣ ጥቅል ጎመን፣ አቦካዶና የግብርና ምርቶችን እያቀረቡ እንደሚገኙ አቶ ኤርሚያስ አማረ ይገልጻል።

ከውጪው ገበያ ከ15 እስከ 20 በመቶ ቅናሽ በማድረግ ምርቶችን ለገበያ ማቅረባቸውን በመግለጽ፣ ሽንኩርት 100 ብር፣ ጥቅል ጎመን 20 ብር እየሸጡ እንደሚገኝና የገበያው ሁኔታ የአካባቢው ሸማቾች እየለመዱ በመሆኑ መነቃቃት እንዳለው ያስረዳል።

በገበያ ማዕከሉ የውሃ ችግር በተወሰነ መልኩ እንዳለና መብራት አቅርቦት ግን መጀመሩን የገለጸው አቶ ኤርሚያስ፣የገበያው ሁኔታ ከዘመን መለወጫ በዓል በኋላ መቀዛቀዙንና ለመስቀል በዓል ግን ጥሩ ሁኔታዎች መኖራቸውን ይናገራል።

የገበያ ማዕከሉ መከፈት ያመረትነውን ምርት በቀጥታ ለገበያ እንድናቀርብ እንደረዳቸው ጠቅሰው፣ በርካታ ምርቶችን ወደ ገበያው ብናቀርብም ሸማቾች እየተጠቀሙበት አይደለምና ሸማቾች ወደ ገበያ ማዕከሉ በመምጣት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል ሲል ይገልጻል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ምክትል ኃላፊ ፍስሃ ጥበቡ በቅርቡ በሰጡት መግለጫ በገበያ ማዕከላቱ የሚስተዋሉ የመሠረተ ልማትና ሌሎች ተያያዥ ችግሮችን ለመፍታት በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

በገበያ ማዕከላቱ የሚስተዋለውን የመሠረተ ልማትና የትራንስፖርት ችግር ለማቃለል እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፣ በአሠራሩ ሂደት በአንዳንድ የገበያ ማዕከላት የሚስተዋሉትን የመሠረተ ልማትና ሌሎች ተያያዥ ችግሮች ለመፍታት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ እንደሚገኝም ተናግረዋል።

# የዓለም ቅርሱ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሊቀልሳናት መምህር የኋላወርቅ ኃይለስላሴ እንደሚናገሩት፤ የመስቀል ደመራ በዓል ክብረበዓል ብቻ ሳይሆን የኃይማኖት አባቶችና ምዕመናን በአንድነት ሆነው ለሀገር ሰላምና አንድነት ለፈጣሪ በንፁህ ልባቸው የሚፀልዩበት ነው።

እንደ መምህር የኋላወርቅ ገለፃ፤ የመስቀል በአል የፍቅር፣ የአንድነት፣ የሰላም፣ የመከባበር፣ የጠፋን ነገር የመግለጥ እንዲሁም የትህትና በዓል ነው። በዓሉ ከኢትዮጵያ አልፎ የዓለም ቅርስ በመሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካል ኃይማኖታዊ ሥርዓቱንና ትውፊቱን ጠብቆ ለትውልድ ሊያስተላልፈው ይገባል።

የአሁኑ ትውልድ በተለይም ወጣቱ ከኃይማኖት አባቶች የሚሰጡ የፍቅር፣ የትህትና፣ የአንድነትና የሰላም ትምህርቶችን በመተግበር ለጠንካራ ሀገር ግንባታ በአንድነት መቆም እንደሚገባውም መምህር የኃዋላወርቅ ይመክራሉ።

መምህር የኋላወርቅ በዕምነት ተቋማት፣ በትምህርት ቤት፣ በቤተሰብና በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ሊፈጠሩ የሚችሉ ልዩነቶችን በማጥበብ አንድነትን የሚያጠናክሩ የግብረ ገብ ትምህርቶችን በተግባር መግለጥ ይገባል ነው ያሉት።

የበዓሉን ታሪክ በሚገባ በማወቅ፣ መንፈሳዊ ይዘቱን ሳይለቅ፣ ታሪኩንና ትውፊቱን ጠብቆ ለትውልድ ማሻገር ከሁሉም ምዕመናን እንደሚጠበቅ የሚገልጹት ደግሞ መምህር ሃይለማርያም ቦንሳ ናቸው።

ትውልዱ የመስቀል በዓል ታሪክን በአግባቡ ማወቅና መጠበቅ እንደአለበት የሚጠቁሙት መምህር ሃይለማርያም ቦንሳ፤ መስቀል መንፈሳዊ በዓል በመሆኑ ምዕመናን በዝማሬ፣ በትምህርት፣ በኃይማኖታዊ ሥርዓትና አለባበስ እንደሚያከብሩት ይናገራሉ።

የመስቀል በዓል ንግሥት እሌኒ መስቀሉ ከተቀበረበት በርካታ ዓመታት ያወጣችበት ዕለት መሆኑን በመግለጽ፤ ይህ በዓል በኢትዮጵያ የሚከበረው ንግሥት እሌኒ ግማደ መስቀሉን ለማግኘት ያደረገቻቸውን ጥረቶች በተግባር እየተገለጠ መሆኑ ለየት እንደሚያደርገው መምህር ኃይለማርያም ያወሳሉ።

የፍቅር፣ ትህትና፣ ሰላምና አንድነት መገለጫ የሆነው የመስቀልን አስተምህሮት የአሁኑ ትውልድ በተግባር እንዲያሳይ የኃይማኖት አባቶች አርዓያነት ወሳኝ መሆኑን የሚጠቁሙት መምህር ኃይለማርያም፤ መስቀል የትህትና እና የአንድነት በዓል በመሆኑ የአሁኑ ትውልድ ለሀገር አንድነትና ፍቅር በዕለት ተዕለት ሕይወቱ ሊተገብረው ይገባል ይላሉ።

መምህር አሮን ሱፋ በበኩላቸው፤ የመስቀል በዓል በኢትዮጵያ ከሚከበሩ ታላላቅ በዓላት ውስጥ አንዱ ነው። ከኃይማኖታዊ መገለጫነቱ ባሻገር የዓለም ቅርስ ሆኖ የተመዘገበ ሀብት እንደሆነ በማንሳት፤ በዓሉ ሲከበረም በደስታና መንፈሳዊ ሥርዓትን በጠበቀ መልኩ እንደሆነ ይገልፃሉ።

የመስቀል በዓል በኃይማኖታዊ መገለጫነቱ ትውፊቱን ጠብቆ እንዲቀጥል ማድረግ የሁሉም ሃላፊነት ሊሆን እንደሚገባ የሚጠቁሙት መምህር አሮን፤ በዓሉ ሲከበርም በመስቀሉ የተገለጠውን የክርስቶስ ቤዛነት፣ ፍቅር እና እውነትነት አርዓያ በመከተል መሆን አለበት ይላሉ።

እንደ መምህር አሮን ገለፃ፤ በዓሉ የአንድነት፣ የአብሮነትና የጽናት ማሳያ ነው። በመዋደድ ልዩነትን፣ መራራቅን እና አለመግባባትን በማስወገድ አብሮነትን ማጠናከር የሚቻልበትን መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል።

በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) እውቅና ተሠጥቶት ዓለም አቀፋዊ ቅርስ ሆኖ የተመዘገበ መሆኑን በማስታወስ፤ የኢትዮጵያዊነት መገለጫና የጋራ ሀብት የሆነውን ይህን በዓል እሴቱን ጠብቆ በማክበርና ለትውልድ ማቆየት እንደሚገባ መምህር አሮን ይጠቁማሉ።

የ2017 ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓል በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ፓትሪያሪክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያሪክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ኃይማኖት፣ ብጹዓን አባቶች፣ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ ዲፕሎማቶች፣ የእምነቱ ተከታዮችና የውጭ ጎብኚዎች በተገኙበት ተከብሮ አልፏል።

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሔት

የቁስቡ ገጾች



## የቱሪዝም ዘርፍ ፖለቲካዊ ድጋፍ ማግኘት የጀመረው አሁን ነው

የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ
አቶ ስለሺ ግርማ

ገጽ 7



ወጣት ቶፊቅ እስማኤል ሃኪም፣

## ስነ ተዋልዶ ጤና- ከተደራሽነት ወደ ጥራት

ገጽ 9



ወይዘሮ ዘነበች ታደሰ

## የገጠሩን ድባብ በከተማ ማሳየት ያስቻለው የጉራጌ ባህል ማእከል

ገጽ 10

# ነፃ ሃሳብ

# ኢትዮጵያ በበረከቶቿ እንድትጠቀም ለሰላም ትልቅ ትኩረት እንስጥ!

**ታሪኩ ዘለቀ**

አሁን ወቅቱ ቱሪዝማችን ነፍስ የሚዘራበት ወቅት ነው። ክረምቱ እየወጣ ሲመጣ የሚተካው ልምላሜ ምድሪቱን አረንጓዴ አልብሶና በአበቦች አስጊጦ ጎበዝ ሰአሊ በታላቅ ጥንቃቄ ከሳለው ስእል ያስበልጣታል። በሚገባ አልተጠቀምንበትም እንጂ ፈጣሪ ከማንም ሳያሳንስ ከብዙዎቹም አስበልጦ ይቺን ሀገር ሰጥቶናል። ተፈጥሮዋ፣ ታሪኳ፣ ባህሏ፣ ህዝቧ ከማንም በላይ የመጎብኘት እምቅ አቅም አለው። አሸንዳ፣ ሶለል፣ ሻደይ፣ ጎቤ፣ ሺኖዬ፣ ጳጉሜን፣ አዲስ ዓመት፣ መስቀል፣ ኢሬቻና ሌሎችም የነሐሴና የመስከረም በረከቶች ናቸው።

ቱሪዝም የገቢ ምንጭ ብቻ አይደለም። መልካም ገፅታ መገንቢያ፣ ማህበረሰብ ማነቃቂያ፣ እርስ በርስ መተዋወቂያ፣ የዓለም አንድ አካል መሆኛም ጭምር ነው። እርግጥ ነው የባህል መደበላለቅ፣ የባህል መበረዝና ሌሎችም ይፈሩ እንጂ የራስን አጥብቆ ይዞ መጎብኘት ከእነ ሕንድና ከእነ ቻይና ልንማር እንችላለን። ወደ ቱርክና ቻይና ሄዶ የሚመለስ ሰው ጠንካራ፣ ደረጃውን የጠበቀ፣ ራስን ያከበረ መስተንግዶ ስለሚጠብቀው ቱርካዊና ቻይናዊ ይሆናል እንጂ ባህልን በክሎ አይመለስም።

ቱሪዝም የብዙ ሀገራትን ቀዳዳ ደፍኗል። በተለይም እንደ እኛ ላሉ የግብርና ምርት ፈልገው ትልልቅ ማሽኖችን፣ መድኃኒቶችንና ነዳጅን የሚያስገቡ ሀገራት መቼም ቢሆን የንግድ ልውውጣቸው ተመጣጥኖላቸው አያውቅም። የግብርና ምርቶችም ገቢያቸው በራሳቸው የመወሰን ደረጃ ላይ ባለመድረሳቸው ገዢያቸው የሰጣቸውን ዋጋ ተቀብለው ነው የሚሄዱት። ይሄ የገቢና የወጪ ንግድ አለመመጣጠን ከሚስተካከልባቸው መንገዶች መካከል ዋናው ቱሪዝም ነው።

ቱሪዝም ተፈጥሮ የሰጠችንን ሀብት፣ እውቀትና ውበት ጨምረንበት የሀገር ኢኮኖሚ ዋልታ እንዲሆን መስራትን የሚጠይቅ ዘርፍ ነው። የቡና ቱሪዝም ብቻ እንኳ ብንጀምር ቡና ሸጠን ከምናገኘው ገቢ ቡናን ለመጎብኘት ከሚመጡት እጥፍ ማግኘት እንችላለን። የቡና መገኛ መሆናችን ብቻ በየዓመቱ ሚሊዮኖችን መሳብ በቻለ ነበር። ለዚህም ዋናው ስራ ማስተዋወቅ ላይ መጠንከር ያስፈልጋል። ከተለመዱት ጎብኚዎች ባሻገር ሌሎች አፍሪካዊያን፣ አረቦች፣ ሕንዶች፣ ቻይናዎች፣ ሩሲያኖች እንዲመጡ ብናደርግ ቱሪዝሙን እናስፋፋዋለን።

መጥራት ብቻ ሳይሆን ስም ብቻ ሆኖ የቀረብን ኢትዮጵያዊ መስተንግዶን አስተካክለን ማረፊያና የሚታዩ ነገሮችን ሰርተን ብንጠብቃቸው ኢትዮጵያን አለመውደድ፣ አለመጎብኘት አይቻልም። በዚህ ረገድ ጠቀሜታቸው የገዘፈ የገበታ ለሀገር፣ የገበታ ለሸገርና ሌሎች ፕሮጀክቶች ግንባታ ለውጥ እያመጣ ነው። መንግስት ከለውጡ በኋላ በሰፊው ለቱሪዝም ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው። በተለያዩ አካባቢዎች የተገነቡ የቱሪስት መዳረሻዎች ቱሪስቶችን በመሳብ የሀገሪቱን ገቢ ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ ናቸው።

በእርግጥ አሁንም የሀገራችን ቱሪዝም ሊለማ በሚችልበት ልክ ያልለማና በዘርፉ ዜጎች ተሰማርተው ተጠቃሚ እንዳልሆኑ በተደጋጋሚ ይነሳል። የኢትዮጵያ ቱሪዝም እንደዘርፍ ትኩረት ስቦ በተቋም መመራት ከጀመረ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ ያስቆጠረ ቢሆንም አሁንም ገና ያልተነካና

**ቱሪዝም ተፈጥሮ የሰጠችንን ሀብት፣ እውቀትና ውበት ጨምረንበት የሀገር ኢኮኖሚ ዋልታ እንዲሆን መስራትን የሚጠይቅ ዘርፍ ነው። የቡና ቱሪዝም ብቻ እንኳ ብንጀምር ቡና ሸጠን ከምናገኘው ገቢ ቡናን ለመጎብኘት ከሚመጡት እጥፍ ማግኘት እንችላለን**

በእምቅነት ደረጃ ያለ ነው። አሁን ላይ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በሁሉም ዘርፍ ማሻሻያ ለማድረግ እቅድ ሲዘጋጅም ትልቅ ትኩረት ከተሰጣቸው መስኮች መካከል አንዱ ቱሪዝም ነው።

ኢትዮጵያ ካላት እምቅ የቱሪዝም አቅምና መዳረሻዎች አንፃር እያገኘች ያለችው ጥቅም አነስተኛ መሆኑ የሚነሳበት ዘርፉን ለማዘመን የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ሰፊ ዝግጅት እና ካፒታል የሚጠይቅ ነው። ኢትዮጵያ በቂ ሊባል የሚችል ተፈጥሯዊና ታሪካዊ ቅርስ አላት። እንደ ገበታ ለሀገር ያሉ ፕሮጀክቶች ደግሞ ተጨማሪ የቱሪስት መዳረሻ በመሆን የቱሪስትን ፍሰት ይጨምራሉ። የፕሮጀክቶች መተግበር ሀገሪቱ በሀብት ላይ ሀብት ማካበት እንድትችል እድል ይሰጣታል።

እ.ኤ.አ በ2019 ከአጠቃላይ የዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ 10 በመቶ ድርሻ ያለው እንደሆነ የሚነገርለት ቱሪዝም ለ334 ሚሊዮን ሰዎችም ስራ መፍጠር ያስቻለ ነው። ኢትዮጵያም ነባራዊ ሁኔታን ለመቀየር እና ዘርፉ በኢኮኖሚው ውስጥ ተገቢውን ድርሻ እንዲይዝ እስቻይ ስራዎችን እያከናወነች ነው።

ኢትዮጵያ ተፈጥሮን፣ ታሪክንና ምጡቅ የአእምሮ ውጤቶችን በመጠቀም የቱሪስት መዳረሻዎችን እየገነባች ነው። ከነበሯት መዳረሻዎች በተጨማሪ አዳዲስ መዳረሻዎችን መገንባቷ ብዝሀነት ያለው የቱሪዝም ሀብት እንዲኖራት ያደርጋል። የመስህብ ቦታዎቹ /ወንጪ፣ ጎርጎራ፣ ኮይሻ፣ ጨበራ ጩርጩራ.../ የሀገርን ገፅታ ከመገንባት በተጨማሪም የቱሪዝም ዘርፉ ለዜጎች የስራ እድል ፈጠራና የውጭ ምንዛሬ ምንጭም እንዲሆን ያስችለዋል።

መሰል የቱሪዝም መዳረሻዎች በሰፉ ቁጥር እነሱን ተከትሎ ደግሞ የቱሪዝም ኢንቨስትመንቱ እያደገ ይመጣል። አንድ በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ የቱሪዝም መዳረሻ ሲፈጠር ሌሎች ባለሀብቶች የስራ እድል ይፈጥርላቸዋል ወይም አዳዲስ የቢዝነስ ድርጅቶች ይፈጠራሉ። የቱሪዝም መዳረሻዎች አካባቢ የሚገኙ ዜጎች ጭምር ተጠቃሚ ይሆናሉ። ይህ ብቻ ሳይሆን ከቱሪዝሙ በተገኘው ገቢ ደግሞ የመሰረተ ልማት አገልግሎትን ያገኛሉ። የተገነቡትም ሆኑ እየተገነቡ ያሉት የቱሪዝም መዳረሻዎች ቱሪስቶችን ወደ ሀገር ከመሳብ በተጨማሪ በሀገራችን የሚቆዩበትን ጊዜ ማራዘምና የማይረሳ ትዝታ ውስጥ አስገብቶ ደጋግመው እንዲመጡ በማድረግ ዋነኛው የገቢ ምንጭ ናቸው።

ይህንን በአግባቡ የተረዱት በቱሪዝም ፍሰታቸው የሚታወቁ ሀገራት ከዋናው ከሚጎበኘው መስህባቸው በተጨማሪ የተለያዩ የመዝናኛና የመገበያያ ስፍራዎችን ያዘጋጃሉ። ተራራ መውጣት፣ ጫካ ውስጥ ማደር፣ የተገደበ አደን፣ የሙዚቃ፣ የምግብና መጠጥ ፌስቲቫሎች እና መሰል ድርጊቶች ብዙ ቦታዎች ላይ ይዘወተራሉ።

በተቃራኒው ኢትዮጵያ እጅግ ብዙ የቱሪስት መስህቦች ቢኖሯትም የሚጎበኙላት በጣም ጥቂቶቹ ናቸው። እነሱም ቢሆን በቂ የሚባል መጓጓዣ እንኳ የሌላቸው ናቸው። የሚመጡትም ቱሪስቶች ያዩትን ካዩ በኋላ ወዲያውኑ ስለሚወጡ የያዙትን እውቀት፣ ገንዘብ፣ ልምድና ሀሳብ እንደያዙ ይወጣሉ። በዚህም ብዙ ነገር ስናጣ ቆይተናል።

የገበታ ለሀገር፣ የገበታ ለሸገር፣ የወንዝ ዳርቻ ልማት፣ የኮሪደር ልማትና መሰል ፕሮጀክቶች መተግበር ከጀመሩ በኋላ የቱሪስቶች ቆይታ እየተራዘመ መጥቷል። በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ ለሚደረጉ ጉብኝቶች ማረፊያ የሆነ ቦታ ማግኘት አስቸጋሪ ነበር። የተለመዱ ሆቴሎችና መስተንግዷቸው ያው የተደጋገመ ስለሚሆን የሚስብ ነገር ማግኘት አይቻልም ነበር።

ታዲያ የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች ታሪክን ከተፈጥሮ ጋር አጣምረው በመያዝ ሁነኛ መፍትሄ ሆነው አምረውና ደምቀው ብቅ ብለዋል። የተፈጥሮ ስጦታቸው ላይ ውበት የዘሩባቸው እጆች ስዕል እንጂ በእውኑ ዓለም የሌሉ እስኪመስሉ ድረስ አሳምረዋቸዋል። በውሀ ዳር ውበት ከተለየን ከሰላሳ ዓመታት በኋላ ባህርን፣ ውበትንና ታሪክን አጣምረው የሪዞርቶች ቁንጮዎች ሆነው በየአካባቢያቸው ተገማሽረዋል። «ኑ እዩን፣ ኑ ተፈጥሮና ጥበብ ሲጣመሩ የሚፈጥሩትን እፁብ ድንቅ ትዕይንት ተመልከቱ...» እያሉ ነው።

ከዚህ በኋላ የትኛውም ቱሪስት እንደመጣ አይወጣም። የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች ማግኔቶች ናቸው፤ ይስቡታልም፣ ያጣብቁታልም። በኮይሻ፣ በደንዲ ወንጪና በሌሎችም ያየነው የመዳረሻ ልማት እምቅ የውበት መጠናችንን ብቻ ሳይሆን የመወሰን እና የመቻል ብቃታችንን የሚያስመሰክር ነው። እነ ሀይቅ፣ አሸንጌ፣ አባያ፣ ጫሞ እና ሌሎችም ይቀጥላሉ።

አሁናዊው ቱሪዝም ታሪካዊ ወይም ባህላዊ አሊያም ሀይማኖታዊ ቅርሶች ብቻ የሚታዩበት አይደለም፤ እንዲያውም ዘመናዊው መዝናኛ የበዛበት እየሆነ ነው። ጥንታዊ ታሪኮች ከጥቂት ድግግሞሽ እና አድናቆት በኋላ ለራሱ ለታሪክ ተትተው፤ ተለዋዋጭና አዳጊው ዘመናዊው ቱሪዝም እየተፈለገ ይገኛል።

እነ ፈረንሳይ፣ ስፔን፣ አሜሪካ እና መሰል ሀገራት ሁልጊዜ የቱሪስቶችን ቀልብ የሚይዙት ከሕዝባቸው ቁጥርም በላይ አስተናግደው ቢሊዮን ዶላሮችን የሚዝቁት ጥንታዊ ወይም ታሪካዊ ብቻ ስለሆኑ አይደለም። ምናልባት ስፔንና ፈረንሳይ ከጥንቱ የሚወስዱት ቢኖራቸውም አሜሪካ ግን ዘመናዊ ነች። የእነ ፈረንሳይም ጥንታዊነት ከነቻይና፣ ግብፅ፣ ሕንድ፣ ኢትዮጵያ ጋር የሚወዳደር አይደለም። ነገር ግን ፈረንሳይ አሁንም በቱሪዝም መስከ መሪ ነች።

እንደ ዘመናዊ ቱሪዝም ምንጭ ከሚታዩት መካከል አንዱ የሆነው የኮንፍረንስ ቱሪዝም ጥሩ ጥሩ ሆቴሎችን፣ መጓጓዣዎችን፣ መሰብሰቢያዎችንና መዝናኛዎችን መገንባት ብቻ የሚፈልግ ነው። ለዚህ ነው የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች ቱሪስቶችን በመሳብ ግንባር ቀደም እየሆነች ያለችው። ሳውዲም ትሪሊዮን ዶላር እያወጣች ያለችው ራሷን እንደ አዲስ ለመገንባት ነው።

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያም ጥሩ ጅምር ላይ ያለች ሀገር ነች። ከታሪካችን፣ ከልምዳችን፣ ከአፍሪካ ኅብረት መቀመጫነታችን የተነሳ ብዙ ኮንፍረንሶችን ብናስተናግድም የከተማችን ውበት፣ ሆቴል፣ መዝናኛና መሰብሰቢያ ምቹ ነበሩ ብለን መናገር አንችልም። ለዚህም ይመስላል አንዳንዶቹን እነ ኪጋሊ፣ ናይሮቢና ሌሎቹም ሲነጥቁን የነበሩት። አሁን አሁን እየሰራናቸው ያሉ ስራዎች በተጨባጭ የከተማዋን ውበት እና ፅዳት ከመጠበቅ አንፃር ትልቅ ለውጥን እያመጡ ነው።

ባለፈው ሳምንት ያስተናገድነው የአፍሪካ ከተሞች ፎረም እንኳ የተካሄደው በአድዋ መታሰቢያ አዳራሽ ውስጥ መሆኑ ለእኛ ትልቅ ለውጥ ነው። ተሰብሳቢዎቹ ወጣ ሲሉ ወደ እንጦጦ አሊያም ወዳጅነት ፓርክ መሄድ ችለዋል። ነገ ከነገወዲያ ደግሞ እነ ወንጪ፣ ጎርጎራና ሌሎቹም እንደዚሁ አይነት ኮንፍረንሶችን ያስተናግዳሉ ማለት ነው። የቱሪዝሙ ገቢ በዚያው መጠን ይጨምራል፤ የሀገሪቱም ገፅታ ይስተካከላል።

የሀገራችን ትልቁ ችግር የሆነው የቤት ግንባታ ሲሟላ፣ የትራንስፖርት እጦቱ ሲቀረፍ፣ ድህነትና መፈናቀል ወደ ልመና የገፋው ኑሮ ተስተካክሎለት መመለስ ሲቻል፣ መልካም አስተዳደር ችግሮች ሲስተካከሉ ሀገራችን ለውስጥም ለውጪም የምትመች ተመራጭ በታደለችው ውብ ተፈጥሮ ላይ በዘመናዊነት የተሸለመች ገነት ትሆናለች።

ይሄ ግን የሁላችንንም ጥረትና ስራ የሚፈልግ ነውና በጋራ እንበርታ! ከሁሉም በላይ እምቅ የቱሪዝም አቅም እያላት ከዚህ ዘርፍ የሚገባትን ጥቅም ሳታገኝ የቆየችው ኢትዮጵያ አሁን በተገነቡት ገበታ ለሀገር በረከቶች ተጠቃሚ እንድትሆን ለሰላም ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል።

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

# የቱሪዝም ዘርፍ ፖለቲካዊ ድጋፍ ማግኘት የጀመረው አሁን ነው

*የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ*
*አቶ ስለሺ ግርማ*



**ምሕረት ሞገስ**

በኢትዮጵያ ለቱሪዝም ምቹ ተብለው ከሚጠቀሱ ወራት መካከል የመስከረም ወር ዋነኛው ነው። ወሩ ለቱሪዝም ለምን ምቹ ተባለ? በመስከረም አጠቃላይ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ የቱሪስቶች መጠን እና ገቢ የሚገኝበትን ሁኔታ እንዲሁም በኢትዮጵያ ስለነበረው እና ስላለው የቱሪዝም ዘርፍ እንቅስቃሴ በተጨማሪ መሠራት ባለባቸው ሥራዎች ዙሪያ ከቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ ጋር የነበረንን ቆይታ እንሆ ብለናል። መልካም ንባብ፡-

**አዲስ ዘመን፡- የመስከረም ወር ለቱሪዝም ምቹ ነው ይባላል። ምክንያቱ ምንድን ነው?**

**አቶ ስለሺ፡-** መስከረም በአገር ደረጃ ከክረምቱ ወጥተን አዲስ ዓመትን የምንቀበልበት፤ ፀሃይ የምናገኝበት እንዲሁም ጎን ለጎን የመስቀል እና የእሬቻ በተጨማሪ የዓለም የቱሪዝም ቀን የሚከበርበት ወር ነው። የዓለም የቱሪዝም ቀን እ.አ.አ. መስከረም 27 የሚከበር ሲሆን፤ መውሊድም በዚሁ ወር ነበር። ስለዚህ በአጠቃላይ መስከረም የተለያዩ ክብረ በዓሎች የሚከበርበት ነው።

ክብረበዓል ሁልጊዜም ሰዎች የሚያርፉበት እና የሚደሰቱበት ጊዜ ነው። ክብረበዓሎቹ ባህላዊ እና መንፈሳዊ ይዘት ቢኖራቸውም ሁሉም ሰው የሚደሰትበት ከመሆኑ አንፃር፤ ሰዎች የሚያሸበርቁበት የተለያዩ አልባሳት፣ ጌጣጌጦችን የሚጠቀሙበት እና ከቦታ ቦታ ሰዎችን ለመጠየቅ የሚጓዙበት ነው። በርካታ የምግብ እና የመጠጥ አይነቶች የሚዘጋጁበት ሲሆን፤ መንፈሳዊ ሲሆን ደግሞ ፈጣሪያቸውን የሚያመስግኑበት ጊዜ ነው። በዚህ ምክንያት በመስከረም ወር ሰፊ እንቅስቃሴ አለ። ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጪ ቱሪስት የሚመች ጊዜ ነው፤ የሚል እምነት አለኝ።

መስከረምን ልዩ የሚያደርገው አብዛኞቹ ክብረ በዓሎች ተቀራርበው የሚመጡበት ከመሆን ባሻገር፤ ከክረምት ከደመናው ወደ ብርሃን የምንሸጋገርበት ነው። በተጨማሪ በክብረ በዓሎቹ ምክንያት የተለያየ ዝግጅት ስለሚኖሩ መስከረም ለቱሪስት ምቹ ወር ናት ብሎ መደምደም ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- በመስከረም አጠቃላይ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ የቱሪስቶች መጠን ምን ይመስላል?**

**አቶ ስለሺ፡-** በቱሪዝም ቋንቋ ከጉብኝት ጋር ተያይዞ ሁለት ዋነኛ ወቅቶች ይጠቀሳሉ። አንደኛው ብዙ እንግዶች የሚመጡበት ምርጥ ወቅት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በተለያየ ምክንያት ብዙም እንግዶች የማይመጡባቸው ወቅቶች ነው። ከመስከረም ጀምሮ እስከ ጥር ያለው ጊዜ ሰፊ የቱሪስት ፍሰት ያለበት ወቅት ነው። ጥር እና ታህሳስ አካባቢ የገና እና የጥምቀት በዓላት አሉ። በተለይ ገና የኢትጵያ ገና እና የአውሮፓዎቹ ገና ተቀራራቢ ጊዜ ሲሆን፤ ዘመን መለወጫቸው በመሆኑ የክርስቶስ የውልደት ቀን (ክሪስማርስ ደይ) ብለው ከሥራ ያርፉሉ።

ከሥራ ሲያርፉ ጊዜ ስላላቸው በቀላሉ ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ። ይህ ሁኔታ በሌላው ዓለም ያሉ ጎብኝዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ እድል ይፈጥራል። ስለዚህ በዚህ ወቅት አንደኛ ብዙ ሰው ይመጣል። የቆይታ ጊዜያቸው ይራዘማል። የተለያዩ ክብረ በዓሎች ስላሉ እና ሁሉም እነርሱ ላይ ስለሚሳተፉ አብዛኛውን ቱሪስት የምናገኘው በዚህ ወቅት ነው። ወደ አገራችን ከ70 በመቶ በላይ የሚሆኑ ቱሪስቶች የሚመጡ ከመስከረም እስከ ጥር ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የተለያዩ አገራት በቱሪዝም ከፍተኛ ገቢ ለማግኘት ብዙ መንገዶችን ይጠቀማሉ። ኢትዮጵያ ከቱሪዝም ወይም ከቱሪስት ገቢ የምታገኘው በምን መንገድ ነው?**

**አቶ ስለሺ፡-** ቱሪስቶች ወደ አገራችን ሲገቡ መጀመሪያ አውሮፕላን ይጠቀማሉ። ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ከመጡ በትራንስፖርት ከአየር በረራ ገቢ ይገኛል። በመቀጠል ከአስጎብኚ ድርጅቶች ፓኬጅ ይገዛሉ፤ ማለትም የሆቴል አገልግሎት፣ የመኪና ኪራይ እና ሌሎችም የሚፈልጓቸውን አገልግሎቶችን እንዲሁም ከጉብኝት ቦታዎች የሚያገኙዋቸውን የተለያዩ አገልግሎቶችን ጨምረው ከአስጎብኚ ድርጅቶች ጥቅል ይገዛሉ።

በተናጠል የመጡ ከሆኑ ደግሞ ለትራንስፖርት፣ ለሚያርፉበት ሆቴል፣ ለሚመገቡባቸው ሬስቶራንቶች ክፍያ ይፈፅማሉ። በተጨማሪ ለአስጎብኚዎች ይከፍላሉ፤ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ መኪና መጠቀም አለባቸው ወይም የአገር ውስጥ በረራ ይጠቀማሉ። ከዚሁ ጎን ለጎን ከጫማ ማስጠረግ ጀምሮ በተለያየ መስክ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለሚሰጧቸው ሰዎች ክፍያዎችን ይፈፅማሉ። እንደአገር በቱሪዝም ዘርፍ አገኘን የምንለው፤ ከእነዚህ ሁሉ የሚሰበሰብ ገቢ ነው።

በእዚህ ወር የሚካሔዱ ኩነቶች ላይ ከበዓላት አከባበር ጋር ተያይዞ የአገር ውስጥ ቱሪስቶችም ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ፤ ይህ ቀላል አይደለም። ለምሳሌ የደቡብ ተወላጆች በጣም ወደ ተለያዩ ቦታዎች ይሔዳሉ። በተለይም ጉራጌዎች ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ። በሚሔዱበት ጊዜ በተመሳሳይ መልኩ ለትራንስፖርት ወጪ ያወጣሉ። በበዓሉ ምክንያት ምግብ እና መጠጥ በልዩ ሁኔታ ይዘጋጃል። ከገበያ ከመግዛት ጀምሮ እነኚህን ምግቦች አዘጋጅተው እስከሚጨርሱ ድረስ በርካታ ወጪ ያወጣሉ።

የመስቀል በዓል መንፈሳዊ ነገርም አለው። አለባበሱም የተለየ ነው። እሬቻም የራሱ የተለያዩ መዋቢያ አለው። ሌሎችም ክብረ በዓሎች በተመሳሳይ አልባሳት፣ ጌጣጌጦች እና የተለያዩ የዕደ ጥበብ ምርቶች ሰፊ ገበያ ይኖራቸዋል። ብዙ ሰዎች የዕደ ጥበብ ምርቶችን በሰፊው አምርተው ለገበያ የሚያቀርቡበት በተለይም ባህላዊ አልባሳት ከመቼውም በላይ ለሽያጭ የሚቀርቡበት ጊዜ ነው። በዚህ ጊዜ በዋናነት ባህላዊ አልባሳት እና ጌጣጌጦች ሰፊ የገበያ ሽፋን አላቸው።

በተለይ ባለፉት ሶስት እና ሁለት ዓመታት አገር ውስጥ የሚከበሩ በዓሎች ላይ በልዩ ድምቀት ለማክበር ወጣቶች፣ አዛውንቶች እና ህፃናት ብዙ ገንዘብ አውጥተው መዋቢያ እና ማጌጫ አልባሳት እና ጌጣጌጦችን እየሸመቱ ነው። ከዛ ጎን ለጎን የሙዚቃ ዝግጅቶች ይደረጋሉ። እነዚህ ሁሉ ቀላል የማይባሉ የገንዘብ እንቅስቃሴዎች እንዲኖሩ፣ ኢኮኖሚው እንዲነቃቃ፣ ገበያው እንዲያንሰራራ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በተጨማሪ የሰዎች እንቅስቃሴ የተሻለ እንዲሆን ያግዛሉ፤ ይህ ሲባል ስነልቦናዊ እና የሳይኮሎጂ ጠቀሜታም አላቸው።

በዓሉን ወደ ተለያየ ቦታ በመሔድ የሚያከብሩ ዜጎች ከነበረባቸው ድብርት እና የሥራ ጫና እንዲሁም ድካም በመላቀቅ ለራሳቸው በአዲስ መልክ አዲስ ሃይል እንዲያገኙ ጠቀሜታ አላቸው። ስለዚህ በዓላቱ ማኅበራዊ ጠቀሜታም አለው። በኢኮኖሚ በኩል ኢኮኖሚውን ያነቃቃል፤ ከአገር ውስጥ ቱሪስት አንፃር ደግሞ ስነልቦናዊ እና ማኅበራዊ ጥቅም አለው ማለት እንችላለን።

**አዲስ ዘመን፡- መስቀል እና ደመራ ብቻ ሳይሆን በመስከረም የተለያዩ ብሔሮች ዘመንን ከመለወጥ ጋር ተያይዞ ለቱሪስት መስዕብ መሆን የሚችሉ ባህላዊ የበዓል አከባበር ሥርዓት አላቸው። ይህንን ከቱሪዝም ዘርፍ ጋር ለማስተሳሰር ምን ያህል እየተሠራ ነው?**

**አቶ ስለሺ፡-**ብዙ ጊዜ እንዲህ ዓይነት ክብረ በዓላት መንፈሳዊ፣ ባህላዊ፣ ቱፊታዊ ወይም ታሪካዊ ይዘት አላቸው። ማለትም ለምሳሌ ዓድዋ ታሪካዊ በዓል ነው። እንዲህ ዓይነት የአደባባይ በዓሎች በሚከበሩበት ጊዜ በብዙ ዓለም እንደተለመደው የቱሪስት ፍሰቱ ለአገር ውስጥ ነው። ነገር ግን የውጪ ቱሪስቶች አገራችንን ለመጎብኘት በሚመጡበት ጊዜ እንዲህ ዓይነት በዓላት መኖራቸው ይስባቸዋል።

በዓላቱ በዓመት አንድ ጊዜ የሚገኙ በመሆናቸው ይበልጥ ሰዎች እንዲመጡ ያደርጋሉ። በዚህ ምክንያት እንደቱሪዝም ሚኒስቴር የተለያዩ አማራጭ የጉብኝት ፓኬጆችን እየቀረፅን እንገኛለን። የግል ዘርፉም በዚህ ጊዜ እንዲቀርፅ እናደርጋለን። ዓላማው ቱሪስቶች ለጉብኝት ሲመጡ፤ በዓል በሚከበርበት አቅራቢያ እንዲጎበኙ ማበረታታት ነው። ለምሳሌ መስቀል በጉራጌ የሚከበር በመሆኑ በጉራጌ ክልል የሚገኘውን ጢያ ትክል ድንጋይ በዚህ ወቅት ፕሮግራማቸው ውስጥ እንዲያካትቱት እናበረታታለን። ስለዚህ ጎብኚዎቹ ጥያን ብቻ ከሚያዩ ከጢያ ትክል ድንጋይ ባሻገር የመስቀል በዓልን በጥሩ ሁኔታ አክብረው ተደስተው የሚሔዱበት ሁኔታ እንዳለ አይተናል። ስለዚህ በዚህ መንገድ ፕሮግራሞች እንዲቀረፁ የማስተዋወቅ ሥራ እየሠራን ነው።

በተጨማሪ በዓላቱን በሚመለከት መረጃዎችን የተለያዩ አጫጭር ቪዲዮዎች እና ማኅበራዊ ድህረገፆች እንዲሁም በሌሎችም አማራጮች እንዲተዋወቁ እናደርጋለን፤ ግንዛቤ እንፈጥራለን። በዓላቱን በሚመለከት በማህበረሰቡም ዘንድ በቂ ዕውቀት እንዲኖር እና ሰዎች ጊዜ እና ገንዘብ መድበው ወደየቦታው እንዲሔዱ እና እንዲያከብሩ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ እንሠራለን። በቀጣይ ግን ለውጪ አገር ቱሪስቶች በደንብ ትኩረት በመስጠት ገና እና ጥምቀት እንደሚተዋወቀው ሁሉ እነዚህም ክብረ በዓላት በበቂ ሁኔታ ታውቀው እንዲጎበኙ በውጭ አገር በሚካሔዱ ተሳትፎዎች ላይ አዳዲስ ነገሮች በምናቀርብባቸው ፓኬጆች እንዲተዋወቁ ሙሉ ሥራ ተጀምሯል።

የማስተዋቅ ሥራ በቀጥታ ወዲያው ውጤቱ አያሳዩም። ነገር ግን በጊዜ ሒደት የሚፈለገውን ገቢ ያስገኛል። እስከ አሁን በሠራነው የማስተዋወቅ ሥራ የሚገኘውን ውጤት ወደ ፊት እናየዋለን። ከዚህ ውጪ አሁንም ቢሆን አነስተኛ ቢሆኑም ቱሪስቶች እየመጡ ነው። የማስተዋወቅ ሥራውን ገና እየሠራን ስለሆነ ወደ ፊት ደግሞ በሰፊው ሊመጡ የሚችሉበት ዕድል ይኖራል ብለን እናምናለን።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፍ ላይ ብዙ ሥራዎች እየተሠሩ ስለመሆናቸው ይነገራል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድም በኢጋድ በቱሪዝም ዘርፍ ተሹመዋል። በእርግጥ አሁን ላይ ምን ያህል ውጤታማ እየሆንን ነው?**

**አቶ ስለሺ፡-** በእኔ እምነት አገራችን ውስጥ አሁን ካፈራናቸው ገበታ ለሸገር እና ገበታ ለአገር ፕሮጀክቶችን ካየን በጣም ጥሩ ውጤት መጥቷል። እንደባለሞያም ሊታይ የሚችል ትልቅ ለውጥ አለ። ለምሳሌ በገበታ ለሸገር በተሰሩ ፕሮጀክቶች እንጦጦ፣ ወዳጅነት ፓርክ እና አንድነት ፓርክን ካየን አንድነት ፓርክ ማጋነን ካልሆነ በአገራችን ውስጥ ካሉ የቱሪስት መዳረሻዎች ውስጥ ገንዘብ እየተከፈለ በዚህ ቁጥር መዳረሻ አለ ለማለት ያዳግታል።

አንድነትን በዓመት ከ300ሺህ ሰው በላይ ሰው ገንዘብ ከፍሎ እየጎበኘ ነው። አብዛኞቹ የቱሪስት መዳረሻዎቻችን ምን ያህል ሰው እንደሚጎበኛቸው ይታወቃል። በተጨማሪ እንጦጦም ቢሆን በጣም ብዙ ሰው የሚሳተፍበት ስፖርት እየተካሔደበት እየተጎበኘ ነው። ወዳጅነት ፓርክም ቢሆን የተለያዩ ፕሮግራሞች እና ብዙ ሰርጎች እየተካሔዱበት ሲሆን፤ ቀን እና ማታ ሰዎች ስፖርት የሚሰሩባቸው እና ወላጆችም ልጆችን ይዘው የሚዝናኑባቸው ሁኔታዎች በስፋት ተፈጥረዋል። ስለዚህ በዚህ ምክንያት እነዚህ ቦታዎች በሙሉ ገፅታን በመገንባት እና በበርካታ ሰዎች በመጎብኘት ሌላው ቀርቶ በገቢ ደረጃ በሚሰበሰብ ገንዘብ ሌሎች መዳረሻዎችን ማልማት ጀምረናል። ስለዚህ የቱሪዝም ዘርፉ አሁን ያለበትን ደረጃ በተመለከተ እጅግ በጣም ውጤታማ ሥራ እየተሠራ ነው ማለት ይቻላል።

ከቱሪዝም አንፃር ኢትዮጵያ ውስጥ ቱሪዝም ገና አዲስ እየተጀመረ ነው። ዘርፉ የፖለቲካ ድጋፍ እና ትኩረት ማግኘት የጀመረው ገና አሁን ነው። ከዛ ውጪ የቆየነው ግብርና መር ኢንደስትሪ መር እየተባለ ነው። አሁን ያለው ትኩረት ከቀጠለ ገና ብዙ መዳረሻዎች እና መሰረተ ልማቶች መሠራት አለባቸው። የአገልግሎት ጥራት አሁንም ፈተና ውስጥ ነው። የአገልግሎት ጥራት እንዲሻሻል የሆቴሎችን ደረጃ መመደብ፤ ከዚህ በፊት

**ወደ ገጽ 8 ዞሯል**

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

## የዘመን እንግዳ

# የቱሪዝም ዘርፍ ፖለቲካዊ ድጋፍ...



ከ7ኛው ገጽ የዞረ

የተመደቡትንም ዳግም ደረጃ መስጠት ያስፈልጋል።

ሬስቶራንቶችን እና አስጎብኚ ድርጅቶችን እስከ አሁን ድረስ ጥራታቸውን መቆጣጠር እና ደረጃ መመደብ ላይ አልደረስንም። አሁን መመሪያ በማፅደቃችን ወደ ምደባ እንገባለን። ስለዚህ መሥራት ካለብን አንፃር ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል። ነገር ግን የተሰሩት ፕሮጀክቶች በጣም ውጤታማ ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል።

በሌላ በኩል ውጤታማነቱን በትንሹ ለመግለፅ ያህል ብዙ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል። የውጪ ምንዛሪ እየተገኘባቸው ነው። በተጨማሪ አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና ናት እየተባለ ከሌሎች ከተማ ጋር ስትወዳደር የነበረችበት የሚታወስ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ እየኖሩ ያሉ የሌሎች አገር ሰዎች ማለትም የውጪ ዜጎች ሊዝናኑባቸው እና ሊኖሩባቸው የሚችሉባቸው ቦታዎች ተፈጥረዋል። ይህም ትልቅ ፋይዳ አለው። ከኢኮኖሚው ባሻገር እነዚህ ፕሮጀክቶች በጣም ውጤታማ ናቸው ጥሩ ውጤት አስገኝተዋል ብዬ አምናለሁ።

ገበታ ለሸገር አልፎ ተርፎ ገበታ ለአገር ከታየ ወንጪ፣ ኮይሻ እና ሃላላ በጣም በጥራት የተሰሩ ሲሆኑ፤ አንዳንዶቹ ምናልባት በቀላሉ ሰው ሊደርስባቸው የማይችሉበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ለምሳሌ ጎርጎራ፣ ጨበራ እና ወንጪ ብዙ ሰው በቀላሉ ሊሔድ እና ሊጎበኛቸው ይችላል። በሌላ በኩል አንዳንድ የሰላም እጦት ያሉባቸው ቦታዎች እንዳሉ ሆነው የሰላም ሁኔታው ሲስተካከል ደግሞ በጣም በሰፊ ቁጥር መጎብኘት የሚችል ይሆናል።

በአቅርቦት በኩል ስናይ በደንብ ማወቅ ያለብን ብዙ ጊዜ ቱሪዝም የተዘነጋ ክንፍ ነው። ብዙ ጊዜ ምን ያህል ቱሪስት መጣ ይባላል። ይህ የፍላጎት ጉዳይ ነው። ስንት ቱሪስት ፈልጎ መጣ እንላለን ነገር ግን ትልቁ ሥራ አቅርቦት ነው። መጀመሪያ የሚጎበኝ መስዕብ አለ? ሁለተኛው መስዕቡ ወይም መዳረሻው አድጓል? ማለትም ቱሪስቱ የሚፈልገውን ነገር በቅርቡ ያገኛል? አስፈላጊ መሠረተ ልማት ተሟልቷል? በዘመናዊ መልኩ የሠለጠነ፣ የበቃ፣ ዕውቀት እና ሥርዓት ያለው የሰው ኃይል አለን? በየቦታው ምቹ የጉብኝት ስርዓት አለ? የሚሉት ጉዳዮች ብዙ ጊዜ የተረሱ እና ብዙ ሰው የማያስተውላቸው ናቸው። ነገር ግን እነዚህ ብዙ ገንዘብ የሚጠይቁ ሲሆኑ፤ በስፋት እየሠራንባቸው ነው።

ከላይ የጠቀስኳቸው ጉዳዮች በቀላሉ የሚሠሩ አይደሉም። ረዥም ጊዜ ይወስዳሉ። ከፍተኛ አቅም እና እውቀት የሚፈልጉ ናቸው። ጥሩ እየሠራን ነው። እነኚህ ነገሮች ከተሟሉ መዳረሻዎቻችን በቀላሉ በቱሪስቶች የመመረጥ ዕድል ይኖራቸዋል። መጥተው የጎበኙ ሰዎች ደግሞ ተደስተው እነርሱ በመጎብኘታቸው ደግሞ ሌሎች እንዲያዩት ለመናገር የሚችሉበት ዕድል ይፈጠራል። ከምንሰራው ማስተዋወቅ ጋር ተያይዞ በቀላሉ ውጤት ለማምጣት የሚያስችል ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህ አሁን አቅርቦት ላይ በሰፊው እየተሠራ ነው። አገልግሎት ላይ በዓይነት፣ በጥራት በጣም የተቀናጀ እና የተደራጀ በሆነ መልኩ እየተሠራ ነው። አሁን ላይ ለሆቴሎች ደረጃ ለመስጠት እየተዘጋጀን ነው። አራት ኮከብ የተሰጣቸው ሆቴሎች ካላሟላ ወደ ታች ይወርዳሉ። አንድ ወይም ሁለት ኮከብ ያላቸው ሆቴሎች ካሻሻሉ ባለ ሶስት ኮከብ ሆቴል ሊባሉ ይችላሉ። ኮከብ ሰጥቶ ማለፍ ብቻ ሳይሆን በየጊዜው ጥራታቸውን በበቂ መጠን በመከታተል እና ድጋፍ በማድረግ ውጤታቸው ላይ በመመርኮዝ ዳግም የመመደብ ሥራ ይሠራል። ለአዲሶቹ በአዲስ መልክ ደረጃ የመስጠት እና ለነባሮቹም በየሶስት ዓመቱ የደረጃ ማሻሻል ሥራ ይከናወናል።

**አዲስ ዘመን፡-ኢትዮጵያ በአፍሪካ ደረጃ 16 ቅርሶችን ያስመዘገበች ብቸኛ አገር ናት። ይህ ቱሪዝምን ለማስፋት ምን ያህል እገዛ አድርጓል?**

**አቶ ስለሺ፡-**በእርግጥ በዓለም ቅርስ በማስመዝገብ ከአፍሪካ ኢትዮጵያ ቀዳሚ ናት። ከዛ አንፃር ከሌሎች የአፍሪካ አገራት ጋር ስንነፃፀር ያን ያህል ተጠቃሚ ወይም ተወዳዳሪ አይደለንም። ያልሆንበት ምክንያት ከላይ የጠቀስኳቸው ምክንያቶች ናቸው። አንድ ቅርስ ተፈጥሯዊ በሆነ ምክንያት ለምሳሌ ብሔራዊ ፓርክ ወይም ቤተመንግስት አሊያም የሃይማኖት ቦታ ወይም ሌላ ዓይነት መልክ ያለው ቅርስ በዓለም ቅርስነት ሊመዘገብ ይችላል። አመዘጋገቡም ባህላዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ የሚዳሰስ የማይዳሰስ ተብሎ ሊመዘገብ ይችላል። ነገር ግን በዛ መመዝገቡ ብቻ ገቢ ለማስገኘት ዋስትና አይሆንም። ምክንያቱም ለአንድ የቱሪዝም እንቅስቃሴ በአጠቃላይ አስፈላጊ የሆኑ ከላይ የጠቀስኳቸው መሰረተ ልማቶች አሉ። ለምሳሌ የትራንስፖርት ሁኔታው ላይ መንገድ፣ ቴክኖሎጂው ላይ የቴሌኮም አገልግሎቶች ላይ መሻሻሎች መኖር አለባቸው። ነገር ግን ከእነርሱ በተጨማሪ የጤና አገልግሎት ላይ የሰው ኃይል መኖር፣ የሠራተኞች አቅም፣ የሰላም እና የፀጥታ ጉዳይ፣ የፖሊሲ ጉዳዮች እና ሌሎችም በጣም አስፈላጊ የሆኑ የዘርፉን ተወዳዳሪነት የሚወስኑ ጉዳዮች አሉ።

ስለዚህ 16 የዓለም ቅርሶች መኖራቸው በራሱ ከፍተኛ ለመጎብኘት ቀዳሚ አያደርገንም። በራሳቸው ደግሞ አስተዋፅኦ እንዳላቸው መካድ አይቻልም። ዩኔስኮ የመዘገባቸው ቅርስ ያለባቸውን ቦታዎች በዓለም ላይ እየመረጡ የሚጎበኙ ሰዎች አሉ። በኢትዮጵያ የተመዘገበው የቅርስ ቁጥር ሲጨምር ኢትዮጵያን ለመጎብኘት የሚያስቡበትን ዕድል ይፈጥራል። በተመሳሳይ በዓለም ቅርስነት የተመዘገበው ሲታሰብ በዓለም ላይ የተመዘገበው እጅግ የተለያየ ነው። የአንዱ አገር ቅርስ ከሌላው የተለየ ነው። እኛ አገር ያለው ቅርስ ሌላ አገር ያለውን ቅርስ አይመስልም። የእኛ አገር ብቻ ሳይሆን የሌሎች አገሮችም ቅርስ ለሁሉም የየራሱ ጥቅም አለው። የዓለም ሕዝብ የሚማርበት ሊጠብቀው የሚገባ አሻራ ተብሎ ተመዝግቧል። በዚህ ምክንያት ለማስተዋወቅ በቀላሉ ዕድል ይፈጥራል። የዩኔስኮ ቅርስ ነው ስንል የተለየ ነው ሊታይ ይገባል ብሎ ማስተዋወቅ በቀላሉ ሰዎችን ሊያሳምን ይችላል።

በዩኒስኮ መመዝገቡ አዲስ እና ሌላ ቦታ የሌለ ነው የሚል እምነት ስለሚፈጥር የማስታወቂያ ሥራውን ለማሳለጥ እና ህብረት ለመፍጠር ያስችላል። ከዛ በተጨማሪ የዩኔስኮ ቅርስ በሚመዘገብበት ጊዜ የጥገና ሥራ የሚያስፈልጋቸውን በቀላሉ ለመጠገን ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ለምሳሌ ላሊበላን እየጠገን ነው፤ በሌሎች ቦታዎችም ጭምር ጥገና ሲደረግ የላሊባላን የፈረንሳይ መንግስት ቢደግፍ፣ የአክሱምን ጥገና የጣሊያን መንግስት ቢደግፍ እነዚህን ጥያቄዎች ለማቅረብ በዩኒስኮ መመዝገቡ በቀላሉ ሃብት አሰባስቦ ጥገናዎችን እና እዛ አካባቢ ያሉ የመዳረሻ ልማት ሥራዎችን ለመሥራት ዕድል ይፈጥራል ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በዓለም በተከሰተው የኮረና ወረርሽኝ እና ያንን ተከትሎ በመጣው የኑሮ ውድነት ሳቢያ የቱሪዝም ዘርፍ እየተፈተነ መሆኑ ይነገራል። እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ስለሺ፡-** የኮቪድ ጉዳይ ትንሽ ከባድ ነበር። ወረርሽኙ በተከሰተበት ጊዜ በርካታ አጥኚዎች ‹‹የኮቪድ ወረርሽኝ ከወጣ በኋላ በበሽታው ምክንያት ሥራቸው የተጎዳ ዘርፎች ቱሪዝምን ጨምሮ ወደ ነበሩበት ለመመለስ ከአምስት እስከ አስር እና ሃያ ዓመታት ሊያስቆጥሩ ይችላሉ›› የሚሉ መላ ምቶች ነበሯቸው። ነገር ግን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ባወጣው ሪፖርት አብዛኞቹ የዓለም አገራት ላይ የቱሪዝም ዘርፉ 96 በመቶ ወደ ነበረበት ተመልሷል የሚል ነው። ከኮቪድ በፊት የነበራቸውን የቱሪዝም ዘርፍ ገቢ ማግኘት ችለዋል። በኢትጵያ በኩል ግን ከኮቪድ በኋላም የሰሜኑ ጦርነት ቀጥሎ የመጣ በመሆኑ እና በጦርነቱም ምክንያት ሰዎች በቀላሉ ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ በመገደቡ እንዲሁም የኤምባሲ ማስፈራሪያዎች እና ክልከላዎች ከፍተኛ ጫና በመፍጠራቸው ተፅዕኖ ከፍተኛ ሆኗል። በእኛ በኩል ኮንቬንሽን በማቋቋም በርካታ ኮንፈረንሶች ወደ ፊት እንዲመጡ ማድረግ ችለናል።

በጉብኝት ወደ ተለያዩ ቦታዎች የሚሔደውን ቱሪስት በቀላሉ ወደ አገር ውስጥ ማምጣት ካልተቻለ በኤግዚቢሽን፣ በኮንፈረንስ እና የተለያዩ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ሰዎችን ማምጣት እንደስትራቴጂ ይወሰዳል። ያንን መሠረት አድርገን ከጎብኚ የሚገኘውን ያክል ባናገኝም ማካካሻ የተጠቀምንበት ለኮንፈረንስ፣ ለኤግዚቢሽን እና ሌሎችም ኩነቶችን በማዘጋጀት ለማካካስ ሞክረናል። በሆቴሎች በኩል በኮንፈረንስ ምክንያት ሆቴሎች እየተያዙ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በቀጣይ ኢትዮጵያ ከቱሪዝም ዘርፉ ተገቢውን ጥቅም እንድታገኝ ምን ይሠራ? በዋናነትስ ኃላፊነቱን ወስዶ መሥራት ያለበት ማን ነው ይላሉ?**

**አቶ ስለሺ፡-** ከመስከረም ጀምሮ እስከ ጥር ያሉ ወራቶች ብዙ እንግዶችን የምንቀበልበት ወቅት ከመሆኑ አንፃር፤ በተጨማሪ በርካታ ቦታዎች ላይ ከቱሪዝም እንቅስቃሴው ተጠቃሚ የሚሆኑ አሉ። ግብርናም ሆነ ኢንደስትሪ የሌላቸው አካባቢዎች አሉ። ቱሪዝምን ብቻ ማዕከል ያደረጉ አካባቢዎች በመኖራቸው በዛ አካባቢ ያሉም ሆኑ በአጠቃላይ በየትኛውም አካባቢ የሚገኝ ኢትዮጵያዊ ቱሪዝምን ማስተዋወቅ ይጠበቅባቸዋል። አገልግሎት ሰጪዎች ደግሞ አገልግሎት ጥራት ላይ በትኩረት መሥራት ይኖርባቸዋል፤ ያለውን ይዞ መቀጠል ብቻ ሳይሆን በየጊዜው ማሻሻል ይጠበቅባቸዋል።

የአገር ውስጥ ጎብኚዎች ደግሞ የጉብኝት ባህላቸው እንዲያድግ እና ሰዎች ከቦታ ወደ ቦታ በሚጓጓዙበት ጊዜ የተሻሉ ነገሮችን ስለሚያዩ፤ ሰዎች የጉብኝት ባህላቸውን ማሳደግ አለባቸው። ሰዎች ባላቸው ጊዜ አገራቸውን እንዲያውቁ እና እንዲጎበኙ ማድረግም ይጠበቅባቸዋል። መገናኛ ብዙሃንም የኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ እንዲያድግ የማስተዋወቅ ሥራ መሥራት አለባቸው። በተጨማሪ የቱሪዝም ዘርፍ ሥራው ድንበር ዘለል ነው። ለብቻ የሚሠራ ሥራ እና የሚገኝ ዕድገት የለም። መንገድን የሚሠራው የመንገድ ዘርፍ ነው፤ የኮሙኒኬሽን አገልግሎትም በተመሳሳይ ስለዚህ ሁሉም ግዴታውን መወጣት አለበት። የግሉ ዘርፍም በንቃት መሳተፍ ይጠበቅበታል። ሁሉም ግዴታውን ከተወጣ ከፍተኛ ውጤት የማይመጣበት ምክንያት የለም። በተለይ ቱሪዝም እንዲያድግ የግል ዘርፉ ኢንቨስትመንቱን እንዲያስፋፋ እንዲሁም የተሻለ ዘመን እንዲሆን እመኛለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ስለሺ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

# ስነ ተዋልዶ ጤና-ከተደራሽነት ወደ ጥራት

አስናቀ ፀጋዬ

የአፍላ ወጣትነት እድሜ የሕብረተሰቡን የቀጣይ ትውልድ ማፍራት ሁኔታ የሚወስን ነው። በተለይ ደግሞ እንደኢትዮጵያ ባሉ የወጣት ቁጥራቸው ከጠቅላላው ሕዝብ አንፃር ከፍተኛ የሆኑባቸው ሀገራት ለወጣቶች አስቻይ ሁኔታዎች ካልተፈጠሩ፣ ተሳታፊነታቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ካልተረጋገጠ ለሚታሰበው ሀገራዊ ለውጥ እንቅፋት ይሆናል። ስለዚህ በአፍላ ወጣቶችና በወጣቶች ዙሪያ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ መስራት አስፈላጊ መሆኑ ሁሉንም ያስማማል።

ወጣቶች አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ አእምሯዊና ማሕበራዊ ለውጦች የሚከሰትበት የእድሜ ክልል ላይ የሚገኙ በመሆናቸው የሕይወታቸው ሂደትና ኡደት ልዩ ትኩረት የሚሻ ነው። ምክንያቱም በዚህ እድሜ ክልል በሚፈጠሩ ስሜታዊነት፣ የአቻ ግፊቶች፣ የመረጃ እጥረት የተነሳ አፍላ ወጣቶችና ወጣቶች ለጤናና ለተለያዩ ማሕበራዊ ችግሮች ተጋላጭ ይሆናሉ። የስነ ተዋልዶ ጤና ችግር ደግሞ ለኤች አይ ቪ ኤድስ ሌሎች የአባላዘር በሽታዎች፣ ላልተፈለገ እርግዝና፣ ለጽንስ ማቋረጥ፣ ለአደንዛዥ እፆች፣ ለአልኮል መጠጦች፣ ለአእምሮ ጤና እክል፣ ለአካል ጉዳትና ለሌሎችም ችግሮች ተጋላጭ ያደርጋቸዋል።

ስለዚህ አፍላ እድሜ ላይ ያሉ ታዳጊዎችና ወጣቶች ጤናቸው በተሟላ መልኩ እንዲጠበቅ ሁሉም ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል። ጤናቸው አደጋ ላይ እንዳይወድቅ እርስ በርሳቸው ተቀራርበው የሚወያዩበትና ራሳቸው የመፍትሄ አካል የሚሆኑበት መንገድ መዘጋጀት ይኖርበታል። ወጣቶች በራሳቸው የእድሜ ክልል ውስጥ የራሳቸውን ችግር ሲነጋገሩ ይበልጥ ግንዛቤ ይኖራቸዋል። ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ነው እስካሁን ድረስ የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጉባኤ ሲካሄድ የቆየው። አምስተኛው የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጉባኤም «ተደራሽነትና ጥራት፤ ምላሽ ሰጪ የጤና ስርዓት ለሁሉም አፍላ ወጣቶች» በሚል መሪ ቃል በቅርቡ መካሄዱ ይታወሳል።

ወጣት ቶፊቅ እስማኤል ሃኪም በጤና ሚኒስቴር የአፍላ ወጣቶችና ወጣቶች ጤና ካውንስል ፕሬዚዳንት ነው። እርሱ እንደሚለው ካወንስሉ እያከናወናቸው ከሚገኙ ተግባራት ውስጥ አንዱ በየዓመቱ በሚዘጋጀው የአፍላ ወጣቶችና ወጣቶች ጤና ጉባኤ ላይ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች እንዲሳተፉ በማድረግ በስነ ተዋልዶ ጤናና እነሱን በሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት እንዲያደርጉ መፍትሄ ሃሳብ እንዲጠቁሙ ማድረግ ነው። በዚህ ጉባኤ ባለፉት አራት ተከታታይ ዓመታት የኢትዮጵያ አፍላ ወጣቶችና ወጣቶች ጤና ጉዳይ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ፣ ምን እንደሚያስፈልግና ምን እንደሚያሳስብና በተለይ እንዴት ተደራሽ መሆን እንዳለበት ሲሰራ ቆይቷል።

ዘንድሮ ደግሞ ባለፉት አራት ዓመታት እነዚህን ከማሳካት አንፃር የተሄደበትን ርቀት በመገምገም በወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ስነ ተዋልዶ ጤና ጥራትን ለማካተት ታሳቢ ያደረገ ውይይት በጉባኤው ተካሂዷል። እስከዛሬ ድረስ በወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ዙሪያ ተደራሽነት ላይ በስፋት ሲሰራ ቆይቷል። ነገር ግን የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተደራሽነቱ ምን ያህል ጥራት እንደነበረው ቁጭ ብሎ መገምገምና ጥራትን ማካተት አስፈጓል። ለዚህም ነው የዘንድሮው ጉባኤ ትኩረቱን በስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ጥራት ላይ ትኩረቱን አድርጎ የተካሄደው። በስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ጥራት በሚፈለገው ልክ ላይኖር ይችላል። ስለዚህ ተጠያቂነትና ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ትልቁ ባለቤት አፍላ ወጣቱና ወጣቱ ነው።

በርካታ ወጣቶች ለጤናና ለተለያዩ ማሕበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሚሆኑት በግንዛቤ እጥረት ምክንያት ነው። ከዚህ አንፃር ካውንስሉ ሚሰራው ነገር ቢኖር በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ለወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ግንዛቤ መፍጠር ነው። ግንዛቤ ከመፍጠር ባለፈ ካውንስሉ ከስነ ተዋልዶ ጤና ጋር በተገናኘ አፍላ ወጣቶችና ወጣቶች አገልግሎት የሚያገኙበትን ቦታ ይጠቁማል።



ወጣት ቶፊቅ እስማኤል ሃኪም፤

**በነዚህ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ በርካታ ወጣቶች አሉ። ነገር ግን የስነ ተዋልዶ ጤናና ሌሎችም የጤና አገልግሎቶች በበቂ ሁኔታ እየተሰጣቸው አይደለም**

የስነ ተዋልዶ ጤና ችግር እንዳያጋጥማቸው አስቀድሞ የመከላከል ስራም ይሰራል። ችግሩን የሚከላከሉበትን ቦታዎች ከመጠቆም ባለፈ በምን አይነት መንገድ ችግሩን መከላከል እንደሚችሉም የሚያሳይበት ስርዓት አለው።

ወጣት ቶፊቅ እንደሚለው ወጣቶች የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርአቱ ጥራት ያስፈልገዋል። ይህን የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል ዘንድሮ በጤና ሚኒስቴር በኩል የተሞከሩ ስራዎች አሉ። ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ላማሻሻል ጥረት ተደርጓል። ሆኖም አሁንም የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራቱን ይበልጥ ማሻሻል ያስፈልጋል። ለአብነት በጤና ተቋማት የሚሰጡ የወጣቶች የጤና አገልግሎቶች አሉ። ነገር ግን አብዛኞዎቹ አገልግሎቶች የሚሰጡት ከሌሎች የጤና አገልግሎቶች ጋር ተደባልቀው ነው። በዚህ ምክንያት ወጣቶች ስለ ስነ ተዋልዶ ጤናና ስለሌሎችም ጤና ነክ ጉዳዮች የማማከር ፍላጎት ኖሯቸው በሃፍረት ምክንያት ወደ ጤና ተቋማት የማይሄዱበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህም ከአገልግሎት ጥራት አኳያ ያለውን ጉድለት ያሳያል።

በሌላ በኩል ደግሞ በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ፓርኮች እየበዙ መጥተዋል። በነዚህ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ በርካታ ወጣቶች አሉ። ነገር ግን የስነ ተዋልዶ ጤናና ሌሎችም የጤና አገልግሎቶች በበቂ ሁኔታ እየተሰጣቸው አይደለም። ከዚህ አንፃር ወጣቶቹ ባላቸው ግዜ ጤናቸውን እንዲያረጋግጡ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የጤና ማእከል ሊኖራቸው ይገባል። ይህ ባለመሆኑም ነው በርካታ ወጣት ሴቶች ላልተፈለገ እርግዝና የሚጋለጡት።

ልክ እንደ ጤናው አገልግሎት ዘርፍ ሁሉ የኢትዮጵያ የትምህርት ስርአትም አብሮ መሻሻል አለበት። በትምህርት ላይ ከታች ጀምሮ መሰራት አለበት። ስለዚህ ብዙ ነገሮችን ለማስተካከል ግዜው አሁን ነው። ዛሬ ላይ ያልተቀረፈ ችግር ነገ ትውልዱ ይቀርፈዋል ማለት አይቻለም። ፆታዊ ጥቃቶች እየተፈፀሙ ነው። በግጭት ምክንያት በርካታ ወጣቶች ተሰደዋል። በርካታ ወጣቶች በመጠለያ ካምፕ ውስጥ ነው የሚገኙት። በነዚህ አካባቢዎች ላይ የሚገኙ ወጣቶች በጤና የመጠበቅ መብታቸው ሊከበርላቸው ይገባል። ስለዚህ ዛሬ ላይ ጥራት ያለው ምላሽ ሰጪ የጤና ስርአት ሊገነባ ይገባል። ሃይማኖት ተቋማት ላይ ያለው የጤና ስርአትም እንዲጠበቅ ይፈለጋል።

ወጣት ቶፊቅ እንደሚያብራራው በግጭቶች ምክንያት ተፈናቅለው በመጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች የስነ ተዋልዶና ሌሎችንም የጤና አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ካውንስሉ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ያቀርባል፤ አቅርቧልም። ከሁሉም በላይ ካውንስሉ ሰላም እንዲመጣ ይፈልጋል። ሰላም ሲመጣ የሚፈለገው የጤና አገልግሎት ለወጣቱ እንደሚደርስ ያምናል። ከዛ ውጪ ግን ግጭት በተፈጠረባቸው አካባቢዎች ላይ ያሉ አካላት ቆም ብለው ደጋግመው ሊያስቡ ይገባል። ትውልድ ነው የሚያቀነጭሩት። ጤና ከፖለቲካ ነፃ የሆነ ዘርፍ እንደመሆኑ ማንኛውም ሰው ጤናውን የመጠበቅ መብት አለውና ይህ ነገር እንዲደረግ ካውንስሉ ድምፅ ይሆናል።

እንደዚህ አይነት ቦታዎች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲጎበኙና ምላሽ እንዲሰጣቸው፣ ሕክምና ቁሳቁሶች በፍጥነት ቦታው ላይ እንዲደርሱ፣ ለቀውስ የተጋለጡ ወጣቶች ባሉበት ቦታ ላይ በቶሎ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት የሚያገኙበትን ሁኔታ የማመቻቸትና የመወትወት ስራ ይሰራል። ተደራሽነት ሲባል ግን ጥራቱን ጠብቆ ነው። ምንም አይነት የጤና አገልግሎት የለም ማለት የለበትም። አገልግሎቱ የተሟላ ሊሆን ይገባል።

የአፍላ ወጣቶችና ወጣቶች ጤና ካውንስል በጤና ሚኒስቴር ስር ያለ ቢሆንም በኢትዮጵያ ወስጥ ያሉ ማንኛቸውም በአፍላ ወጣቶችና ወጣቶች ዙሪያ ስራ የሚሰሩ አካላት ሁሉ ከካውንስሉ ጋር ይሰራሉ፤ እንዲሰሩም ሕጉ ያስገድዳቸዋል። ካውንስሉም ከነዚህ አካላት ጋር ይሰራል። የኢትዮጵያ አፍላ ወጣቶችና ወጣቶች ካውንስል አባል የሚባሉትም በኢትዮጵያ የሚገኙት ሁሉም የአፍላ ወጣቶችና ወጣቶችን ያካተተ ነው። በአምስተኛው የአፍላ ወጣቶችና ወጣቶች ጉባኤ ላይም ከየክልሉ ከፕሬዚዳንት እስከ ምክትል ፕሬዚዳንትና ፀሃፊ ድረስ ሶስት ሶስት ወጣቶች እንዲሳተፉ ተደርጓል። በጥቅሉ ከ200 በላይ የሚሆኑ ወጣቶች ተሳትፈዋል።

ወጣት ቶፊቅ እንደሚለው በኢትዮጵያ ከ3 ሺ በላይ የወጣት ስብእና መገንቢያ ማእከላት አሉ። የካውንስሉ አጋር አካላት የሴቶችና ማኅበራዊ ሚኒስቴርና ትምህርት ሚኒስቴር እንደመሆናቸው እነዚህ አካላት በወጣቶች ዙሪያ ባለቤት ሆነው ይሰራሉ። በነዚህ 3 ሺ በላይ በሚሆኑ የወጣት ስብእና መገንቢያ ማእከላት ሁሉም የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ይሰጣሉ። አገልግሎቶቹ ጥራት ያላቸውና የተሟሉ ናቸው የሚለው ግን ቁጭ ብሎ መፈተሽ ያለበት ጉዳይ ነው።

የዛሬ ዓመት በተሰራ ጥናት እነዚህ 3 ሺ የወጣት ስብእና መገንቢያ ማእከላት ጥራት እንደሌላቸው ሪፖርት ቀርቧል። ጥራት እንደሚያስፈልጋቸው፣ አስፈላጊ መሰረተ ልማቶች ሊሟሉላቸው እንደሚገባ በጥናቱ ተጠቁሟል። እንደዚህ አይነት ጉድለት ያለባቸው የወጣት ስብእና መገንቢያ ማእከላት እንዲዘጉና አቻ ተቋማት እንዲከፈቱ ተደርጓል። በ2017 ዓ.ም ደግሞ እነዚህ የወጣት ስብእና መገንቢያ ተቋማት በአገልግሎት ጥራትና ተደራሽነት በ10 ከመቶ እንዲያድጉ እየተሰራ ይገኛል።

በሌላ በኩል ደግሞ በሁሉም ጤና ተቋማት ላይ የወጣት ጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት እንዲገነቡ መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ስራው ተግባራዊ ይሆናል። አብዛኞዎቹ የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችም በነፃና በበጎ ፍቃድ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። ወጣቶች በጤና ተቋትም ሄደው የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ሲያገኙ ክፍያ አይጠየቁም። ስለዚህ ባለፉት አራት ዓመታት በስነ ተዋልዶ ጤና ተደራሽነት ላይ ሰፊ ስራ ሲሰራ ቆይቷል። አሁን ደግሞ ተደራሽነቱን ከማስፋት በዘለለ ምላሽ የመስጠት ስራው እንዳለ ሆኖ በሁሉም የጤና ስርአት የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ላይ ይበልጥ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የገጠሩን ድባብ በከተማ ማሳየት ያስቻለው የጉራጌባህል ማእከል

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በዛሬው የስኬት አምዳችን አዲሱ ዓመት ከሚያስከትላቸው ደማቅ በዓላት አንዱ በሆነው የመስቀል በዓል ማግስት ላይ ተናኝተናል። በዓሉ በሃይማኖታዊና ባሕላዊ ስርዓት የሚከበር ሲሆን፣ በኃይማኖታዊ ይዘቱ መስከረም 16 ደመራ ተደምሮ መስከረም 17 በመላ ኢትዮጵያ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በደማቅ ስነስርዓት ይከበራል።

በተለያዩ ማሕበረሰቦች ዘንድ ደግሞ ከበዓሉ አስቀድሞ ካሉት ቀናት አንስቶ በተለያዩ ዝግጅቶች የሚከበር ሲሆን፣ በተለይ በአዳዲሶቹ የማእከላዊ ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ክልል እንዲሁም በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልሎች የተለያዩ አካባቢዎች በድምቀት ከሚከበሩ በዓላት መካከል አንደኛው ነው።

የዕለቱ የስኬት እንግዳችንም የመስቀል በዓልን በድምቀት ከሚያከብረው ከጉራጌ ብሔረሰብ የተገኘች ናት። ጠንካራ የሥራ ባሕል ካለውና ባሕሉን ጠብቆ በማቆየት ከሚታወቀውና መስቀል ሲነሳ ሁሌም አብሮ ስሙ ከሚነሳው የጉራጌ ብሄረሰብ የተገኘችው እንግዳችን ወይዘሮ ዘነበች ታደሰ ትባላለች። ወይዘሮ ዘነበች የወኸምያ የጉራጌ ባህል ማዕከል መስራችና ባለቤት ናት።

ወይዘሮ ዘነበች እንዳሉት፤ ወኸምያ የጉራጌ ባህል ማዕከል ትክክለኛው የጉራጌ ባህል የሚታይበትና የጉራጌ ባህላዊ ምግብ በተለይም ክትፎና ቆጮ በሙሉ ግርማ ሞገስ የሚገኝበት ቤት ነው። ማዕከሉ የተቋቋመበት ዋናው ምክንያት ከተማ ውስጥ ለሚኖሩና ትክክለኛውን የጉራጌ ባህላዊ ምግብ ለሚፈልጉ ደንበኞች ተደራሽ ለማድረግ ታስቦ ነው።

ሁለት አስርት ዓመታት እድሜን ያስቆጠረው ይህ የባህል ማዕከል ትክክለኛ ከሆነው ከጉራጌ ባህላዊ ምግብ ባለፈ ገጠር ውስጥ ያሉትን ባህላዊ ቁሳቁስ ጭምር ፍንትው አድርጎ ያሳያል። ይህም የገጠሩን ድባብ በማምጣት ስሜት የሚያጭር ሲሆን፤ ይህን ስሜት ማምጣት የወኸምያ የጉራጌ ባህል ማዕከል ዋና ዓላማው እንደሆነም ወይዘሮ ዘነበች አጫውታናለች።

በጉራጌ ዞን በእዣ ወረዳ ልዩ ስሙ ጉየና የሶ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ድጋግ በተባለ አካባቢ ተወልዳ ያደገችው ወይዘሮ ዘነበች፤ የመጀመሪያ ደረጃና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን እስከ ዘጠነኛ ክፍል በትውልድ አካባቢዋ ተምራለች። ያኔ ታድያ በመኖሪያ አቅራቢያ ትምህርት ቤት ማግኘት እንደዛሬ ቀላል አልነበረምና ፊደል ለመቁጠር እንኳ ከፍተኛ ውጣ ውረድ ይገጥማት እንደነበር ታስታውሳለች። የበረታ ጥረት ስኬትን ያጎናጽፋልና ብርታት ጥንካሬዋን አሰባስባ ትምህርቷን ተከታትላለች።

ታታሪና ሥራ ወዳድ ከሆነው የጉራጌ ማህበረሰብ የተገኘችው ወይዘሮ ዘነበች፤ ፊደል ለመቁጠር ገና በለጋ ዕድሜዋ ረጅም ርቀት በእግሯ ተመላልሳለች። ስንቅ በመያዝ በሳምንት አንድ ጊዜ ቤተሰብ ጋ በመመለስ እስከ ዘጠነኛ ክፍል መማሯንም ትገልጻለች።

ለችግር እጅ ያልሰጠችው ወይዘሮ ዘነበች፣ በወቅቱ መማር እንዲሁም የትምህርት ቁሳቁስ ማሟላት እንድትችል ከትምህርቷ ጎን ለጎን ትናንሽ የሚባሉ ሥራዎችንም ሰርታለች። ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ እንደ ደብተር እስኪሪብቶና እርሳስ እንዲሁም የገብስ ቆሎ ያሉትን ትምህርት ቤት አካባቢ ትሸጥም ነበር።

ይህም ህይወቷ የንግድ ሥራን ‹‹ሀ›› ብላ እንድትጀምር በሩን ከፍቶላታል፡ ተማሪዎች በእረፍት ጊዜያቸው ሲጫወቱ እሷ ግን ጨዋታ አታውቅም ቆሎ ትሸጥ ነበር። እንደ ልጅ ጨዋታ ሳያምራት ቅዳሜና እሁድ ወደ ከተማ በመሄድ ለዚህ ንግዷ የሚያስፈልጉትን በመግዛት የንግድ ሥራዋን አቀላጥፋለች።

በዚህ ጊዜ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ስትከታተል የነበረችው ወይዘሮ ዘነበች፤ በሳምንት አንድ ጊዜ ከቤተሰብ ስንቅ ይዞ ተመላልሶ መማር እየከበዳት ሲመጣ ወደ ከተማ መውጣትን ምርጫዋ አድርጋ አዲስ አበባ አቅንታለች።

ቀን እየሰራች ማታ መማር የምትችልበት ምቹ ሁኔታ መኖሩን በመረዳት አዲስ አበባ የገባችው ወይዘሮ ዘነበች፤ ጊዜያዊ ማረፊያዋን ዘመድ ቤት በማድረግ የአስረኛ ክፍል ትምህርቷን በማታው ክፍለጊዜ ያደገችበትን የንግድ ሥራ ደግሞ በቀኑ ክፍለጊዜ ቀጠለች።

በወቅቱ ቅዳሜና እሁድ ከአዲስ አበባ ወደ ድሬዳዋ በመጓዝ ድሬዳዋ የሌለውን ከአዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ የሌለውን ደግሞ ከድሬዳዋ በማምጣት ነግዳለች። ለአብነትም ድሬዳዋ ላይ ሲጋራ ውድ በመሆኑ ከአዲስ አበባ ትወስዳለች። በምትኩ አልባሳት ከድሬደዋ በማምጣት



ወይዘሮ ዘነበች ታደሰ

ከትምህርት በኋላ እያዞረች ትሸጥ ነበር።

በጠንካራ የሥራ ባህል ያደገችው ወይዘሮ ዘነበች፤ ከድሬዳዋ አዲስ አበባ ተመላልሶ የመስራቱ ሁኔታ ከበድ እያላት ሲመጣ ደግሞ ከተማ ውስጥ ተረጋግታ መስራትን ምርጫዋ በማድረግ በተለያዩ ምግብ ቤቶች ሰርታለች። ሆቴሎችን እንዲሁም የግለሰብ ቤቶችን በመከራየት ምግብ በመስራት ውጤትና ስኬት ማስመዝገብ ችላለች።

‹‹ሰውን ሰው ያደረገው ዕቁብ ነው፤ ዕቁብና ዕድር የጀመረው ጉራጌ ነው።›› እየተባለ በጨዋታ በጨዋታ እንደሚነሳው ሁሉ እኔም ዕቁብ ሰብስቤ አራት ኪሎ አካባቢ የመጀመሪያውን ምግብ ቤት ከፈትኩ›› የምትለው ወይዘሮ ዘነበች፤ በወቅቱ የጉራጌ ክትፎን ጨምሮ የተለያዩ ባህላዊ ምግቦችን ታዘጋጅ እንደነበርም ነው ያስታወሰችው።

የምግብ ሥራን ከውስጥ በመነጨ ተነሳሽነት በመስራት ሥራዋን ማሳደግ ችላለች። ባህሏን አክባሪ እንደሆነች የምትናገረው ወይዘሮ ዘነበች፤ እያደገ በመጣው የምግብ ሥራ ውስጥ የጉራጌ ባህላዊ ምግብን በጥራት በማዘጋጀት ታስተዋውቅም ነበር።

እያደገና እየሰፋ የመጣው የምግብ ሥራም ዛሬ ላይ ስመ ጥር ወደሆነው ወኸምያ የጉራጌ ባህል ማዕከል ማደግ ችሏል። ‹‹ጥበብ አብሮ ይወለዳል›› እንደሚባለው የጉራጌ ባህላዊ ምግብን በባህል ማዕከል ለማሳየት ስትነሳ በሙሉ ፍላጎት ላይ ተመስርታ ነበር።

ኢትዮጵያዊ የሆኑ ባህሎች ሲዘነጉና ዘመን አመጣሽ በሆኑ ባህሎች ሲተኩ ያስተዋለችው ወይዘሮ ዘነበች፤ የራሷን ድርሻ በመወጣት ኢትዮጵያዊ የሆኑ ባህሎችን ለማቆየት አንድ እርምጃ እንደተጓዘች ትናገራለች።

እሷ እንዳለችው፤ በጉራጌ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የአመጋገብ፣ የአለባበስና አጠቃላይ የአኗኗር ዘይቤዎች ከዕለት ወደ ዕለት ሲደበዝዙ ማየቷ ያስቆጫታል። ተቆጭታ ብቻም አልቀረችም፤ ባህሉ መናቅና መረሳት የሌለበት በመሆኑ ማህበረሰቡ ባህሉን በደንብ እንዲረዳውና እንዲይዘው ሌላውም እንዲያውቀውና እንዲከተል በሚል ባህላዊ ምግቡን ከመመገቢያ ቁሳቁሱና አጠቃላይ የገጠሩን ድባብ ጭምር ለከተሜው ማቅረብ ችላለች።

እንግዳ ሆነው ወደ ጉራጌ አገር የሄዱ ሰዎች አገር ቤት የሚበሉት ክትፎና አዲስ አበባ አልያም ሌሎች ከተሞች ላይ የሚበሉት ክትፎ ተመሳሳይ እንዳልሆነ ሲናገሩ ብዙ ጊዜ አስተውያለሁ የምትለው ወይዘሮ ዘነበች፤ ባህሉን ከማስተዋወቅ ባለፈ ትክክለኛውን የጉራጌ ባህላዊ ምግብ ከሙሉ ዝግጅቱ ጋር ለማቅረብ ወስና የብሄረሰቡ መገለጫ የሆነውን ክትፎና ቆጮ ብቻ በሆቴል ደረጃ አዘጋጅታ ሁሉም ሰው በቅርበት ማግኘት እንዲችል አድርጋለች።

ፒያሳ ጣይቱ ሆቴል አካባቢ የከፈተችውን የመጀመሪያውን ክትፎ ቤት/ የባህል ማእከል/ ሥራዋ ተቀባይነት እያገኘ ሲሄድም 22 አካባቢ ሰፋ ባለ ቦታ ላይ የጉራጌ ማህበረሰብ ባህላዊ ምግብ የሆነውን ክትፎ ከእነቁሳቁሱ ተደራሽ ማድረግ ችላለች። ፒያሳ ላይ የነበረው ወኸምያ የጉራጌ ባህል ማዕከል በልማት መፍረሱን ጠቅሳ፤ ሰፋ ባለ ቦታ ላይ ከቤት አሰራሩ ጀምሮ የጉራጌ ማህበረሰብ የሚጠቀምባቸውን መገልገያ ቁሳቁስ በስፋት የያዘው ወኸምያ ክትፎ 22 አካባቢ በሥራ ላይ እንደሚገኝ ተናግራለች።

ባህልና ወጉን ጠብቆ የተቋቋመው ወኸምያ የጉራጌ ባህል ማዕከል በዋናነት የጉራጌ ባህላዊ ምግብ የሆነውን ክትፎ፣ ቆጮ፣ ጎመንና አይብ በአይነት በአይነቱ እያቀረበ ይገኛል። በአቀራረቡና በሚጠቀማቸው ባህላዊ ቁሳቁስ አድናቆትን አትርፏል። ለኢትዮጵያውያን ከሚሰጠው አገልግሎት አልፎም የቱሪስቶች መዳረሻ መሆን ችሏል። ብዙዎች ከምግቡ ባለፈ በውስጡ አጭቆ በያዛቸው የጉራጌ ባህል ቁሳቁስ ይደመማሉ። ከመቀመጫዎቹ ጀምሮ እያንዳንዱ ቁሳቁስ ባህሉን የሚወክልና አቀራረቡም ጭምር የአገር ቤት ድባብ ያለው በመሆኑ በርካቶችን የሚያዝናና የሚያስደስት ነው።

መስቀል በጉራጌ በታላቅ ድምቀት የሚከበርና ከዓመት ዓመት በናፍቆትና በጉጉት የሚጠበቅ በዓል እንደሆነ ያነሳችው ወይዘሮ ዘነበች፤ ወኸምያ ማለት ዋናው መስቀል የሚከበርበት ዕለት መሆኑን ገልጻለች። ወደ ወኸምያ የጉራጌ ባህል ማዕከል የሚመጣ ደንበኛም በዋናው የመስቀል ቀን እንደመጣ ተቆጥሮ ደስተኛ ሆኖ በልቶና ጠጥቶ እንዲጠግብ በማሰብ ነው ለማእከሉ ስያሜው የተሰጠው ትላለች። አገልግሎት አሰጣጡም እንደ ሆቴል ሳይሆን ደንበኛው በቤቱ እንደሚስተናገድ ሁሉ ክትፎው፣ ቆጮው በአይነት በአይነቱ፣ አይብ ጎመኑና ቅቤው ጭምር ፊትለፊቱ እየመጣ ይጨመራል። ይህ ደግሞ ደንበኛው እጅግ እንዲደሰት ያደርጋል በማለት ታብራራለች።

መስቀል በጉራጌ የሚከበረው ቀደም ብሎ ከመስከረም 14 ጀምሮ ለ15 ቀናት ሲሆን፤ በየዕለቱ የሚከናወኑ ተግባሮችና ምግቦችም እንዲሁ የተለያዩ ናቸው። ለአብነትም የመጀመሪያው መስቀል ከዋናውና እርድ ከሚከናወንበት አንድ ቀን /ጾም ቀን ከዋለ ደግሞ ሁለት ቀን/ ቀድሞ የሚከበረው የሴቶች መስቀል ነው። በዕለቱ ጎመን፣ አይብና ቆጮ ተዘጋጅቶ ይበላል። የመጀመሪያው መስቀል ለሴቶች የተሰጠበት ዋናው ምክንያትም ሴቶች በመስቀል ዝግጅት ካለባቸው ትልቅ ኃላፊነት የተነሳ እንደሆነ ይነገራል።

ዋናው መስቀል ወኸምያ የሚባል ሲሆን፤ በዕለቱ እርድ የሚከናወንበት፣ ያለው የሌለው ሳይል ሁሉም ክትፎ የሚበላበት፣ አዲስ ልብስ የሚለበስበት፣ የተጣላ የሚታረቅበት፣ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎችና በውጭ አገራት ጭምር የነበሩ የአካባቢው ተወላጆች የሚሰበሰቡበትና ወደ ቤተሰብ የሚገቡበት፣ ወጣቶች የሚተጫጩበትና ትዳር የሚመሰርቱበት እንዲሁም ያለው ለሌለው አካፍሎ ሁሉም ሰው በጋራ እኩል የሚደሰትበት አንጋፋው የመስቀል ዕለት መስከረም 15 ነው።

ወኸምያ የጉራጌ ባህል ማዕከልም ስያሜውን ያገኘው ከዚሁ መነሻ እንደሆነና እንደስያሜው ሁሉ ለደንበኞቹ ትልቅ እርካታ ያለው አገልግሎት እንዲሰጥ ታሳቢ ተደርጎ ነው። በማለት ያስረዳችው ወይዘሮ ዘነበች፤ ወኸምያ የጉራጌ ባህል ማዕከል ወደፊትም አገልግሎት አሰጣጡን ማራኪ በሆነ መንገድ እንደሚቀጥል ገልጻለች።

‹‹የመስቀል በአል ልዩ ስሜት ይሰጠኛል››። የምትለው ወይዘሮ ዘነበች፤ በየዓመቱ ወደ አገር ቤት በመግባት በዓሉን ታከብራለች። ከበዓል አከባባሩ ባለፈ ከልጅነቷ ጀምሮ ያሳለፈችውን ጊዜ በማስታወስ ከእኩዮቿ ጋር የምትጨፍረው ጭፈራ፣ መብላት መጠጣቱ፣ ጨዋታና ሳቁ ሁሉ አሁን አሁን እስኪመስላት ሀሴት ታደርጋለች። ከመብላት መጠጣቱና ጫወታው ባለፈም ልጆች የሌላቸው አቅመ ደካማ እናቶችን በማገዝ መስቀልን ደስ ብሏቸው እንዲያሳልፉ በማድረግ ደስታን ታተርፋለች። ይህም መስቀል ሲመጣ ከሚያስደስቷት ጉዳዮች አንዱ እንደሆነ አጫውታናለች።

‹‹የጉራጌ ብሄረሰብ በመስራት ብቻ ሳይሆን፤ በምርቃትም ያምናል›› የምትለው ወይዘሮ ዘነበች፤ መስቀል ሲደርስ ሁሉም ከያለበት ተሰባስቦ ወደ አገር ቤት የሚገባው በዋነኛነት ምርቃት በመፈለግ ሙሉ ዕምነት እንደሆነ ገልጻለች። እሷ እንዳለችው ምርቃት የአምላክ ፈቃድ ማስፈጸሚያ ቃል እንደመሆኑ በርካቶች የልባቸውን መልካም ምኞት በምርቃት እንደሚያገኙ በማመን ምርቃት ለመቀበል የቻሉትን ሁሉ ያደርጋሉ።

የጉራጌ አንድና አንድ በዓሉ መስቀል እንደሆነ ያነሳችው ወይዘሮ ዘነበች፤ ተወላጁም ዓመት ሙሉ የሰራውን ለመስቀል የሚያውለው ዋነኛ በዓሉ በመሆኑ አስቀድሞ ተቀማጭ ያደርጋል። በጉራጌ ማህበረሰብ ከመስቀል መቅረት የሞት ያህል በመሆኑ ሁሉም የጉራጌ ተወላጅ መስቀልን አገር ቤት ያከብራል። መስቀልን አክብሮ ወደመጣበት በተመለሰ ጊዜም ቀጣዩን መስቀል በመናፈቅ ገንዘብ ያጠራቅማል ይቆጥባል። ይህ ደግሞ የጉራጌ ተወላጅን ልዩ የሚያደርገውና በእጅጉ የሚያስደስተው ነው።

ከትምህርት ቤት ጀምራ የንግድ ሥራን የተለማመደችው ታታሪዋ ወይዘሮ ዘነበች፤ በምግብ ሥራ ለበርካቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር ዛሬ ላይ እራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ በር የከፈተች ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅትም 45 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥራለች።

ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድም እንዲሁ የተለያዩ ድጋፎችን የምታደርገው ወይዘሮ ዘነበች፤ በየዓመቱ ለመስቀል ስትገባ ከምታግዛቸው ሰዎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ ለሚገኙ የተለያዩ አካላት ከምታደርገው ድጋፍ በተጨማሪ በትውልድ አካባቢዋ መንገድ አሰርታለች። ትምህርት ቤትም ገንብታለች። ትምህርት ቤቱ እስከ ስምንተኛ ክፍል ሲሆን፤ እሷ በልጅነት ዕድሜዋ ያሳለፈችውን እንግልት አሁን ያለው ትውልድ እንዳይደግመውና በቀላሉ ፊደል መቁጠር እንዲችልና ርቆ እንዳይሄድ አድርጋለች። ከትምህርት ቤቱ በተጨማሪ የመምህራን መኖሪያ ቤት ጭምር ገንብታ ለመምህራን አስረክባለች።

በመጨረሻም በምርቃት በጉራጌ ማህበረሰብ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው እንደመሆኑ በምርቃት የተሰናበተችን ወይዘሮ ዘነበች፤ 2017 ዓ.ም ለአገራችን ሰላም፣ ፍቅርና አንድነትን ይዞ እንዲመጣ፤ በዓሉም የሰላምና የፍቅር በዓል ይሁን በማለት መልካም ምኞቷን ገልጻለች።

# ተናጋሪው ዶሴ

# የመጥፎ ጉጉት መዘዝ

ምሕረት ሞገስ



ወሩ ልክ እንደአሁኑ መስከረም ነው። እንደተለመደው ሠፋ ሽሪፍም እንደሁሉም ወላጆች የመስከረም ወር ወጪ አስጨንቆታል። ሶስት ልጆች ያለው በመሆኑ የእነርሱን ፍላጎት ለማሟላት ቀን እና ሌሊት ይሠራል። መስከረም 2 ገና የበዓሉ ድባብ አላለፈም። ሰፋ ገበያው ሞቅ ያለ በመሆኑ የበዓሉን ምሽት ቤት ማሳለፍ ትቶ፤ እየሠራ ለማደር ወስኗል። ገንዘብ ማግኘትን አጥብቆ በመሻቱ፤ እንቅልፍ አላታለለውም። ሌሊት ስምንት ሰዓት በቦሌ ጎዳናዎች ላይ ቀስ እያለ በመንዳት ተሳፋሪ ይፈልጋል።

**የሠፋ የኋላ ታሪክ**

ሠፋ ሽሪፍ የተወለደው በጉራጌ ዞን ጉንችሬ ወረዳ ጋርባዶ ቀበሌ ነው። ከእናቱ ወዱ ያኺ እና ከሽሪፍ ሽብሩ በ1978 ዓ.ም የተወለደው ሠፋ፤ ከአካባቢው ልጆች በተሻለ መልኩ ጋርባዶ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመማር ችሏል። ነገር ግን ምንም እንኳ እናት እና አባቱ እርሱን እዛው ቅርባቸው ለማስተማር ቢፈልጉም፤ ሠፋ ገጠር ቆይቶ ለመማር ፈቃደኛ አልሆነም። በትምህርቱም ብዙ አልዘለቀም። 5ኛ ክፍል ሲደርስ ትምህርቱን አቋርጦ አዲስ አበባ ገባ። ቀን መኪና እያጠበ የሚያሸከመው ሲያገኝ ተሸካሚ ሆኖ እያገለገለ ሕይወቱን መግፋት ጀመረ።

ብርቱ ሠፋ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ መንጃ ፍቃድ አውጥቶ አሽከርካሪ ሆነ። ተቀጥሮ መስራት ሲጀምር ትዳር መሠረተ። በየዓመቱ ልጆች እየወለደ የሶስት ልጆች አባት ለመሆን በቃ። አሮጌ መኪና ገዝቶ መሥራት ቢጀምርም፤ ሊያዋጣው አልቻለም። እያሽከረከረ የሚያገኘውን ገቢ መልሶ ለመኪናው የሚወጣው ወጪ ይወስድበታል።

የላዳ ሹፌሩ ሠፋ ሽሪፍ አሁን 38 ዓመቱ ነው። ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት ሲኖር፤ ታዋቂነትን ያተረፈው በታክሲ አሽከርካሪነት ብቻ ነው። ከወጣትነቱ ጀምሮ ጎልማሳ እስኪሆን ድረስ ስራው ሹፍርና ነው። ታግሎ የደረሰበት ትልቅ ደረጃ በመሆኑ ሹፌርነቱን አጥብቆ ይወደዋል። በሹፌርነት ዘመኑ ለወትሮ ለቤተሰቡ እጁ አያጥረውም ነበር። የሜትር ታክሲ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ግን ገቢው እየተመናመነ የላዳ ደንበኛ ቁጥር እየቀነሰ መጣ።

ከቀን ወደ ቀን ከገበያው መቀነስ ባሻገር የላዳዋ በየጊዜው መበላሸት፤ ሠፋ ከነቤተሰቡ ችግር ላይ እንዲወድቅ አስገደደው። ይህን ተከትሎ ሹፌር ሆኖ በመስራት ቤተሰቡን ማስተዳደር ቢያቅተውም፤ ሥራው ቀን እና ለሊት እያካሔደ በየሳምንቱ እየተበላሸች የምትረብሸውን ላዳውን እያባበለ ከኑሮ ጋር ትግሉን ቀጠለ። የጎደለበትን እየሞላ ለመሻገር ቢሞክርም፤ አንድ ቀን ግን ለችግር ማለፊያ ብሎ የወሰደው እርምጃ ከባድ ጥፋት ሆኖ የእርሱን እና የቤተሰቡን ሕይወት በእጅጉ አበላሸው።

ሠፋ ቦሌ እና ሃያ ሁለት አካባቢ የሚዝናኑ ጠጪዎች ስለማይጠፉ እነዛ አካባቢ ለሊት ለሊት መሥራት ዋነኛ ገቢ የማግኛ ምንጩ አድርጎታል። ዕድል ሲቀናው ጠጪዎቹ ከመሳፈሪያ ክፍያ አልፈው፤ ጉርሻ እያሉ የሚሰጡት ገንዘብ ብዙም ባይሆን ኑሮውን ይደጉምለታል። እንደተለመደው መስከረም 2 ቀን 2016 ዓ.ም ከለሊቱ ስምንት ሰዓት አካባቢ ቦሌ ጉምሩክ ካርጎ አጠገብ ቆሞ ተሳፋሪ ሲጠብቅ፤ ብርሃነ ተ/ሚካኤልን አገኘው።

**የተሳፋሪው ክፉ አጋጣሚ**

ብርሃነ ተ/ሚካኤል የዋህ ሰው አማኝ ገራገር የሚባል ዓይነት ነው። መዝናናት አጥብቆ ይወዳል። ስስት አያውቅም፤ ያለውን አካፍሎ ያበላል። ቤተሰቡን እና ጓደኞቹን ብቻ ሳይሆን የተዋወቀውን ሁሉ ለማስደሰት ይሞክራል። ብርሃነ እንደተለመደው እኩለ ለሊት እስኪያልፍ ሲዝናና እና ሲጠጣ ቆይቶ ወደ ቤቱ ለመሔድ አሰበ። በኪሱ ምንም ዓይነት ገንዘብ አልነበረውም። ሃያ ሁለት አዲሱ አስፓልት ዳሽን ባንክ አካባቢ ቆሞ ቤቱ ገርጂ ጃክሮስ አደባባይ የሚያደርሰውን መኪና ሲፈልግ፤ ሠፋ ሽሪፍ አሮጌ ታክሲውን እያሽከረከረ አጠገቡ ቆመ።

ከሃያ ሁለት አካባቢ ብርሃነ ቤት ጎሮ ጃክሮስ አደባባይ ለመድረስ ሠፋ 300 ብር ጠየቀ። ብርሃነ አልተከራከረም። ‹‹አድርሰኝ ገንዘቡን ግን የምሰጥህ ከቤት አውጥቼ ነው›› አለው። ሠፋ በሃሳቡ ተስማማ፤ አብረው እየተጨዋወቱ ጉዞ ጀመሩ። ብርሃነ አሽከርካሪው ሠፋ ተመችቶታል። የብርሃነ ቤት ሲደርሱ፤ ብርሃነ ከመኪና ወርዶ ከተነጋገሩበት 300 ብር በተጨማሪ 100 ብር ጉርሻ ለሠፋ ሰጠው። ብርሃነ ‹‹ሌላ ቀንም እንድጠራህ ስልክ ቁጥርህን ስጠኝ።›› አለው።

ሠፋ ስልክ ቁጥሩን መናገር ጀመረ። ብርሃነ ግን ሞቅ ስላለው ቁጥሩን በትክክል መመዝገብ አቃተው። ሠፋ ደጋግሞ ነገረው። ሞከረ፤ አልሆነለትም። ለሠፋ ‹‹ራስህ መዝግብ›› ብሎ ሰጠው። ብርሃነ ለሠፋ ተንቀሳቃሽ ስልኩን የሰጠው ሙሉ ለሙሉ አምኖት ነበር። ስልኩን ከመስጠት አልፎ፤ በሹፌሩ በኩል መኪናውን ተደግፎ ግማሽ ሰውነቱን ወደ መኪናው ውስጥ አስገብቶ ነበር። ሠፋ ስልኩን ሲያየው ሳምሰንግ ኤ ዜሮ ስሪ ነው። ውድ ሊሆን እንደሚችል አሰበ። በዛው ቅፅበት ቢሸጠው ምን ያህል ሊያገኝ እንደሚችል እና ዕዳዎቹን እንዴት እንደሚከፍል አስቦ እጅጉን ጓጓ። ሞባይሉን ለመውሰድ ብሎ መኪናውን አስነስቶ አበረረ።

ሠፋ ስልኩን ለመውሰድ ብሎ በኃይል መንጭቆ መኪናውን ሲያስነሳ፤ ራሱን ጥሎ ሙሉ ለሙሉ መኪናውን ተደግፎ ከፊል ሰውነቱ መኪናው ውስጥ ሆኖ የቆመው ብርሃነ፤ በቤቱ በር ፊት ለፊት በማጅራቱ ኮብልስቶን ላይ ወደቀ። ሰፋ መኪናውን አላቆመም። ብርሃነ በዛች መጥፎ አጋጣሚ ኮብልስቶን ላይ በመውደቁ የራስ ቅሉ፤ ደረቱ እና ሆዱ ላይ በደረሰበት ጉዳት ላይመለስ እስከ ወዲያኛው አሸለበ።

**የደም ጥሪ**

አሽከርካሪው ሠፋ ሽሪፍ የሰረቀውን ስልክ ይዞ ቤቱ ገባ። ሠፋ ብርሃነ መሞቱን አላወቀም። ስልኩን በመስረቁ በምንም መልኩ እያዛለሁ ብሎ አላሰበም። ከቀናት በኋላ ወጥቶ የስልኩን ዋጋ አጣራ። አዲሱ ስልክ 14 ሺህ ብር መሆኑን አወቀ። የሚሸጠው ስልክ እንዳለው በመንገር፤ ዋጋው 7ሺህ 500 ብር ነው ሲል አስተዋወቀ። ገዢ መኖሩ ተነግሮት 22 አካባቢ አቃቤ ሕግ ቢሮ ድረስ ሄዶ በመደራደር ስልኩን ሊሸጥ ሲል በቁጥጥር ስር ዋለ።

ሠፋን የያዘው የፖሊስ ምርመራ ቡድን ሠፋ የእምነት ክህደት ቃሉን እንዲሰጥ አዘዘው። ሠፋ ስልኩን የት እና በምን መልክ እንዳገኘው ተናገረ። የፖሊስ የምርመራ ቡድኑ አቶ ብርሃነ በደረሰበት ጉዳት መሞቱን ለሠፋ ነገረ። ሠፋ በበኩሉ ድርጊቱን እንደፈፀመ አምኖ በፀፀት የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጠ።

**የፖሊስ ምርመራ**

የፖሊስ ምርመራ ቡድኑ ባካሔደው ብርቱ ጥረት፤ ብዙም ሳይቆይ ገርጂ ጃክሮስ አካባቢ ለተፈፀመው የውንብድና እና የግድያ ወንጀል መረጃ ብቻ ሳይሆን በቂ ማስረጃ አገኘ። ድርጊቱን የፈፀመውን መንጀለኛ ከማግኘት በተጨማሪ 15 የሠው ምስክር፣ ከቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የአስክሬን የምርመራ ውጤት የተገኘውን ማለትም ሟች ብርሃነ ተ/ሚካኤል ሕይወቱ ያለፈው ጭንቅላቱ፣ ደረቱ እና ሆዱ ላይ በደረሰበት ከባድ ጉዳት ምክንያት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቀረበ። የሟች አስክሬን ፎቶ እና ተከሳሽ ሠፋ ድርጊቱን በፈፀመበት ጊዜ የነበረውን ሁኔታ የሚያሳይ ፎቶ አደራጅቶ አቃቤ ሕግ ክስ እንደሚሠርት አቀረበ።

**የአቃቤ ሕግ**

የአቃቤ ሕግ በበኩሉ ከፖሊስ የቀረበለትን የክስ ማስረጃ አጣርቶ እና አደራጅቶ ተጠርጣሪ ሠፋ ሽሪፍ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 540ን ተላልፎ ተገኝቷል ሲል የወንጀሉን መነሻ፣ መረጃ እና ማስረጃውን አደራጅቶ ለፍርድ ቤት አቀረበ።

አቃቤ ሕግ በክስ ዝርዝሩ ላይ እንዳብራራው፤ ተከሳሽ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በቀን 02/01/2016 ዓ.ም በግምት ከለሊቱ ስምንት ሰዓት ከአስር ሲሆን፤ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ክልል ልዩ ቦታው ቦሌ ጉምሩክ ካርጎ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ አቶ ብርሃነ ወደ መኖሪያ ቤቱ ለመሔድ ተከሳሽ የታክሲ አገልግሎት እንዲሰጠው ብር 300 ተስማምተው ነበር። ተከሳሽ ላዳ መኪና እያሽከረከረ የሟች ቤት በር ላይ ሲደርሱ፤ ሟች ከመኪናው ወርዶ ቤት ገብቶ ገንዘብ ይዞ በመምጣት 100 ብር ጨምሮ 400 ብር ከፍሎታል።

ስልክ ቁጥር እንለዋወጥ ከተባባሉ በኋላ፤ ሟች ተጠርጣሪው ስልክ ቁጥሩን እንዲፅፍለት 14 ሺህ ብር የሚያወጣ ሳምሰንግ ጋላክሲ ኤ ዜሮ ሶስት ስልኩን ሰጥቶታል። ተከሳሽ ስልኩን ከተቀበለ በኋላ ስልኩን ለመውሰድ እንዲመቸው ሟች መኪናውን በከፍተኛ ፍጥነት መንጭቆ በማስነሳት ስልኩን ይዞ ሲሔድ ሟች ኮብልስቶን መንገዱ ላይ በመውደቁ የራስ ቅሉ፣ ደረቱ እና ሆዱ ላይ በደረሰበት ጉዳት ሕይወቱ ያለፈ መሆኑን የክስ ዝርዝሩ ያስረዳል።

አቃቤ ሕግ ተከሳሽ ሠፋ ሽሪፍ ድርጊቱን ስለመፈፀሙ ለፖሊስ በሰጠው የእምነት ክሕደት ቃል ላይ ማመኑን እና ከቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የተገኘው የአስክሬን የምርመራ ውጤትም ይህንኑ ድርጊት መፈፀሙን እንደሚያመላክት ለፍርድ ቤቱ ገለፀ።

**ውሳኔ**

ሠፋ ሽሪፍ ሳቢር በተከሰሰበት ከባድ የውንብድና ወንጀል ጉዳዩ በክርክር ላይ ቆይቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ችሎት በሰኔ 28 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት፤ ፍርድ ቤቱ ክስ እና ማስረጃውን ከሕግ ጋር አገናዝቦ ተከሳሹን ያርማል ሌሎችንም ያስተምራል በማለት በአስራ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ውሳኔ አስተላልፏል።

# መስቀል እና ሽምግልና

**ዋስልኝ አየለ**

ሃይማኖታዊ በዓላት ሃይማኖታዊ ብቻ አይደሉም። ባህላዊና ሞራላዊ እሴት አላቸው። ባህላዊ እሴቶች የልጃገረዶችንና የወጣቶችን መንፈስ ያድሳሉ። አዲስ ተስፋን ያበስራሉ። ሞራላዊ እሴቶች የህብረተሰቡን አብሮ መኖርና መተጋገዝ ያጠነክራሉ። ይሄ በኢትዮጵያ ምድር የተለመደ ነው። ጎዳና ላይ የወደቁ ወገኖች እንኳን ጎብኚ የሚያገኙት በበዓላት ቀን ነው። በዓላትን ብቻ ጠብቆ ማድረጉ ትክክል ባይሆንም (የሀገሪቱን የኢኮኖሚ አቅም እናስብና) በበዓላት ቀን ራሱ ማሰቡ ግን የሞራል ልዕልናን ይጠይቃል።

ሌላው የበዓላት ውበት የማህበራዊ ሕይወት ልዕልና መሆናቸው ነው። አንድ አባካኝ፣ ዕቅድ የለሽ፣ ለሰው የማይጨነቅ... የሚባል ሰው ሳይቀር ለበዓላት ሰዋዊ ዝግጅት ያደርጋል። ከወዳጅ ዘመድ ይገናኛል። በአጠቃላይ በዓላት ማህበራዊ ሕይወትን ያጠናክራሉ።

በዓላት የየራሳቸው ባህላዊና ሃይማኖታዊ ይዘት አላቸው። ከመስቀል በዓል የማስታውሰው የሽምግልና ሥነ ሥርዓት ነው።

በአካባቢ አወዛጋቢ ነገር ሲያጋጥም ችግሩ የሚፈታው በሽማግሌ ነው። የተጣላ ሰው የሚታረቀው በሽማግሌ ነው። ለመስቀል ደግሞ እርቅ የግድ ነው። መስቀል በ 17 ይሁን እንጂ፤ የመስቀል በዓል ግን እንደየአካባቢው ባህል እስከ 20 ምናምን ሁሉ ይቆያል። በቡድን የሚከበርባቸው አካባቢዎች ይኖራሉ። ይህ የመስቀል በዓል እንዲህ ጎረቤት ተሰባስቦ መከበሩ አንድ ልዩ ባህሪ እንዲኖረው አድርጎታል።

የመስቀል በዓል የቤት ውስጥ በዓል አይደለም፤ ጎረቤት ተሰባስቦ ሜዳ ላይ በጋራ የሚከበር በዓል ነው። በዚህ በዓል ውስጥ ታዲያ አንድ የማውቀው ባህል የመስቀል በዓል በመጣ ቁጥር ትዝ ይለኛል። ይሄውም በመስቀል ሰሞን ሽማግሌዎች በእርቅ ሥራ የሚጠመዱት ነው። ምንም አይነት ጠብ ይሁን በአካባቢ የተቀያየመ ሰው ካለ ለመስቀል በዓል የግድ መታረቅ አለበት። የተኮራረፉ ሰዎች እያሉ በዓሉ በፍጹም ሊከበር አይችልም። እዚህ ላይ በጣም የምታስደስተኝ ሽማግሌዎች የሚጠቀሟት የማግባቢያ ስልት ናት። በእርቅ የድርድር ሥርዓቱ ውስጥ ከተደራዳሪዎች አንዱ ወይም ሁለቱም ለመታረቅ ፈቃደኛ ካልሆኑ ሽማግሌዎች እንዲህ ይላሉ።

‹‹በሉ እንግዲያውስ በዓሉ ይቅርላችሁ! እኛንም የእንጨት ሽበት አድርጋችሁናል። የዘንድሮን በዓል እንግዲህ የሰው መሳቂያ አድርጋችሁን እናሳልፈው። ‹በአካባቢው ሽማግሌ እንኳን የለም እንዴ!› እየተባልን እንሰደብ። እግዜር ዓመት ዓመቱ አድርሶ ለዚህ ያበቃንን በዓል መብራት ሲወጣ እኛ በእናንተ የተነሳ እንተወው...›› እያሉ ሽማግሌዎች ሲፈርዱ ከተደራዳሪዎች ደግሞ ‹‹እናንተ ለምን ትተውታላችሁ? እናንተ ደምሩ!›› በማለት ሁለቱም የተኳረፉት ሰዎች ‹‹እኔ እቀራለሁ እሱ አብሯችሁ ይደምር፤ እኔ እቀራለሁ እሱ አብሯችሁ ይደምር›› ይባባላሉ። አሁንም ግን ሽማግሌዎች አይበገሩም። ጭራሽ የምጸት ሳቅ እየሳቁ ‹‹የኛ ባልንጀሮች የደም እርቅ ያስታርቃሉ ‹ጎረቤት ማስታረቅ ያልቻሉ› እየተባልን ደግሞ እዚህ ደመራ ላይ ልንታይ?›› እያሉ ተራ በተራ ‹‹እኔማ የዚያን ዕለት እዚህ አካባቢ አልታይም፤ እኔም አልታይም›› እያሉ ተደራዳሪዎችን ያስፈራሯቸዋል።

የዚህን ጊዜ እንግዲህ የሚታረቁት ሰዎች የግድ መታረቅ እንዳለባቸው ያምናሉ። እርቁን እምቢ ቢሉ እንደ ጀግና ሳይሆን የሚታዩት እንደ ባለጌ ነው። በባህሉ ውስጥ ከሽማግሌ ቃል መውጣት ነውር ነው። በዓሉን ጎረቤትን አስከፍቶ መዋል በአካባቢው ያስተዛዝባል፣ በዕድርም ሆነ በሌሎች ማህበራዊ ግንኙነቶች ላይ ‹‹እሱ ደግሞ ባለጌ›› ያሰኛል። ምክንያቱም ሽማግሌ ብዙ ነገር ነው። ነገ በራሱ ላይ የሆነ ነገር ቢደርስ ከሽማግሌ አያልፍምና የሽማግሌን ሀሳብ መቀበል የግድ ነው። በዚህም ምክንያት ለመስቀል በዓል ክረምቱን ሙሉ ተኮራርፎ የከረመ ሁሉ ይታረቃል።

የእርቅ ሁኔታው እንደየቅሬታቸው ይለያያል። ቀላል የሚባል መቀያየም ከሆነ ከጎረቤት ሽማግሌዎች አያልፍም፤ ብዙ የተነጋገሩና የመደባደብ ደረጃ ላይ የደረሰ ከሆነ ደግሞ ራቅ ካለ አካባቢ ሽማግሌ ይመረጣል። የሚመረጡ ሽማግሌዎችም ብዙ የማስታረቅ ልምድ ያላቸውና የሃይማኖት አባቶች ናቸው። በዚህ በማስታረቅ ሥራ ውስጥ የሚታወቁ የአካባቢው ሽማግሌዎች ዛሬም አሉ። እስከሩቅ አካባቢ ድረስ ሰዎችን ለማስታረቅ ይሄዳሉ።

እነዚህ ሽማግሌዎች የማስታረቅ ጥበባቸው ለብዙ ሽማግሌዎች አርዓያ ሆኗል። ሽማግሌዎቹ በአዘቦት ቀን እንኳን አብረዋቸው ሲጫወቱ ብዙ ነገር የሚያስተምሩ ናቸው። ብዙ ጊዜ ነገራቸውን ከሆነ ታሪክ ጋር አያይዘው ነው የሚያወሩት። በእርቅ ጊዜም እንደዚሁ ናቸው። ነገራቸውን በሆነ ገጠመኝ ወይም በቆየ ታሪክ እያጣቀሱ የመጋጨትና የመኳረፍን ነውርነት ያስረዳሉ። የማስታረቅ ጥበባቸው እንደየታራቂዎች ባህሪ የሚመቻቸውን ስልት እየተጠቀሙ ነው። በእርቅ ውስጥ ሁሉም የሚጠቀሟቸው ዘዴዎች ቢኖሩም አንዳንዶቹ ደግሞ የራሳቸውን ስልትም ይጠቀማሉ። ዋሽቶ ማስታረቅ ከሚለው ይልቅ አሳምኖ ማስታረቅን ይችሉበታል። የሚታረቁት ሰዎች ትልቅ ቅሬታ ውስጥ የገቡ ቢሆን እንኳን በሰው ልጅ ውስጥ የሚያጋጥም መሆኑን ያሳምናሉ፤ ከዚህ የከፋ ችግር ያጋጠማቸው ሰዎች እንደነበሩና ታርቀው እንደተጋቡ ወይም በሌላ ወዳጅነት ተሳስረው ትልቅ ነገር ላይ እንደደረሱ የሚያሳይ ታሪክ ይነግሯቸዋል። ባይታረቁ ግን ልጆቻቸው ነገ በሰላም እንደማይኖሩ፣ ይባስ ብሎም ሊገዳደሉ እንደሚችሉ ይነግሯቸዋል።

እንግዲህ የመስቀል በዓል ከሃይማኖታዊ ይዘቱ በላይ እንዲህ አይነት የባህላዊና ማህበራዊ እሴት ይዘትም አለው። በተለይ የተጣሉት ሰዎች ቤተሰቦች በዓሉን በጉጉት ይጠብቁታል፤ ምክንያቱም ቤተሰቦቻቸው ይታረቁላቸዋል። የሚጣሉት ሁለት የጎረቤት አባወራዎች ሊሆኑ ይችላሉ፤ ሁለቱ አባቶች ሲኮራረፉ ልጆች ከብት ጥበቃ አብረው ነው የሚውሉት፤ ግን አባቶቻቸውን እየፈሩ አንዳቸው ሌላኛው ቤት አይሄዱም፤ በዚህ ውስጥ እንግዲህ የአባቶች መታረቅ ለልጆች የሚፈጥረውን ደስታ አስቡት!

ከዚህ አንድ ነገር እንረዳለን፤ የአዋቂዎች አዋቂ አለመሆን በልጆች ላይ የሚፈጥረውን መጥፎ ጫና! ይሄ ነገር ለጎረቤት ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገር ላለው ሁኔታም ትልቅ ትምህርት የሚሆነን ነበር። የተማርን ነን ያሉ ሰዎች በራስ ቡድን ወዳድነት ብቻ ተጠምደው ዘረኝነትን ሲሰብኩ ይውላሉ፤ እነዚህ ተፅዕኖ ፈጣሪ ናቸው የተባሉ ሰዎች ይህን ሲያደርጉ ሌላው ይከተላል ማለት ነው።

እንዲህ ነው እንግዲህ የሽማግሌ ሃይል። የአካባቢው ማህበረሰብ እምነት የሚጥልባቸው። ገበሬዎች የሚጠቀሙት አንድ ሥነ ቃል እንዲህ ይላል።

**እንበለውና የመጣው ይምጣ!**
**ከሽማግሌ ከእርቅም አይወጣ**

የዚህ ሥነ ቃል ትርጉም እንበለው፣ እንደባደብ ማለት አይደለም። የሥነ ቃሉ ትልቁ መልዕክት የትኛውም ነገር ከሽማግሌ እንደማይወጣ ነው። በምሳሌያዊ ንግግሮቻችን እንኳን ሽማግሌ የሃሳብ ሃይል እንዳለው የሚያሳዩ ናቸው።

ሽማግሌ በምክሩ አርበኛ በሰናድሩ፣ ሽማግሌ ሳለ ምክር አይጠፋም ጎረምሳ ሳለ ላም አይነዳም፣ ሽማግሌ ካለበት ነገር አይናቅም፣ ሽማግሌ ካልሞተ ስንዴ ካልመረተ፣ ሽማግሌ ይገላግላል የተጠቃ አቤት ይላል፣ ሽማግሌን ከምክር ከመለየት ከምግብ መለየት... የሚሉት ይገኙበታል። ክብር ለሽማግሌዎች!

## ዓለም አቀፍ

# የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ጦራቸው ከሔዝቦላሕ ጋር በሙሉ ኃይሉ እንዲዋጋ አሳሰቡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



<u>አዲስ አበባ</u>፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ ከአሜሪካና ሌሎች አጋሮቻቸው በኩል ተኩስ እንዲያቆሙ ቢጠየቁም ወታደሮቻቸው ሔዝቦላሕን በሙሉ ኃይል እንዲፋለሙ አሳስበዋል።

የሊባኖስ የጤና ሚኒስቴር ሐሙስ ብቻ በአየር ጥቃት 92 ሰዎች መገደላቸውን ይፋ አድርጓል። ሔዝቦላሕ በበኩሉ በደቡባዊ ቤይሩት እስራኤል በፈጸመችው የአየር ጥቃት የቡድኑ የድሮን ክፍል ኃላፊ መሐመድ ሱሩር መገደሉን ይፋ አድርጓል።

በሔዝቦላሕ እና እስራኤል መካከል የሚደረገው ውጊያ ከቁጥጥር ውጭ እንዳይወጣ ስጋት አለ። እስራኤል ከሰኞ ጀምሮ በሊባኖስ ጥቃት እያደረሰች ትገኛለች። በተባበሩት መንግሥታት የእስራኤል አምባሳደር ዳኒ ዳነን ሀገራቸው ለውይይት በሯ ክፍት ነው ማለታቸውን ተከትሎ የተኩስ አቁም ተስፋ ተደርጎ ነበር።

ሆኖም ከትናንት በስቲያ ሐሙስ ሃሳቡ በእስራኤል ፖለቲከኞች ሙሉ በሙሉ ውድቅ ተደርጎ ጦርነቱ ቀጥሏል። ለተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ኒው ዮርክ የሚገኙት ኔታንያሁ ሀገራቸው እስራኤል ‘‘ግቧን እስክትመታ’’ ጦርነቱን እንደማታቆም ዝተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ግብ አድርገው ካስቀመጧቸው ነገሮች አንዱ በሰሜን እስራኤል የተፈናቀሉ ነዋሪዎች ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ ማስቻል ነው።

‘ኋይት ሐውስ’ በበኩሉ ኔታንያሁ ይህን ይበሉ እንጂ የተኩስ አቁሙ በመልካም ሁኔታ እየተሳለጠ ነው ብሏል። የዩኬው ጠቅላይ ሚኒስትር ሰር ኪየር ስታርመር በሊባኖስ ያለውን ችግር ለመቅረፍ አስቸኳይ የተኩስ አቁም እንዲደረግ ጠይቀዋል።

የእርሳቸው ስጋት ይህ ጦርነት ገደቡን ጥሶ ከወጣ ማንም የሚቆጣጠረው አይሆንም የሚል ነው። እስራኤል በጋዛ የከፈተችውን ዘመቻ ተከትሎ በጦርነት ስጋት 70ሺህ የእስራኤል ዜጎች ከሊባኖስ ድንበር አቅራቢያ ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲሄዱ ተደርጓል። ይህም ሔዝቦላሕ ሊያደርስ የሚችለውን ስጋት በመፍራት የተካሄደ ነው።

በሊባኖስ በኩል ደግሞ ባለፉት አራት ቀናት ብቻ 90 ሺህ ሰዎች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል። ከዚህ ቀደም ብሎ ደግሞ ጦርነቱን በመፍራት 110 ሺህ ነዋሪዎች ከቤታቸው ሸሽተዋል ይላል የተባበሩት መንግሥታት።

እስራኤል ከሰሞኑ በፈጸመችው ጥቃት ሔዝቦላሕ የስንቅና ትጥቅ ማስተላለፊያ ይሆኑታል የተባሉ መሠረተ ልማቶች ወድመዋል። ይህም በሶሪያና ሊባኖስ ድንበር የሚገኝ ነበር።

ሔዝቦላሕ በበኩሉ 50 ሮኬቶችን ወደ ኪርያት አታ ከተማ እንዲሁም 80 ሚሳኤሎችን ወደ ሳፌድ ከተማ ተኩሻለሁ ብሏል። ሁለቱም የሰሜን እስራኤል ከተሞች ላይ የደረሰው ጉዳት በውል አይታወቅም። እስራኤል ከየመን የተተኮሰ ሚሳኤል አከሸፍኩ ብላለች።

የእስራኤል አየር ኃይል ኮማንደር ጄኔራል ቶመር ባር ሐሙስ ለወታደሮቻቸው ሲናገሩ አሁን እየተካሄደ ያለው ኦፕሬሽን ወደ ሊባኖስ እግረኛ ለማስገባት የሚያዘጋጅ ነው ብለዋል።

ይህ በእንዲህ ሳለ የኳታር መንግሥት ቃል አቀባይ ማጂድ አል አንሳሪ ሀገራቸው በሊባኖስ አሰቃቂ የቤተሰብ እልቂት ዜናዎች እየደረሷት እንደሆነ ተናግረዋል። የንጹሃን ሰቆቃው የጋዛን የሚመስል እንደሆነም ተናግረዋል።

የዩኬና የአውስትራሊያ አቻዎቻቸው ጋር የተነጋገሩት የአሜሪካ መከላከያ ሚኒስትር ሎይድ ኦስቲን ሁለቱ ተዋጊዎች ወደለየለት ጦርነት እንዳይገቡ ብቸኛው መንገድ ዲፕሎማሲ ነው ብለዋል።

ሐሙስ ምሽት የእስራኤል መከላከያ ሚኒስቴር 8 ነጥብ 7 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት እገዛ ከአሜሪካ ማግኘቱን ይፋ አድርጓል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

ከዳግማዊ ምኒልክ ኮምፕሪሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል
ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የሆስፒታሉ-ያልተገታው ስኬታማ ጉዞ

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

የታሪክ ድርሳናት እንደሚናገሩት፤ ዳግማዊ ምኒሊክ ኮምፕሪሄንሲቭ ስፔሻሊይዝድ ሆስፒታል ሥራውን የጀመረው የሩስያ ሐኪሞች ቡድን በአዲስ አበባ አሁን ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል በሚገኝበት ቦታ ላይ ድንኳን በመትከል የሕክምና አገልግሎት በመስጠት ነው። በወቅቱ ለአድዋ ቁስለኞች ሕክምና አገልግሎት ይሰጥ ዘንድ የኢትዮጵያ መንግስት ከራሺያ መንግስት ጋር በመተባበር የተቋቋመ ነበር።

አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቶም 1989 ዓ.ም አገልግሎቱ የተቋረጠ ሲሆን፤ ከሦስት ዓመት በኋላ በንጉሰ ነግስት ዳግማዊ ሚኒሊክ በጎ ፈቃድ 1902 ዓ.ም እንደገና አገልግሎት መስጠት ጀመረ። ሁለተኛ ስራውን ሲጀምር ግን ከፈረንሳይ መንግስት ጋር በመነጋገር የፈረንሳይ ሐኪሞችን በመጠቀም እና የኢትዮጵያ ሐኪሞችን በመያዝ ሁለገብ ሕክምና መስጠት እንደጀመረ የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አገልግሎቱን እያሻሻለ ዛሬ ላይ መድረሱ ይታወቃል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ የአገልግሎት አድማሱን በማስፋት ጤናማ ማሕበረሰብ ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት ውስጥ ቁልፍ ሚናውን እየተወጣ ይገኛል።

ዳግማዊ ምኒሊክ ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻሊይዝድ ሆስፒታል ዋና ሥራ አስኪያጅ ዶክተር ተከተል ጥላሁን እንደሚሉት፤ ሆስፒታሉ ዘመናትን ተሻግሮ የመጣ ታሪካዊ ተቋም ነው። የሚሰጠውን አገልግሎት ለማስፋት በትኩረት እየሰራም ይገኛል። በተለይም ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር ተቋማት ጋር በመስራትና የማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ የሚጠበቅበትን እያከናወነ ነው።

በአሁኑ ወቅት ከጥቁር አንበሣ ሆስፒታል ስፔሻላይዝድ ጋር በመሆን የዓይን ሕክምናን በተመለከተ ተማሪዎቹ ሙሉ ለሙሉ የሚማሩት በዳግማዊ ምኒሊክ ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻሊይዝድ ሆስፒታል ነው። ጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ዕድሜ ጠገብ እና ረጅም ጊዜ ልምድ ያላቸው መምህራን እየመጡ በማስተማራቸው ተቋሙ ተጠቃሚ ሆኗል። ይህ ደግሞ ለታካሚውም ሆነ ለሆስፒታሉ ፋይዳው የጎላ ነው።

እንደ ዶክተር ተከተል ገለፃ ከጥቁር አንበሳ ጋር በትብብር ከሚሰሩ ሕክምናዎች መካከል ሌላኛው የልብ እና ሳንባ ቀዶ ሕክምና ሲሆን በጥምረት ይሠራል። የደም ቧንቧ ቀዶ ሕክምናም በተመሳሳይ ከጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በጋራ ይሰራሉ። በተመሳሳይም በሕፃናት ቀዶ ሕክምናም ተመሳሳይ ትብብር አለ።

ከቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ኮሌጅ ጋር በመሆን የፅንስና ማሕፀን ስፔሻሊስት ተማሪዎችን እየላኩ እና አገልግሎት እየሰጡ ነው። ከዚህም በዘለለ ከተለያዩ የግል ጤና ተቋማት ጋር በተለይም ደግሞ ጤና ላይ ከሚያስተምሩ ኮሌጆች ጋር ተቋሙ ይሰራል። የግል ኮሌጆች ተማሪዎቻቸው ወደ ዳግማዊ ምኒሊክ ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻሊይዝድ ሆስፒታል ‹‹ለአፓረንት ይልካሉ። የዳግማዊ ምኒልክ ሃኪሞችም ልምድ እና እውቀታቸውን ያካፍሏቸዋል፤ ያስተምሯቸዋል ብቁ ባለሙያ እንዲሆኑ ያግዛሉ። በዚህ ረገድ ጠንካራ ትስስር ተፈጥሯል።

በሀገሪቱ ካሉ ዩኒቨርሲቲዎችም ጋር በመቀናጀት በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ



ዶክተር ተከተል ጥላሁን፤

ሲሆን፤ ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን ተማሪዎችን ወደ ሆስፒታሉ ‹‹ለፕራክቲስ›› እየላኩ እውቀት እየቀሰሙ ነው። በተመሳሳይ ከጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ ሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ እና ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በትብብር እየሰራ ነው። ከዳግማዊ ምኒሊክ ጤና ሣይንስ ኮሌጅ ጋር እንደ አንድ አካል ሆኖ እየሰራ እንዳለና ወደፊትም የመዋሃድ ዕድልም ሊኖረን እንደሚችል ዶክተሩ ተስፋቸውን ገልፀዋል።

የሕክምና ተቋሙ ከውጭ ሀገራት ጋር በተያያዘ ጤና ላይ ከሚሠሩ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ጋር ትብብር አለው። በተለይም ዓይን ላይ ‹‹ኪዩር ኤንድ ብላይንድነስ›› ከሚባል ድርጅት እና ሌሎችም ጋርም አብሮ ይሰራል። በዚህም በ2016 በጀት ዓመት ማጠናቀቂያ አካባቢ ብቻ 200 የሚጠጉ ሕጻናት የዓይን ቀዶ ሕክምና አግኝተዋል። ከስፔን ሀገር የመጡ እና የመግባቢያ ሥምምነት ተፈራርመው የኦፕሬሽን ክፍል ለማዘመን ተስማምተዋል። ከኔዘርላንድ መጥተው ነፃ አገልግሎት የሚሰጡም አሉ።

ይህ አሠራር የሆስፒታሉ ባለሙያዎች ትልቅ ልምድ እና ዕውቀት የሚያገኙበት ሲሆን፤ ተገልጋዮችም ፈጣን አገልግሎት ለማግኘት ያስችላቸዋል። በአጠቃላይ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር ለማዘመንና ወደ ላቀ ደረጃ ለማሻገር ሆስፒታሉ በትጋት እየተንቀሳቀሰ ነው።

ዶክተር ተከተል ጥላሁን እንደሚሉት፤ ዳግማዊ ምኒሊክ ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻሊይዝድ ሆስፒታል ዘርፈ ብዙ ተግባራትን በማከናወን ላይ ነው። ስፔሻሊስቶች እና ሰብ-ስፔሻሊስቶችም በመላ ሀገሪቱም በመንቀሳቀስ አገልግሎቶችን እየሰጡ ይገኛል። ዓይን ሕክምና ምሩቃንም ከሆስፒታሉ ተመርቀው ወደገጠር ሲሄዱ በተለይም ደግሞ የሀገሪቱ ጠረፋማ አካባቢዎች የግብዓት እጥረት አለ። ይህን ታሳቢ በማድረግ ዳግማዊ ምኒሊክ ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻሊይዝድ ሆስፒታል የግብዓት ድጋፎችን እያደረገ ነው።

ዋና ሥራ አስኪያጁ እንደሚሉት፤ ሆስፒታሉን ዕድሜ ጠገብ ሲሆን ከ100 ዓመት በላይ ያስቆጠሩ ሕንፃዎች ያሉበት ነው። በሁለተኛው የጣሊያን ወረራ ወቅት የተገነቡ በርካታ ሕንፃዎችም አሉ። እነዚህ ያረጁ ሕንፃዎች ለሕክምና በጣም አስቸጋሪ ናቸው። ይህን በተቻለ መጠን ማስተካከል አስፈላጊ ነው። በዚህም የተነሳ በ2008 ዓ.ም ባለ ስምንት ወለል ሕንፃ ተገንብቶ አገልግሎት እየሰጠ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ዓለም አቀፍ ደረጃ የጠበቀ አገልግሎት እንዲሰጥ እየታደሰ ነው። ሆስፒታሉ በዓይን ሕክምና የሚታወቅ በመሆኑ ለዚህ ሕክምና ዓላማ ብቻ የሚውል ባለ አራት ወለል ሕንፃ ገንብቶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

ሌላኛው የወንጀል ሕክምና እና ሥነ-ምረዛ ዲፓርትመንት (Forensic and Toxicology) ራሱን ችሎ አገልገሎቱን ለማስፋፋት ባለ አምስት ሕንፃ ተገንብቶ እየተጠናቀቀ ነው። በዚህ ውስጥ በሀገራችን በጣም ችግር የሆነውን የዘረ-መል ሕክምና በሰፊው እንዲሰጥም እየተሰራበት ነው።

በተቋሙ ከካርድ መጥፋት ጋር በተያያዘ ተደጋጋሚ ቅሬታ ነበር የሚሉት ዶክተሩ፤ ከ30 ዓመት በላይ በዚህ ሆስፒታል ክትትል የሚያደርጉ አሉ። መሰል ካርዶች ሲጠፉ ለታካሚም ሆነ ለሐኪሙ እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል። ይህ ችግር ግን አሁን ተረት ሆኗል፤ ሙሉ ለሙሉ ዲጂታላይዝ ተደርጓል። በዚህ ሲስተም አንድ ሐኪም ለስንት ሕሙማን አገልግሎት እንደሰጠ ይታወቃል። ከዚህም በዘለለ መረጃ አያያዝ መዘመኑ ጥናትና ምርምር ለማድረግ ፋይዳው የጎላ ነው። በቀጣይ የእናቶችና ሕፃናት ሕክምና ማዕከል ለብቻው ሕንፃ የሚያስፈልግ መሆኑ ስለታመነበት፤ በ2018 በጀት ዓመት ለመጀመር ውጥን አለ። ለዚህም የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ፣ ጤና ሚኒስቴር እና የኮንስትራክሽና ዲዛይን ቢሮ ጋር በመነጋገር ወደ ተግባር እንገባለን።

ዘመናዊ ሕንፃዎችን ከመገንባት በዘለለም የተቋሙ ባለሙያዎችም አቅማቸውን ለማሳደግ የሚያግዛቸው ስልጠና እና ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል የሚሉት ዶክተር ተከተል፤ በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ስልጠናዎችና የትምህርት ዕድሎች ይመቻችላቸዋል። በተለይም ደግሞ ስፔሻሊቲ ሕክምናዎች ሀገር ውስጥ ብዙም የሌለ በመሆኑ ከጤና ቢሮ ጋር በመሆን ውጭ ሀገር ሄደው እንዲማሩ ዕድል እየተሰጠ ነው። ጠቅላላ ሃኪሞችም በሀገር ውስጥ ራሳቸውን በዕውቀት እንዲያሳድጉ አስፈላጊው ዕድል እየተመቻቸ ነው። እንደ ተቋም ደግሞ በሁሉም ዘርፍ ያሉ ሰራተኞች ብቁ እንዲሆኑ በጀት ተይዞ አስፈላጊ የሆኑ ስልጠናዎች ይሰጣቸዋል።

አገልግሎት ከማሻሻል አኳያ የሕክምና ጥራት ማሻሻያዎችን ላይ በትኩረት እየተሰራበት ነው። ታታሪ ሰራተኞችን ለማትጋትም የሚቻለው ሁሉ እየተደረገ ነው። ምንም እንኳን የጤና ተቋም ለትርፍ የተቋቋመ ባለመሆኑና በቂ የገንዘብ ድጋፍ ባይደረግም ምርጥ ፈፃሚዎች የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ እየተደረገ ነው። ከዚያ አነስ ለሚል ደግሞ መጠነኛ የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል። በአጠቃላይ በርካታ ፕሮጀክቶች ተነድፈው ውጤታማ ተግባራት እየተከናወኑ ነው።

ወደ ሆስፒታሉ ድንገተኛ ክፍል የመጣ ታካሚ ከ24 ሰዓት በላይ በሆስፒታሉ መቆየት የለበትም በሚል ወደ ሥራ መግባቱን የሚናገሩት ዶክተሩ፤ ታካሚው በዚህ ጊዜ ውስጥ ታክሞ መውጣት ወይንም አልጋ መያዝ አለበት። ይህ ካልሆነ ደግሞ ትክክለኛ ሕክምና ወደሚያገኝበት ተቋም መላክ አለበት። እነዚህ ለውጦች የመጡት አገልግሎትን ለማሻሻል በተነደፉ ፕሮጀክቶች እና ተግባራዊ እንዲሆኑ በተሰጠው ልዩ ትኩረት ነው።

ዳግማዊ ምኒሊክ ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻሊይዝድ ሆስፒታል በርካታ ለውጦችን እያስመዘገበ ቢሆንም ችግሮች መኖራቸውንም ዋና ሥራ አስኪጁ ይጠቁማሉ። የሕክምና መሳሪያዎች ከውጭ ተገዝተው ቢገቡም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን በትንሽ ብልሽቶች ሥራ ያቆማሉ። ይህም ሥራ ከማስተጓጎል በዘለለ የሀገር ሃብት ይባክናል። በዚህም ብዙ የሕክምና መሳሪዎች ያለ ሥራ እየቆሙ ነው። ለዚህ ትልቁ ችግር በዘርፉ የሰለጠኑ የጥገና ባለሙያዎች አለመኖር ሲሆን፤ ሌላኛው ችግር ደግሞ መሰል መሳሪያዎች ሲገዙ የሚደረጉ ሙሉ ያልሆኑ ሥምምነቶች ናቸው።


በሌላ በኩል ጠንካራ የሚባል የማትጊያ ሥርዓት አለመኖር ሰራተኞችን የበለጠ ለሥራ ለማነሳሳት ፈተና ነው። ከመሰረተ ልማት አኳያም ዕድሜ ጠገብ ሆስፒታል በመሆኑ አንዳንድ ችግሮች ይስተዋላሉ። ሌላው ቀርቶ የፍሳሽ መስመሮችን እንኳን በትክክል ለመለየት የማያስችሉ መስመሮች የተዘረጉበት ነው። ሌላው ግቢ ውስጥ የተገነቡት ዕድሜ ጠገብ ሕንፃዎች ስትራክቸር እና የማስፋፊያ ሥራ በሚገባ ማናበብ አስቸጋሪ ነው። ምንም እንኳን የሆስፒታሉ ግቢ 61 ሺ ካሬ ሜትር ቢሆንም፤ ቦታው የተያዘው በየቦታው በተገነቡ ትንንሽ ቤቶች ነው። ይህም በመሆኑም ለማስፋፊያ አስቸጋሪ ያደርገዋል።

ሌላኛው ችግር ትልልቅ የሕክምና መሣሪያዎች ግዥ ነው። ከውጭ ሀገር በጨረታ ተገዝተው የሚገቡ ቢሆንም፤ በየጊዜው ያለው የዋጋ ግሽበት ችግሮች እየፈጠሩ ነው። በተመሳሳይ መድሃኒት ግዥ ላይም ችግሮች አሉ። የእነዚህ ድምር ውጤት በሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ ብሎም የታካሚ እርካታ ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ናቸው።

እነዚህ ችግሮች ቢኖሩም መልካም አጋጣሚዎችም በርካታ መሆናቸውን የሚናገሩት ዶክተር ተከተል፤ ሕክምና የነፍስ ጥሪ በመሆኑ በታማኝነት ማገልገል ይገባል። የጤና ሥርዓቱን ለማሻሻል እና ጤናማ ማህበረሰብን ለመፍጠርም መንግስት የሰጠው ትኩረት ጥሩ ቢሆንም አሁንም የበለጠ መሥራት እንደሚገባም ያሳስባሉ።

# አስተሳሰብን በአዲስ የመቀየር ጥበብ

**አስናቀ ፀጋዬ**



የአዕምሮን እንደ አዲስ የማስተካከል ጉዳይ በጣም ወሳኝ ነው። ፈረንጆቹ ጋር ደግሞ ይህ በጣም የተለመደ ሀሳብ ነው። እንደውም /reprogram your mind/ or /reprogram your sub conscious mind/ እያሉ የተለያዩ ሀሳቦችን ያነሳሉ። ለመፍትሄዎችም የተለያዩ መፅሃፎችን ይፅፋሉ። ሴሚናሮችን ያዘጋጃሉ። ቪዲዮዎችን ይሰራሉ። በዚህም ሰዎች አዕምሯቸውን እንደ አዲስ ይቀይራሉ።

ለምን መሰላችሁ? ኑሮ ያደክመናል። ሕይወት ተደጋጋሚና አሰልቺ ትሆናለች። አዕምሯችን ብዙ መጥፎ ነገሮችን ይሸከማል። ቁጭት፣ ጭንቀት፣ ፍርሃት አለብን። በቃ! መጥፎ ስሜቶች በውስጣችን አሉ። ታዲያ እነዚህ ስሜቶች ከአእምሯችን ውስጥ መራገፍ አለባቸው። እንደ ልጅ ጥርት ያለ ሃሳብ ማሰብ አለብን። ንፁህ አዕምሮ ያስፈልገናል። አዕምሯችንን እንደ አዲስ ለማስተካከል ታዲያ ምን ማድረግ አለብን?

የመጀመሪያው አዕምሮህ እንዴት እንደሚሰራ ማወቅ አለብህ። ለምሳሌ ስልክ ነክቶ ለማያውቅ ሰው ዘመኑ የደረሰበትን የመጨረሻውን የስልክ ምርት አይፎን ሰርቲን ፕሮ ማክስ ገዝተህ ብትሰጠው «እንዴት የሚያምር የከበረ ድንጋይ ነው? ደሞ እኮ ልስላሴው» ብሎ ቤቱ እንደተራ እቃ ሊያስቀምጠው ይችላል። ለምን አያውቀውማ! አዕምሮህ ለምን እንደሚሰራና እንዴት እንደሚሰራ ካላወክ አጠቃቀሙን አታውቅበትም።

አንዳንዴ አእምሯችን እንዴት እንደሚሰራ ስለማናውቅ ስንጨነቅ መድሃኒት እንውጣለን። ትንሽ ነገር ሲገጥመን «ምነው ፈጣሪዬ ምን አደረኩህ» እንላለን። ትንሽ ነገር ሲፈጠርና መጥፎ ስሜት ሲሰማን ፈጣሪን እናማርራለን። በቃኝ እንላለን። ተስፋ እንቆርጣለን። እኔ እኮ አበቃልኝ እንላለን። ሕይወትን ትርጉም እናጣበታለን። ለምን? የአእምሯችን አሰራር አልገባንም። አዕምሯችን ነው የተጎዳው። እኛ ግን በአካል ሁሉ ነገራችን ይጎዳል።

አያችሁ የአእምሯችን አሰራር በጣም ወሳኝ ነው። ስለዚህ አንተ ሕይወትህን እየጠላሃት ያለኸው ምን አልባት አዕምሮህ እንዴት እንደሚሰራ ስላላወክ ነው። ከዚህ በኋላ ግን መጨነቅ ማቆም አለብህ። መፍራት ታቆማለህ። መጥፎ ስሜቶችና ሃሳቦች አዕምሮህን አይቆጣጠሩትም። አዕምሮህ እንዴት እንደሚሰራ ማወቅ ብቻ ነው ካንተ የሚጠበቀው።

ሁለት አይነት የአእምሮ ክፍሎች አሉ። ንቁ /conscious/ እና ድብቅ /sub-conscious/ ይባላሉ። ንቁ /conscious የአእምሮ ክፍል በጣም ንቃት ውስጥ ሆኖ ነው የሚያገለግለው። ለምሳሌ አንድ ነገር አዲስ ከሆነ ንቁ ሆነን ነው የምንሰማው። አዲስ ነገር ስንለምድ ነቃ ብለን ነው የምናዳምጠው። ለመጀመሪያ ግዜ ምግብ ያበሰላችሁ ግዜ እያንዳንዱን ሂደት በንቃት ነው የምንከታተለው። ኪ ቦርድ ለመጀመሪያ ግዜ ስንተይብ (ታይፕ ስናደርግ) እያንዳንዷን ፊደል እየመረጥን ነው።

ብዙ ግዜ ግን በቀን ውስጥ አዲስ ነገር የምንለምደው ለጥቂት ሰዓታት ነው። ብዙ ሰዓት ንቁ አይደለንም። ስለዚህ ንቁ /conscious/ የሚባለውን የአእምሮ ክፍል ብዙ ግዜ አንጠቀምበትም። ስለዚህ በጣም ወሳኙ ሁለተኛውና ድብቅ /sub-conscious/ የሚባለው የአእምሮ ክፍል ነው። ይህ የአእምሮ ክፍል ደጋግመን የምናደርጋቸውን ነገሮች የሚቆጣጠር የአእምሮ ክፍል ነው። በሰውነታችን ውስጥ ከሚካሄዱ እያንዳንዱ ሂደቶች ጀምሮ ለምሳሌ የምግብ ልመትና መተንፈስን ጨምሮ ማንኛውንም የሰውነት ስርአቶችን ይቆጣጠራል።

ይህን ብቻ ሳይሆን ልማዶቻችንን፣ ደጋግምን የምናደርጋቸውን ነገሮች በሙሉ ድብቅ /sub-conscious/ ነው የሚቆጣጠረው። ለምሳሌ የኮምፒዩተር ኪቦርድ ላይ ስትፅፍ የሆነ ሰዓት ላይ መልመድ ትጀምራለህ። ስለዚህ ይህ ድብቅ /sub-conscious/ የሚባለው የአእምሮ ክፍል ማስታወሻዎችን ይመዘግባል። ስለሆነም በኪቦርዱ ላይ ኤ የቱ ጋር እንደሆ ታውቃለህ። ወዲያው ሌሎቹንም ፊደሎች ትነካካለህ። ብዙ ነገሮች ላይ ፈጣን የምትሆነው ድብቁ የአእምሮ ክፍልህ ስለለመደው ነው። ስለዚህ ድብቁ የአእምሮ ክፍል ደጋግመን ያደረግነውን፣ ተደጋግሞ የሰማነውን፣ የተነገረንን፣ ደጋግመን ያየነውን ሕይወታችን ላይ መዝግቦ ያስቀራል። ዋናው የአእምሮ ማስታወሻ ክፍል ነው። በእሱ መንገድ እንድንጓዝ ያደርገናል።

ለዛ ነው አንዳንድ ልጅ በልጅነቱ አትችልም እየተባለ ተደጋግሞ ከተነገረው ትንሽ ከፍ ሲል አልችልም የሚል ስሜት ይሰማዋል። ስለዚህ አይሞክርም። አዲስ ነገር ላይ አይደፍርም። አንዳንድ ልጅ በልጅነቱ አንተ ጎበዝ ነህ ! ጀግና ነህ እየተባለ ያደገ ልጅ ደግሞ ደፈር ይላል። ብዙ ነገር ይሞክራል። ደጋግሞ የሰማውን በሕይወቱ ላይ ይገልጠዋል። በልጅነት ግዜ ብቻ ሳይሆን ከፍ እያልን ስንሄድ አብረናቸው የምንውላቸው ጓደኞቻችን የሚነግሩን ነገሮች በእኛ ድብቁ የአእምሮ ክፍል ውስጥ ተመዝግበው ይቀራሉ። ድብቁ የአእምሮ ክፍል አብዛኛውን የሕይወታችን ክፍል ይወስናል።

ድብቁ /sub-conscious/ የአእምሮ ክፍል አንድ የተለየ ባህሪ አለው። ሞኝ ነው። ደጋግሞ የተነገረውን ነገር ያስቀራል። መቼም ሞኝ ታውቃላችሁ። የሆነ ነገር ካደረጋችሁት «እሱ እኮ እንዲህ አድርጎኝ» ይላል። ቂም ነው የሚይዝባችሁ። ልክ «ሞኝና ወረቀት የያዘውን አይለቅም» እንደሚባለው። ሞኝ ውለታ ከዋላችሁለትም የሆነ ቀን አስታውሶ «እሱ እኮ እንደዚህ አድርጎልኝ» ይላችኋል። በቃ! ድብቁ የአእምሮ ክፍል ልክ እንደሞኝ የሰበሰበውን፣ ደጋግሞ የሰማውን መዝግቦ ያስቀራል።

እንግዲህ ለዚያ ነው አንተም የምትጨነቀው። አየህ! የሚያስጨንቁ ጉዳዮችን ደጋግመህ ትሰማለህ። ስለዚህ በሕይወትህ ትጨነቃለህ። የዘራኸውን ታጭዳለህ። የምትዘራው መጥፎ ጭንቀት፣ መጥፎ ሀሳብ፣ መጥፎ ነገር ከሆነ እሱ በሕይወትህ ይገለጣል። አሁንም የምትጨነቀው ለዚያ ነው። ደስ የሚለው ነገር ግን ይህ ድብቁ የአእምሮ ክፍልህን መቀየር ትችላለህ። እንዴት አድርገህ? እየደጋገምክ ለአእምሮህ ጥሩ ጥሩ ነገሮችን በመንገር። አዳዲስ ነገሮችን በአእምሮህ ውስጥ በመዝራት።

አይምሯችን እንደመሬት ነው። የሚዘራበትን መምረጥ አይችልም። መሬት አፍ አውጥቶ ስንዴ ዝሩብኝ አይልም። እኛ ሰዎች ነን መሬቱ ላይ የምንዘራው። ግን ደግሞ ስንዴ ፈልገን ስንዴ ከዘራን መሬቱ ስንዴ ያበቅላል። አይምሮህ አንተ የምትፈልገውን ነገር ነው የምትጭንበት። የምትሰማው ነገር ወሳኝ ነው። ጥሩ ነገር ከሰማህ በአእምሮህ ውስጥ ጥሩ ነገር እየዘራህ ነው።

አየህ! ከዚህ በኋላ አይምሮህን አዲስ ማድረግ አይደል ዓላማህ? ስለዚህ አይምሮህን የሚያስተካክል ነገር መስማት ትጀምራለህ። የምትሰማው ነገር መንፈሳዊ ነገር ሊሆን ይችላል። መልካም ነገር፣ ተስፋ የሚሰጥ ነገር ሊሆንም ይችላል። ከዚህ ውጪ ግን ሌላ ነገር አትሰማም። ሌላ ነገር አታደርግም። ትጠነቀቃለህ። ለምትዘራው ነገር ተጠንቀቅ። የአይምሮ በርህን ጠብቅ። አየህ! ከዚህ በኋላ መጥፎ ዜና መስማት የለብህም። ለምን? መጥፎ እንድታስብ ያደርግሃላ።

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በትዝታ መኖር ማቆም ይኖርብሃል። ምን አልባት ስለትናንት እየደጋገምክ ታስብ ይሆናል። ትላንት ስለደረሰብህ መጥፎ ነገር፣ ስለገጠመህ ቁጭት፣ በጣም የሚያስቆጩህን አጋጣሚዎች ታስባቸዋለህ። ጭንቀትህ ስለትናንት ነው። ስለዚህ ትላንትን በዛሬ ውስጥ እየኖርክ ነው ማለት ነው። አይምሮህ ደጋግመህ የምታስበውን ነው የሚሰጥህ። ትላንትናን ካሰብክ ትላንትናን ዛሬም ትደግመዋለህ። ሕይወት ተደጋጋሚ ትሆናለች። አሰልቺ ትሆናለች። የትናንቱን ዛሬም ትኖረዋለህ።

ታዲያ ምን ይሻላል? ነገን በዛሬ ውስጥ መኖር መጀመር አለብህ። ነገን እያሰብክ ዛሬ ላይ ጠንክር። ነገ በሕይወትህ ይገለጣል። አየህ! መልካም ነገሮችን ደጋግመህ ስታስብ መልካም ነገር በአይምሮህ ውስጥ እየዘራህ ስለሆነ መልካም ነገር በሕይወትህ ትገልጣለህ። የቀንም የሌሊትም ሕልመኛ መሆን አለብህ። የቀን ሕልመኞች መሆን በራሱ ሕይወታችንን ይቀይረዋል። ቀን ላይ ዝም ብለን ስንቀመጥ መልካም ነገሮችን ብናስብ «እንዲህ ባደርግ፣ ይሄን ባሳካ፣ ይሄ ቢኖረኝ» ብንል አይምሯችንን መልካም ነገር እየመገብነው ነው።

ድብቁ የአእምሮ ክፍል አንተ ተኝተህም ይለፋል። አንተ የምትፈልገውን ነገር ለመስጠት የማያደርገው፤ የማይቆፍረው ጉድጓድ የለም። አንዳንዴ ቁጭ ስትሉ ከሰው ጋር እያወራችሁ የሆነ ሃሳብ ብልጭ ብሎላችሁ አያውቅም? እርግጠኛ ነኝ ያውቃል። ምክንያቱም ድብቁ አይምሮ ደጋግሞ እያሰበ ነበር። አንተ ሌላ ነገር ውስጥም ብትሆን አይምሮህ መልሱን ሲያገኝ መስራት ይጀምራል።

አየህ! ስለነገ ሕልምህና መልካም ነገር ካሰብክ የሆነ ሰዓት ላይ በሕይወትህ ድብቁ የአእምሮህ ክፍል ይገልጠዋል። ፈጣሪህም ተአምሩን የሚያሳይህ በድብቁ የአይምሮ ክፍልህ ነው። ታዲያ የቀን ሕልመኛ ብቻ ሳይሆን የሌሊትም ሕልመኛ መሆን አለብህ። ልትተኛ ስትል በጣም የምትፈልገውን ነገር አጥብቀህ እያሰብክ መተኛት አለብህ። እውቁ የሳይንስ ሊቅ አልበርት አንስታይን «ልተኛ ስል በጣም ልፈታው የምፈልገውን ሳይንሳዊ ችግር እያሰብኩት እተኛለሁ። እኔ ግን የማስበው ፈትቼዋለሁ ብዬ ነው። ጠዋት ስነሳ ግን ያን ችግር ፈትቼው፤ መፍትሄውንም አግኝቼው እነቃለሁ» ይላል።

ስለዚህ የትኛውንም የዚህ ዓለም ችግር እንደፈታኸው አስበህ ምትኖር ከሆነ የሆነ ሰዓት መፍትሄው በሕይወትህ ይገለጣል። ድብቁ የአይምሮ ክፍል ስራውም ይህ ነው። ለዛ ነው የቀንም የሌሊትም ሕልመኛ መሆን ያለብህ።

በሶስተኛ ደረጃ ውስጥህ ነው ወሳኙ። ወዳጄ! ውጫዊ ነገሮችና ውጫዊ ሁኔታዎች ያንተን ውስጣዊ ሰላምና ደስታ ሊወስኑት አይገባም። መፍቀድ የለብህም። ምክንያቱም ለምሳሌ ሰዎች ሲያደንቁህ ደስ የሚልህ ከሆነ፣ ፊት ሲነሱህ፤ የልባቸውን አውጥተው መጥፎ ነገር ሲናገሩህ አንተ የሚከፋህ ከሆነ ያንተን ውስጥ እየተቆጣጠረው ያለው ውጫዊ ዓለም ነው። ዓለም ስትገላበጥ ውስጥህ መገላበጥ የለበትም። ከውጪ ወደ ውስጥ መኖር ማቆም አለብህ። ከውስጥ ነው ወደውጪ መኖር ያለብህ።

ውስጥህ ሰላምና ደስታ ካለ ዓለም አብራህ ትስቃለች። አብራህ ትደምቃለች። ሕይወትህን የሚወስነው ውስጣዊ ነገር ነው። አየህ! መለወጥና መቀየር የምትጀምረው ከውስጥ ወደ ውጪ መኖር ስትጀምር ነው። አለበለዚያ ይች ዓለም አትሞላም። ስለዚህ ዓለም በተቀየረች ቁጥር ውስጥህ የሚቀየር ከሆነ መቼም ደስተኛ አትሆንም። ሕይወትህ ላይ ጭንቀቶችና መጥፎ ሀሳቦች የሚቆጣጠሩህ ውጫዊ ነገሮችን እያየህ ነው።

አየህ! እንደዛ እንዲሆን መፍቀድ የለብህም። አንተ ሁልግዜም የሰው ልጅ ነኝ ብለህ ማመን አለብህ። «እኔ ሁልግዜም ደስተኛ ነኝ፤ በፈጣሪዬም ደስተኛ ነኝ፤ ጤና ሰጥቶኛል» በል። ያለህን እያየህ በውስጥህ እርካታ ሊኖርህ ይገባል። ያኔ ውጪህም ያምራል።

በአራተኛ ደረጃ አካባቢህን ምረጥ። አንዳንዴ አንተ በጣም አቅም አለህ። በጣም ትችላለህ። ሕይወትህ ላይ የጎደለህ ነገር የለም። ፈጣሪህ የሰጠህ ብዙ ችሎታዎች አሉህ። ብቃትህን እንዳታወጣው ያደረገህ በአካባቢህ ያሉ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። አካባቢህም ሊሆን ይችላል። ታዲያ አይምሮህን እንደ አዲስ ማስተካከል የምትፈልግ ከሆነ መቆረጥ ያለብትን ቁረጥ። መቀጠል ያለበት ነገር ካለ ደግሞ ቀጥል። ከጥሩ ሰዎች ጋር ዋል።

አካባቢህ አንተን ይወስንሃል። ለምሳሌ ማድቤትህ ውስጥ ምግብ እያበሰልክ አንድ ሰው መጥቶ ቆሻሻ ቢደፋብህ ትተናነቀዋለህ። ለምን? ምግቡ ሆድህ ውስጥ ስለሚገባ ለምትበላው ታስባለህ። አይምሮህ ውስጥ ለሚገባው ነገርም ማሰብ መጀመር አለብህ። አይምሮህ ውስጥ መጥፎ ነገር፣ ቆሻሻ ለሚበትኑ ዜናዎች፣ ሃሳቦች፣ መጥፎ ሰዎች፣ እንደማትችል ለሚነግሩህ ሰዎች ቦታ መስጠት የለብህም።

አካባቢህን በደምብ አጥናው። ላንተ የሚመጥን ከሆነ አይምሮህ እንደ አዲስ መስራት ይጀምራል። የምትሰማው ነገር በጣም ወሳኝ ነው። ሕይወትህ ላይ የሚገለጠውም ደጋግመህ የሰማኸው፣ ያደረከው፣ የምትውለው ቦታ ነው። የዛሬ አምስት ዓመት ያደረካቸው ነገሮች አሁን ያለህበትን ወስነዋል። የዛሬ አምስት ዓመት የምትደርስበትን የሚወስኑት ደግሞ አሁን የምታደርጋቸው ነገሮች ናቸው። ስለዚህ አካባህን ምረጥ።

አምስተኛውና የመጨረሻው ደረጃ የመደጋገም ኃይል ሲሆን ይህም ወሳኝ ነው። ከባድ ነገሮች ቀላል የሚሆኑት ከደጋገምናቸው ብቻ ነው። አንድን ነገር ደጋግመን ስናደርገው አይምሯችን ያንን ነገር ቀለል አድርጎ ለመስራት የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም። በአይምሯችን እየደጋገምን አንድን ነገር ስንሰራ በቀላሉ ነገሩን ዕንድንከውን ጥርጊያ መንገድ ያመቻቻል።

ስለዚህ የመደጋገም ኃይል ወደሕይወታችን እንዲገባ ማዳበር አለብን። አንተ የምትደጋግመውን ነው ሕይወትህ ላይ ምታገኘው። ደጋግመህ የምትሰማውና የምታየው ነገር በጣም ወሳኝ ነው። ስለዚህ በእጅ በእግርህ ብለህ አይምሮ ማሰብ ያለበትን እንዲያስብ አድርግ። እየደጋገምክ ለአይምሮህ ጥሩ ነገር ንገረው።

## ርዕሰ አንቀፅ

# ትምህርትን ማደናቀፍ የሕዝብ ጠላትነት መገለጫ ነው!

ማንኛውም ለሀገርና ሕዝብ አስባለሁ፤ እሠራለሁ፤ አልያም እታገላለሁ የሚል ኃይል፤ ከመናገር የተሻገረ በተግባር የሚገለጽና ሕዝባዊ ረብ ያለው ሥራን የማከናወን ልምምድ ሊኖረው ይገባል። ይሄ ባልሆነበትና ከሚነገር ሀቲት በተቃርኖ የሚገለጽ ድርጊት ባለቤት ሆኖ ግን ስለ ሀገር ቆሜያለሁ፣ ስለ ሕዝብም እታገላለሁ ማለቱ ትርጉም አይኖረውም።

በኢትዮጵያ አሁናዊ ሁኔታ የሚታየውም ይሄው ሀቅ ነው። ለምሳሌ፣ አሁን ያለንበት ወርሃ መስከረም በመላው ሀገሪቱ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን ተቀብለው ተገቢውን እውቀት የሚያስቀስሙበት ወቅት ነው። በዚህ ረገድ በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይም በአማራ ክልል ያለው እውነት ከዚህ የተቃረነ ነው።

ለአብነት፣ በአማራ ክልል ባለው የጽንፈኞች እንቅስቃሴ ምክንያት መምህራን ወደ ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ መንገድ ላይ እየተጠበቁ የሚገደሉበት፤ ተማሪዎችም ወደ ትምህርት ገበታቸው ሄደው እውቀት እንዳይቀስሙ በዛቻና ማስፈራሪያ የሚከለከሉበት፤ ትምህርት ቤቶችም ትውልድ የመቅረጫ አውድነታቸውን እንዳይላበሱ የሆኑበት ነው።

በዚህ ድርጊትም ትውልድን ለማነጽ ወደ ትምህርት ቤት የሚያቀኑ መምህራን በመንገድ ላይ ተገድለዋል። ተማሪዎችም ወደ ትምህርት ገበታቸው ገብተው የሚማሩበትን ዕድል ተነፍገዋል። ትምህርት ቤቶችም ትውልድን ተቀብለው ሊያንጹ ሲያደርጉ የነበረው ሽርጉድም ለፍሬ እንዳይበቁ ሆነዋል።

ይሄ የሆነው ደግሞ ለሀገር ዋልታ ነን፤ ለሕዝባችንም የምንሞት የሕዝብ ጋሻ ነን የሚል የማታለያ ሃሳብን በሚያራምዱ ጽንፈኛ ኃይሎች አደናቃፊነት ነው። በዚህ የማደናቀፍ ሥራቸውም ነው ዛሬ ላይ በአማራ ክልል ወደ ትምህርት ገበታ ደርሶ ዕውቀት ሊቀስም ከሚገባቸው ሰባት ሚሊዮን ያህል ሕጻናትና ታዳጊዎች መካከል እስካሁን ከአራት ሚሊዮን በላዩ ወደ ትምህርት ገበታቸው መድረስ አልቻሉም።

በዚህ መልኩ በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የታጠቁ ጽንፈኛ ኃይሎች፣ ከዚህ ድርጊታቸው ሊታቀቡ፤ ስለ ነገው የሀገር ተረካቢ የክልሉ ታዳጊ ወጣቶችና ሕጻናት ተስፋ ግድ ሊላቸው፤ እና እነዚህን ታዳጊ ወጣቶችና ሕጻናትን የጥፋት አጀንዳቸው ማስፈጸሚያ ካደረጉበት አካሄድ ሊታቀቡ፤ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ እንቅፋት ከመሆን ሊቆጠቡ ይገባል።

ይሄ ተግባር ዛሬ ላይ ለራስ ጥቅም ማስፈጸሚያነት እየተካሄደ ያለ ቢሆንም፤ በነገው የክልሉ ሕዝብ ሁለንተናዊ እድገትና ተጠቃሚነት ላይ፤ በዋናነትም ነገን በብዙ ተስፋና ሕልም ለሚጠብቁ ታዳጊ ወጣቶችና ሕጻናት ሕይወት ላይ መቆመር ነው። ዛሬን ያልተማረ ትውልድ ነገ ለሀገርም ለሕዝብም የሚተርፍ እውቀትና አቅም አይኖረውም። እውቀትና አቅም የሌለው ትውልድ በተፈጠረ ቁጥር ደግሞ በሀገርም ሆነ በሕዝብ ላይ አደጋን ይዞ ነው የሚመጣው።

ምክንያቱም፣ ያልተማረ እና ያላወቀ ትውልድ ሕልም የለውም። ሕልም የሌለው ትውልድ ደግሞ ለሀገርም ለሕዝብም የሚሆን ሃሳብም ተግባርም የለውም። ሀገር እንደ ሀገር፣ ሕዝብም እንደ ሕዝብ ደግሞ በትውልድ ሕልምና ሃሳብ ካልተመራ፤ በተግባር የሚገለጥ በትውልድ እውቀትና ትልም ካልታገዘ ከዛሬ ፈቀቅ የሚል ነገር አይኖረውም። ይልቁንም ነገን የማያልም፣ ከዛሬ የሚሻገር ሕልምና ግብ የሌለው ትውልድ በተፈጠረ ቁጥር ጉዞው የቁልቁለት፤ መንገዱም የኋሊት ነው የሚሆነው።

በተለይ ደግሞ ዛሬ ላይ በታጠቁ ጽንፈኞች ወደ ትምህርት ገበታው እንዳይሄድ የተፈረደበት የአማራ ክልልም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች ያለ ታዳጊ ወጣትና ሕጻን፤ ነገ ላይ በሀገር ግንባታ ሂደትም ሆነ በሕዝቦች ሁሉን አቀፍ ተሳትፎና ተጠቃሚነት እውን መሆን ሂደት ውስጥ እዚህ ግባ የሚባል ሚና እንዳይኖረው የሚያደርግ ነው።

ሊታወቅ የሚገባው ግን፣ ሀገር የምትገነባው፤ ሕዝብም ወደ ተሟላ ከፍታው ሊደርስ የሚችለው ዜጎች በእውቀትም በሙላትም የድርሻቸውን መወጣት ሲችሉ ነው። አሁን እየተደረገ ባለው የታጠቁ ጽንፈኛ ኃይሎች አካሄድ ግን ይሄ እሳቤ ፈጽሞ የተዘነጋ በመሆኑ፤ ከዚህ ነገ ላይ ክፉ ጥላን አጥልቶ ከሚያልፍ ተግባራቸው ሊቆጠቡ ይገባል።

ከዚህ በተጓዳኝ ዛሬ ላይ የሚፈጸሙ ማናቸውም ተግባራት፣ በነገው የትውልዶች እድል ፈንታ ላይ የሚወስኑ እንደመሆናቸው፤ ከጽንፈኛ ታጣቂ ኃይሎች ባሻገር ያሉ የትምህርት ባለድርሻዎች ከእነሱ የሚጠበቀውን ተገንዝበው ከወዲሁ ኃላፊነታቸውን መወጣት፤ የጸጥታ ኃይሉ ለክልሉም ሆነ የሰላም ችግር ባለባቸው አካባቢዎች እያከናወነ ያለውን ተግባር በሙላት መደገፍና ለዘላቂ ሰላሙ አቅም መሆን ይጠበቅባቸዋል። ይሄ ሲሆን ነው የዛሬ ተግባራችን በትውልዶች ነገ ላይ የተሻለ ነገርን የሚያኖረው!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


## ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# ባህላዊ እሴቶቻችን የጋራ ማንነታችን መገለጫ ናቸው

ሚሊዮን ሺበሺ

ባህል በመለያነት የአንድ ማህበረሰብ ሊሆን ይችላል። ባህሉን የሚያንፀባርቀው የሆነ አካባቢ ማህበረሰብ ሊሆን ይችላል። የፈጠረውና ያዳበረው አንድ ማህበረሰብ ሊሆን ይችላል። ይህ ማህበረሰብ ምናልባትም ‹‹የባህሉ ባለቤት›› ሊባል ይችላል፤ ምናልባትም በተለየ መንገድ ሊኮራበትም ይችላል።

አንድን ባህልና ሥርዓተ ክዋኔ ግን ‹‹የእገሌ ብቻ ነው›› ማለት እልም ያለ ኋላቀርነት ነው። በዚህ ዓለም አንድ በሆነበት ዘመን፣ በአንድ አካባቢ የሚከወን ሥርዓተ ክዋኔ ብዙዎች ጋ የመድረስ ዕድል አለው። በብዙዎች የመታየት ዕድል አለው። ስለዚህ ብዙ ሰው ይጋራዋል፤ ብዙ ሰው ሊወደው ይችላል ማለት ነው።

በነገራችን ላይ ‹‹ዓለም አንድ ሆናለች፣ ዘመኑ የሉላዊነት (ግሎባላይዜሽን) ነው›› ሲባል የግድ በቴክኖሎጂ ውጤቶች ብቻ አይደለም። ዓለም አንድ ሆናለች ሲባል በአመለካከት ጭምር ነው። ከሰፈርና ከመንደር አጥር በመውጣት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ሰው ሩቅ ምሥራቅም ሆነ ሩቅ ምዕራብ ያለ ነገር የራሱ መንደር ጭምር ነው። ከመልከዓ ምድራዊ መንደርነት መውጣት አለበት። በዚህ ዘመን የትኛውም የዓለም ጫፍ ላይ የሚደረግ ነገር ጠቃሚ ሆኖ ካገኘው የትኛውም የዓለም ጫፍ ላይ የሚኖር ሰው ይጠቀመዋል። ‹‹ይህ የኔ አይደለም፣ እኔ የፈጠርኩት አይደለም፣ የኔ ወገኖች የፈጠሩት አይደለም...›› ብሎ አይተወውም፤ ምክንያቱም ቴክኖሎጂው ብቻ ሳይሆን አመለካከታችንም አንድ እየሆነ ነው። በአጭሩ የማንም ነገር የሁሉም ነው።

ሰሞኑን የመስቀል እና የኢሬቻ በዓላት በኢትዮጵያ ይከበራሉ። በተለይም ኢሬቻ ደግሞ በአዲስ አበባ እና በቢሾፍቱ በልዩ ሁኔታ ይከበራል። የመስቀል በዓል ደግሞ በሰሜን እና በደቡብ ኢትዮጵያ፣ በአዲስ አበባ፣ በልዩ ሁኔታ ይከበራል። በልዩ ሁኔታ የሚከበሩበትን ማለታችን እንጂ ሁለቱም ከተጠቀሱት ቦታዎች ውጭም ይከበራሉ። የመስቀል በዓል ሃይማኖታዊ ይዘቱ የሚጎላ ቢሆንም በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ግን መልከ ብዙ በዓል ነው።

ኢሬቻም ለፈጣሪ ምስጋና የሚቀርብበት ሃይማኖታዊ መልክ ያለው ቢሆንም የኦሮሞ ባህልና እሴት የሚንፀባረቅበት በዓል ነው። በተለይም ባለፉት አምስትና ስድስት ዓመታት በአዲስ አበባና ቢሾፍቱ በልዩ ሁኔታ እየተከበረ ነው።

የአጀንዳችን ዋና ጉዳይ ግን የእነዚህን በዓላት ምንነትና አከባበር ማብራራት አይደለም። እነዚህ በዓላት አጀንዳ በሆኑ ቁጥር በአንዳንድ ወገኖች ብሽሽቅ የሚኖረው ለምንድነው? ‹‹የኛ ነው አትንኩብን!››፣ ‹‹የእናንተ ነው አይመለከተንም!›› የሚባለው ለምንድነው?

ዓለም አንድ ሆናለች ስንል በአመለካከት ጭምር ነው ብለናል። ስለዚህ በአንድ ትንሽዬ መንደር ውስጥ የምትደረግ ነገር ዓለምን ልታዳርስ ትችላለች። ይህ የሚሆነው ነገርየውን ለማዳረስ የሚያስችል ፈጣሪን የቴክኖሎጂ ግብዓት ስላለ አይደለም፤ ይልቁንም የጋራ ፍላጎት፣ የጋራ ስሜት፣ የጋራ ደስታና ኀዘን ስለሚፈጠር ነው።

የሰሞኑ አጀንዳ ኢሬቻ ነውና ኢሬቻን ምሳሌ እናድርግ። በኢሬቻ ሥርዓተ ክዋኔ ውስጥ የሚደረጉ ነገሮችን ስናይ ሥርዓተ ክዋኔውን ከሚፈጽሙ ሰዎች እኩል እንደሰታለን፤ በሚደረጉ ነገሮች እንደመማለን። ለዚህ ዝግጅት በተዋቡ ቆነጃጂት እንማረካለን፤ ይህ ተፈጥሯዊ ግዴታ ነው። ባህላዊ ጭፈራዎችም ሆኑ ትውፊታዊ ክንውኖች ያስደስቱናል።

ይህን ስል ግን ሁሉም ሰው ይደሰታል ማለት አይደለም። የማይደሰት ይኖራል፤ ጭራሽ ይባስ ብሎ የሚናደድም ይኖራል። ‹‹ለምን?›› እና ‹‹ማን?›› የሚሉ ጥያቄዎችን እንያቸው።

በእንዲህ አይነት ሥርዓተ ክዋኔዎች የማይደሰት ይባስ ብሎም የሚናደድ ውስጡ ነፃ ያልሆነ ሰው ነው። ነፃ ያልሆነው ደግሞ በጥላቻ ነው። ይህ ማንንም ሳይሆን የሚጎዳው ራሱን ነው። ‹‹አለመውደድ፣ አለማድነቅ.... መብት ነው›› ሊባል ይችላል። አዎ! መብት ነው! በግድ ውደድ ሊባል አይችልም። ሲጀመር ይህ ስሜት እንጂ በትዕዛዝ የሚሆንም አይደለም። በዚህ ዘመን መብትን ማክበር መሠልጠን ነው። ልብ ማለት ያለብን ግን ያልወደደበት ምክንያት ከመብት አንፃር ብቻ አይደለም። ከጥላቻ ነው፤ ውስጣዊ ነፃነት ከማጣት ነው። በፖለቲካዊ መንገድ የሚባሉ ነገሮች ተፅዕኖ ስለሚያደርጉበት ነው። ለሆነ አካል ስለሰጠው ነው። ‹‹አለመውደድ መብት ነው›› ብለን ማለፍ እንችል ነበር፤ ችግሩ ግን ይባስ ብሎ እንደ ጭቆና የሚያየውም አለ። መከናወኑን የሚቃወም አለ። ንቆ መተው ይቻላል፤ ዳሩ ግን እንዲህ አይነት ትንንሽ ነገሮች ሲደማመሩ የትርክት ተፅዕኖ ይፈጥራሉ። የምርም ሰዎችን ለመጉዳት የሚደረግ ሥርዓተ ክዋኔ ነው ብሎ የሚያምን ይኖራል። ልብ መባል ያለበት ነገር ግን በዚህ ዘመን የትኛውንም ባህልና ሥርዓተ ክዋኔ አለማክበር ኋላቀርነት መሆኑን ነው።

እዚህ ላይ ግን አንድ ልብ መባልና ደፈር ብሎ በግልጽ መነገር ያለበት ነገር የመንግሥት አካላት ቱባ የሆኑ የማህበረሰብ መገለጫዎችን ከፖለቲካ ጋር መቀላቀላቸውን ነው። ይህን እየተሸፋፈኑ ማለፍ ራስን መሸወድ ነው። ዜጎችን የበለጠ ወደ እልህና ጥላቻ እንዲገቡ ማድረግ ነው። ዜጎች በፍርሃት ዝም ቢሉ እንኳን በውስጣቸው ግን ማማረራቸው አይቀርም። እንዲህ አይነት የማህበረሰብን መገለጫ ባህል ሰዎች በንጹህ ልባቸው እንዲወዱት ማድረግ እንጂ በብሽሽቅ እና በእልህ መጫን አይቻልም። አሸንዳ፣ ሻደይ፣ አሸንድዬ፣ ኢሬቻ... በመሳሰሉት ባህላዊ በዓላት ላይ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች የሚያደርጓቸው ንግግሮች ብሽሽቅ የተጫናቸው ናቸው። ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በፖለቲካዊ መድረኮች መናገር ሲገባቸው በእንዲህ አይነት የባህል ጨዋታ መድረኮች ላይም ይናገራሉ። ከብዙ ዘመናት በፊት የነበረ ነገር እያመጡ ‹‹ድሮ እንዲህ ይደረግ ነበርና...›› ይላሉ። በቃ! እሱ የተደረገው ድሮ ነው!

በተቃውሞ ጎራ ያሉት ደግሞ በፖለቲካ ትግል አልሳካላቸው ሲል እንዲህ አይነት ባህላዊ ነገሮችን እንደ አጀንዳ ይጠቀሟቸዋል። እንቶኔ በእንቶኔ ላይ የጫነው ነው ይላሉ። ወይም ፀጉር በመሰንጠቅ ይህ የተደረገው እንዲህ ለማድረግ ተፈልጎ ነው በማለት ሰው ያላሰበውን ያሳስባሉ፤ ያልታሰበና ያልተቀኘ ቅኔ ካልፈታነው ይላሉ። ደግነቱ ግን ሁለቱንም ሕዝብ እየነቃባቸው ነው። ያም ሆኖ ግን ተፅዕኖ መፍጠሩ አይቀርም።

ስለዚህ የሁላችንም አመለካከት የዘመኑነን ሰዋዊ ነፃነት የሚመጥን መሆን አለበት። የአንዱ አካባቢ ውብ ባህል ለሌላውም ውብ የሚሆነው በንፁህ ልቦና ሲታይ ነው፣ በንጹህ ልቦና ሲከበር ነው። በአንዲት የዓለም ዳርቻ የተደረገ ነገር ሰፍ ብለን የምናየው ነገርየው በራሱ እንድንወደው ስላደረገን እንጂ ሰው አስገድዶን አይደለም። አሸንዳንም ሆነ ኢሬቻን የምንወደው ውብ ባህሉን እንጂ የሕወሓት ወይም የብልጽግና ካድሬ አስገድዶን አይደለም። በመንግሥት በኩል ይህ ልብ መባል አለበት።

አንዳንድ ወገኖች ደግሞ ነገርየውን መንግሥት የፈጠረው የሚመስላቸው አሉ። እንዲህ አይነት ባህሎችና ትውፊቶች ለሺህ ዘመናት በውርርስ የመጡ እንጂ መንግሥት የፈጠራቸው አይደለም፤ የሕዝብ ናቸው። እንዲህ አይነት ባህሎች እንዲከበሩ መንግሥት ደግሞ ማመቻቸት አለበት፣ ኃላፊነቱም ነው። በአንድ በኩል የራሳችን ለሆኑ ነገሮች ትኩረት ይሰጥ እያልን በሌላ በኩል ደግሞ መበሻሸቅ አያዋጣም። ሲጠቃለል፤ በዚህ ዘመን የማንም ባህል የሁሉም ነው!


ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፣ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፣ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## ያልጠለቀች ጀንበር ...

መልካምሥራ አፈወርቅ



ዕትብቷ የተቀበረው ከአባ ጅፋር አገር ከጅማ ምድር ነው ። ተወልዳ ባደገችበት ከተማ ተምራ፣ ትዳር ይዛ ወግ ማዕረግ ማየት አልታደለችም። ድንገት ከቤተሰብ ጋር የተነሳ ግጭት ሰላሟን ነሳት። ይህ እውነት ለቀጣይ ሕይወቷ ዕንቅፋት መስሎ ቢታያት ቆም ብላ አሰበች።

የሀሳቧ ዳር በዝምታ አልተቋጨም። ከ‹‹ነገሩ ጦም እደሩ››ን መረጠች። ውስጧ ርቆ መሄድን ቢያልም ሩቁን መንገድ አሳያት። ውላ ማደር አልፈለገችም። ጓዟን ሸክፋ ተነሳች። ዘመዶቿን ትታ ጅማን ተሰናብታ አዲስ አበባ ገባች።

ዘቢደር ኩራባቸው የአዲስ አበባ ሕይወት በስራ ተቀበላት። ጉልበቷን ሳትሰስት፣ አቅሟን ሳትደብቅ ከሚተጉት ጋር ዋለች። የላቧን ዋጋ አላጣችም። በሰራችው ልክ እያገኘች ራሷን አቋቋመች። ዘቢደር መልካም ባለሙያ ነች። የድግስ ዝግጅት ባለ ጊዜ እጇን የሚሹ ፈልገው ያገኟታል። ዝናዋን የሰሙ ሌሎች አድራሻዋን አያጡትም ። ስትፈለግ ትገኛለች። ስትጠራ ትመጣለች።

ለዘቢደር አሁን ጅማና ቤተሰቦቿ ትዝታዎች ናቸው። የአቅሟን ቤት ተከራይታ መኖር ከጀመረች ዓመታት ተቆጥረዋል። ዘቢደር ሥራ ባገኘች ግዜ እረፍት ይሉትን አታውቅም። የተሰጣትን ኃላፊነት በወጉ ልትወጣ ሌት ተቀን ትደክማለች።

ሁሌም እሳትና ሙቀት የማያጣው ውሎዋ አንዳንዴ በድካም ያልፋል። እንዲህ በሆነ ጊዜ ጤናዋ ከስጋት መውደቁ አይቀርም። አዲስ አበባ ስራውን ከጀመረች ወዲህ የስኳር ሕመም አግኝቷታል። ለመፍትሄው የምትወስደውን የኢንሱሊን መርፌ የምትወጋው በራሷ እጅ ነው።

ዘቢደር የስኳር ሕመሟና አድካሚ ስራዋ እየታገሏት ነው። ኑሮን አሸንፎ ለመቆም አትሆነው የለም። አንድ ቀን ግን ይህ አይነቱ ትግል ካላሰበችው አጋጣሚ አደረሳት። እየተራመደች ሳለ ሕመሟ ከመንገድ ጣላት። በዚህ መነሻ ችግሯ እየከፋ፣ ድካሟ እየባሰ ሄደ። ሕክምና ጀምራ፣ መድሀኒቷን ተከታትላ ወደስራዋ ተመለሰች።

### በሌሳ ቀን...

ከቀናት በአንዱ ዘቢደር እንደልማዷ ከቤት ወጣች። ክረምቱ ሊገባ ‹‹መጣሁ›› ማለት ይዟል። ዕለቱ ካለፉት ቀናት የተለየ አይደለም። ድካም ቢጤ ቢሰማትም መንገዷን አላቆመችም። ባልዘገየ፣ ባልፈጠነ እርምጃዋ ጉዞዋን ቀጠለች። ድንገት በእሷ ላይ የሆነው አጋጣሚ ግን ሁኔታዎችን እንዳልነበሩ ቀየራቸው።

ዘቢደር ዓይኗ ላይ የሆነ ነገር አጭበረበራት። ፊቷን በእጇ ከልላ ልትከላከለው ሞከረች። ማጭበርበሩ እንዳሰበችው አልተዋትም። እንደምንም መሬቱን ፈልጋ በዝግታ አረፍ አለች። ሰውነቷ ቦታ ከመያዙ አንዳች ነገር ዓይኖቿን ሲከልላት ታወቃት። አሁንም በእጇችዋ ፊቷን እየሞዠቀች ሁኔታውን ታገለችው። ማጭበርበሩን ተከትሎ በድንገቴ ጨለማ ተጋረደች።

ራሷን አላመነችውም። ብርሀን ፍለጋ ወደሰማይ አንጋጠጠች። ከጸሀይዋ ሙቀት በቀር የደረሳት የለም። ዓይኖቿን እየገለጠች፣ እየጨፈነች ጭላንጭል ፍለጋ ዋተተች። አዲስ ነገር አልተገኘም። በአፍታ ቆይታ ዓይኗ ከብርሀን ተራርቆ መሄጃዋ ጠፋት።

እንደምንም ከቤት ደርሳ የሆነባትን ለጎረቤት አዋየች። የሰሟት ሁሉ የምትለውን አላመኑም። የፈጠጡ ዓይኖቿን እያዩ ደህንነቷን አረጋገጡላት። በወቅቱ በአቅሟ ለመታከም ሞከረች። የዓይኗ ችግር ሞራ መሆኑ ተነገራት። እንደጅማሬው በርትታ አልቀጠለችም። ወጪው ሲከብዳት ቸልተኝነት አበዛች።

ዘቢደር ግራ ዓይኗን እንደጋረዳት በቀኙ ብቻ ስትመራ ከረመች። ይህ እውነት ግን ብዙ አልቀጠለም። በሌላ ቀን በድንገት የቀኝ ዓይኗም ተስፉ ተጋረደ። ሁለቱም ዓይኖቿ ከብርሀን ተጣልተው ከጨለማ ተዋደዱ። ዘቢደር በድንገት የጀመራት ችግር ከእይታ አራርቆ ዓይነ ስውርነትን አስተዋወቃት።

ትናንት በሩጫ የሚተጉ እግሮች ዛሬ ከቤት ውለዋል። ሰርተው የሚያበሉ እጆች አሁን በችግር ተይዘው የሰው ፈላጊ ሆነዋል። ከምንም በላይ ንቁና ፈጣን የነበሩ ውብ ዓይኖች በጠዋቱ በጨለማ ተጋርደዋል።

ዘቢደር ሁለት ዓይኖቿ ከታወሩ ጀምሮ የሕይወት አቅጣጫዋ ተቀየረ። ከመስራ ወደመቀመጥ፣ ከመኖር ወደ አለመኖር የቀየራት ክፉ አጋጣሚ ካልታሰበ መንገድ አዋላት። ትናንት የሚያውቋት በርካቶች ሊረዷት ተረባረቡ። ዝቅ ያለው ጉልበቷ፣ የታዘዘው ማንነቷ ጥሎ አልጣላትም። ቀን ቆጥሮ ዋጋዋን በመልካም መለሰ። ጎረቤቷቿ፣ ባልንጀሮቿ ታሪኳን የሰሙ ሁሉ ጎዶሎዋን ሊሞሉላት ፈቀዱ።

### ጉዞ በነጭ በትር ...

አሁንም የሕይወት ትግሉ ቀጠለ። ዘቢደር ከስኳር ሕመሟ እየታገለች ራሷን ልታሸንፍ ቆመች። የሚንከባለሉ ንጹህ ዓይኖቿ ዛሬም አስተውለው የሚያዩ ይመስላሉ። አሁንም በነጭ በትሯ እየተመራች የጎደለ ኑሮዋን ልትሞላ ተንቀሳቀሰች።

ትናንት ትሮጥበት የነበረ ሜዳ ዛሬ ዙሪያው ገደል ሆነባት። የምታውቀው ሁሉ ባዕድ መስሎ ተሰማት። ዘቢደር ከትናንት ማንነቷ ብዙ የሕይወት ሰበዞች ጎደሉባት። ሳታስበው የሌሎች ጥገኛ ያደረጋት ዓይነስውርነት ቀላል የማይባል ዋጋ ያስከፍላት ያዘ። በብዙ ክፉ አጋጣሚዎችም አመላለሳት።

### ‹‹ከንፈር መሀል ጥሬ››

በአንድ ምሽት በነ ዘቢደር መንደር ድንገቴ የእሳት አደጋ ተነሳ። ይህን ተከትሎም ጩኸት ግርግሩ በረከተ። ነገሩ ባስ ባለ ጊዜም ብዘዎች ሕይወታቸውንና ንብረታቸውን ለማዳን ሩጫ ጀመሩ። ሰፈሩ ሰባ ደረጃ ከሚባለው አካባቢ ነው። አብዛኛው ኑሮው በወንዝ ዳርቻ በመሆኑ አቅጣጫውን ወደ ውሀው አድርጓል።

እሳቱ እየባሰ ችግሩ ስር መስደድ ሲጀምር አብዛኛው እየተጠራራ ‹‹እግሬ አውጭኝ›› ሲል ከአካባቢው ራቀ። ይህ ሁሉ ሲሆን ብቸኛዋን ዓይነስውር ያስታወሳት አልነበረም። ዘቢደር እሳቱ ተቀጣጥሎ ከእሷ ጥግ እስኪደርስ በፍርሀትና በመቁነጥነጥ ቆየች። ተደግፋው ከቆመችበት ግንብ በቀር የጠበቃት አላገኘችም።

እሳቱ አራት ቤቶችን አቃጥሎ፣ ብዙ ንብረቶች አወደመ። ዘቢደር ጭሱና ወላፈኑ ወደእሷ ሲቀርብ ይሰማታል። አሁንም ግን የትነሽ ሲል የሚፈልጋት አልተገኘም። ደጋግማ እየጮኸችና እየጸለየች ፈጣሪዋን ‹‹እየኝ፣ ተመልከተኝ ›› ብላ ተማጸነች። ልመናዋ ከመሬት አልወደቀም። ‹‹ከንፈር መሀል ጥሬ›› እንዲሉ ያን የጨለማ ክፉ አጋጣሚ በተአምር አሸንፋ ከቀጣዩ ቀን ቆመች።

ዘቢደር ይህን ጨምሮ ሌሎች ክፉ ጊዚያትን በሚያስገርሙ አጋጣሚዎች አልፋለች። ነጭ በትሯን ይዛ ስትራመድ መኪና በጥሶ የጣለውን የኤሌክትሪክ ገመድ ከመርገጥ የዳነችበትን ቀን ዛሬም ድረስ አትዘነጋውም።

ዘቢደር ሁሌም የሚያግዟት ‹‹አይዞሽ›› የሚሏትን አታጣም። እንዲያም ሆኖ የብቸኝነት ሕይወት ይፈትናታል። በድንገት ቀኑ በጨለመባት ጊዜ ራሷን ከሁኔታዎች ማስማማት ይጠበቅባት ነበር።

ለእሷ ከድንገቴው የዓይነስውርነት ውጣ ውረድ ጋር መታገል ቀላል አልሆነም። ውላ አድራ ግን ችግር መከራውን ከራሷ አግባባችው። ለቅሶ፣ ትካዜን ትታ ውስጧን አበረታች፣ ጠነከረች። አንድ ሁለት ሲል መቁጠር የጀመረው ጊዜ እንደዋዛ ሰባት ዓመታትን ቆጠረ።

አንዳንዴ በሰዎች፣ ሌላ ግዜ በነጭ በትሯ እየተመራች አሁንም ራሷን ፈለገች። ብርቱዋ ዘቢደር ቀኗን በትካዜ ማሳለፍ ምርጫዋ አልሆነም። የሆነባትን ስታስብ ብታዝንም ውሎዋ በዚህ ስሜት እንዲታሰር አትሻም።

ልበ መልካሞች በሚያደርጉላት ድጋፍ እየታገዘች አስቸጋሪውን ኑሮ ቀጠለች። ውስጧ ተስፋ አላጣም። ከዓይነ ስውራን ትምህርትቤት ገብታ የብሬን ትምህርት ቀሰመች። ለእርምጃዋ እንዲበጅ የመንገድ አቅጣጫ ተሞክሮን ወሰደች።

### ሰባ ደረጃን ከውሾች ጋር ...

ዘቢደር የምትኖርበት የሰባ ደረጃ አካባቢ ለልማት ተፈልጓል። ነዋሪው ሰፈሩን ለመልቀቅ ጓዙን ከሸከፈ ሰንብቷል። እሷ ተከራይ ነች። ለእኔ የምትለው መጠጊያ የላትም። ቤቶች እየፈረሱ ሰዎች መውጣት ሲጀምሩ በእጅጉ ጨነቃት።

ቀስ በቀስ በዙሪያዋ የነበሩ ቤቶች ተነስተው ስፍራው ባዶ ሆነ። አከራዮቿ ቤታቸውን አፍርሰው ዕቃቸውን ይዘው ወጡ። ጣራው በተነሳ የግድግዳ ጥግ እሷና ውሾቿ ብቻ ቀሩ። ቀኑ አልፎ ምሽት ተተካ። ጨለማ የዋጠው አካባቢ በጭርታ ሲዋጥ ውስጧ ፍርሀት ነገሰ።

ሰፈሩን አቋርጦ የሚያልፍ ወንዝን ይዞ ብቅ የሚሉ ጅቦች ሁሌም ስጋት ናቸው። ይህን የሚያውቁ አንዳንዶች ዘቢደርን እያሰቡ የሚሆነውን ገመቱ። ዙሪያዋን ያሉት ታማኝ ውሾች ግን ‹‹አለንሽ›› ሲሉ ጠበቋት። ዘቢደር ከፈጣሪዋ በታች እነሱን አመነች። ብርድና ውርጩን ችላ የቀን ሌቱን ጨለማ አለፈች።

ዘቢደር በወንዝ ዳርቻ ሰው አልባ ሕይወት ከጀመረች ከአንድ ወር በላይ ሆኗል። ቀኑን እንደምንም አልፋ ምሽቱ ሲደርስ ይጨንቃታል። አሁንም ከፈጣሪ በታች ከሚጠብቋት ታማኝ ውሾች በቀር የደረሰላት የለም።

ዘቢደር አንድ ቀን በድንገት ታመመች። ውሾችና ወንዝ በከበባት ስፍራ ራሷን ማስታመም አልቻለችም። ይህኔ የዓይኖቿ መጥፋት ያጎደለባትን ሕይወት አስባ ከልብ አዘነች። ውሀ ቀድቶ የማይሰጣት ወገን ማጣቷ ልቧን ነካው።

ከቀናት በአንዱ ግን መልካም ዓይኖች ወደ እሷ ተመለከቱ። አንዲት ባልንጀራዋና የቀበሌው አመራሮች ደርሰው ከስፍራው አወጧት።

ዘቢደር ጓዝ ንብረቴን አላለችም። ሙሉ የቤት ዕቃዋንና ልብሷቿን እዛው ትታ ተከተለቻቸው። ሁኔታዋን ያየችው ሴት ልቧ ራራላት። ቀን እስኪያልፍ ብላ በቤቷ አስጠጋቻት። ዘቢደር ስጋትና ሕመም ሲፈራረቅባት የቆየው አካሏ ለጊዜው አረፍ አለ። እንዲያም ሆኖ ውስጧ ጤና የለውም። ሕመም እያዳከማት ነው። ሆስፒታል ገብታ ታክማ ተመለሰች።

ዘቢደር አሁን በጽኑ ታማለች። ሕይወቷን ለማዳን ሕክምና ያሻታል። ስለጤናዋ ግድ ያላቸው ስለእሷ ዝም አላሉም። በአስቸኳይ ከሆስፒታል አደረሷት። አሁን በቀላሉ ታክማ የምትወጣ አልሆነም። የስኳር ሕመሟ ለወራት አልጋ አስይዞ አስተኛት።

ዘቢደርን ያዩ የሕክምና ባለሙያዎች ከልባቸው አዘኑ። ድና ብትወጣ የምትሄድበት፣ እንደሌለ ባወቁ ጊዜ ሊረዷት ተባበሩ። አራት ወራትን ከሆስፒታሉ ግቢ ሳትወጣ ቆየች። ይህ በመሆኑ ዘቢደር አፏ ለምስጋና ተከፈተ። በዓይነስውር አቅሟ በወንዝ ዳር ያሳለፈችውን የብቸኝነትና የጨለማ ጊዜ አስባ ስለነገው ተስፋ ጣለች።

### የሰኔው በረከት...

ከቀናት በአንዱ ዘቢደርን ያሉ ሰዎች ቀርበው አወሯት። ንግግራቸው። ስለዓይኗ ደህንነት ነበር። ሰዎቹ ‹‹የወደቁትን አንሱ የነዳያን ማህበር›› ከተሰኘ ድርጅት የመጡ ናቸው። ዘቢደር ዓይኗን ሊያሳክሟት እንደሚፈልጉ ስትሰማ ሳታቅማማ ተስማማች። ድርጅቱ እንደእሷ ጊዜና ዕድሜ ዘንበል ያለባቸውን ወገኖች በመደገፍ ይታወቃል።

ከሆስፒታሉ ወጥታ ወደ ድርጅቱ ገባች። አሁን ሰኔ ግም ማለት ጀምሯል። ከጥቂት ጊዚያት በኋላ ዓይኗ እንደሚታከም ቃል ተገብቶላታል። ዘቢደር እነዚህን ቀናት እስኪደርሱ በጉጉት ጠበቀች። ተስፋዋ ለመለመ። አንድ ቀን የተያዘላት ጊዜ ቀጠሮው ደረሰ። ሕክምናውን ወደምታገኝበት ሀኪም ቤት ተጓዘች።

የሀኪሞቹ የመጀመሪያ ስራ የቀኝ ዓይኗን ቀዶ ሕክምና መስራት ነበር። እንደታሰበው ሆኖ በስኬት ተጠናቀቀ። ዓይኗ ለቀናት ታሽጎ መቆየት ነበረበት።

### ድንገቴው ብርሀን

እነሆ የታሸገው ዓይን ሊፈታ ቀኑ ደርሷል። ዘቢደር በቀጠሮው ዕለት ከሀኪም ዘንድ ቀርባለች። እሽጉን በጥንቃቄ መፈታት ተጀምሯል። እይታዋን ለማረጋገጥ ጥያቄ ቀረበላት። የሰጠችው ምላሽ አስደንጋጭም፣ አስደሳችም ነበር። በጨለማ ውሥጥ የኖረው ዓይኗ በትክክል ደማቁን ብርሀን ማየት ጀምሯል።

ዘቢደር ውስጧ ሲመላለስ የኖረው ግማሽ ተስፋ ዕውን ሆኗል። ሰባት ዓመታትን ከጨለማ የተዛመደ ማንነቷ አሁን በከፊል ከብርሀን ተዋዷል። ይህ ለእሷ ከሙሉ በላይ ነበር። እውነታውን የሰሙ ደስታዋን በእኩል ተጋሩ። የቀረቧትን እያየች በስም መጥራት ያዘች። አዲስ ዓለም፣ አዲስ ሕይወትን ተቀበለች።

ሁኔታው በዚህ ብቻ አልቆመም። ሁለተኛውን ዓይን ለመስራት ሌላ ቀጠሮ ተይዟል። ከአንድ ወር በኋላ ዘቢደር ሀኪም ፊት ቀረበች። ልክ እንደቀድሞው ኣይነት ሕክምና መካሄድ ጀመረ። ግራ ዓይኗ ዳግመኛ ሕክምናውን አገኘ። የዘቢደር ውጤት ተመሳሳይ ነበር። ሁለቱም ዓይኖቿ በብርሀን ከለላ ተገናኙ

### ያልጠለቀች ጀንበር ...

እነሆ! የሰባት ዓመታት የጨለማ ምዕራፍ በ‹‹ነበር›› ተዘጋ። ይህ ልብ ወለድ መሰል ታሪክ በዚህች ሴት ዕውን መሆኑ የበርካቶች እጅን በአፍ አስጭኗል።

ልበ ቀናዋ ዘቢደር ዛሬ ብድር ከፋይ ሆናለች። በምትገኝበት ድርጅት ደካሞችን ደጋፊ፣ የወደቁትን አቃፊ ነች። ትናንት ከብርሀን፣ ወደጨለማ፣ መልሶም ወደ ብርሀን ላመጣት ፈጣሪዋ ምስጋናዋ የላቀ ነው። ከእሷ ጎን ለነበሩ ወዳጆቿ ሁሉ የተለየ አክብሮት አላት።

አሁን የስኳር ሕመሟ ጥሩ ደረጃ ላይ መሆኑ ተረጋግጧል። ዘቢደር ድቅድቅ ጨለማዋ ተገፏል። ጀንበሯ አልጠለቀችም። ዛሬም በብርሀን መንገድ ልትመላለስ ውስጧ የበረታ፣ መንፈሷ የጠነከረ ነው።

# መሠረተ ልማት

# በኃይል ቁጠባ መታገዝ ያለበት የኤሌክትሪክ ልማትና ተደራሽነት ማስፋፋት ጥረት

**ኃይሉ ሣህለድንግል**

ኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ሃይል በስፋት ማመንጨት የሚያስችሏት ሰፊ የውሃ፣ የንፋስ፣ የጸሀይ እንዲሁም የጂኦተርማል ሀብት እንዳላት ይታወቃል። ሀገሪቱ እያደገ የመጣውን የኤሌክትሪክ ሃይል ፍላጎቷን ለማርካትም በእነዚህ በተለይ የውሃ፣ የንፋስና የጸሀይ ሃይል ሀብቶቿን በመጠቀም የኤሌክትሪክ ሃይል ለማምረት በሰፊው እየሠራች መሆኑ ይታወቃል።

ሀገሪቱ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የኤሌክትሪክ ሃይሏን በስፋት ስታመርት የቆየችው ከውሃ ሃይል ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ከንፋስና የጸሀይ ሃይል ሃል በስፋት ወደ ማመንጨት ገብታለች።

በእዚህ የኤሌክትሪክ ሃይል ልማት የሀገሪቱን የኤሌክትሪክ ሃይል ፍላጎት ለመመለስ እየቻለች ከመሆኑ በተጨማሪ ለጎረቤት ሀገሮች ጭምር የኤሌክትሪክ ሃይል በመላክ የውጭ ምንዛሬ እያገስገባች መሆኗም ይታወቃል። በቀጣይም ከሌሎች ሀገሮች የኤሌክትሪክ ሃይል ጥያቄ እየቀረበላትም ነው።

ሀገሪቱ ይህን ሁሉ ሥርታም በኤሌክትሪክ ሃይል ተደራሽ ማድረግ የቻለችው ከሕዝቧ 54 በመቶውን ብቻ ስለመሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ። አብዛኛው በገጠር የሚኖረው የሀገሪቱ ሕዝብ / ከገጠሩ ሕዝብ ከ90 በመቶው በላይ ይባላል/ የኤሌክትሪክ ሃይል ተደራሽ እንዳልተደረገም እንዲሁ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ሀገሪቱ ይህን ሁኔታ ለመቀየርም ትኩረት ሰጥታ እየሠራች ትገኛለች። ከዋናው የኤሌክትሪክ መስመር የገጠሩን ሕዝብ የኤሌክትሪክ ሃይል ተጠቃሚ ለማድረግ እያከናወነች ካለችው ተግባር በተጨማሪ ከዋናው ግሪድ በርቀት ላይ የሚገኘውን የገጠሩን ማህበረሰብ በሌሎች የኢነርጂ አማራጮች የኤሌክትሪክ ሃይል ተጠቃሚ ለሚያደርጉ ሃይል የማመንጨት ሥራዎችም ትኩረት ሰጥታለች።

ሌሎች መረጃዎች እንዳመለከቱት፤ በሀገር ደረጃ በወጣው የኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም 35 በመቶውን በኦፍ ግሪድ አማራጭ ለመድረስ ታቅዷል። 65 በመቶው ደግሞ ዋናው ግሪድ የሚደርስበት ይሆናል። ከዋናው ውጪ ያለው ሥራ በኦፍ ግሪድ የሚከናወን ይሆናል። በዚህም ዋናው የኤሌክትሪክ ግሪድ በማይደርስባቸው አካባቢዎች በሚኒ ግሪድና በመሳሰሉት ህብረተሰቡን ለመድረስ እየተሠራ ነው።

መቶ በመቶ የኤሌክትሪክ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ በሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉንም አማራጮች አሟጦ መጠቀም የግድ እንደሚሆን ታምኖበት እየተሠራ ነው። መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ አብዛኛውን የማህበረሰብ ክፍል የኤሌክትሪክ ሃይል ተጠቃሚ ለማድረግ የተለያዩ የኃይል ማመንጫ ፕሮግራሞች ተቀርፀው ተግባራዊ እየተደረጉ ናቸው።

ለእዚህም በሀገሪቱ የአጭርና የረጅም ጊዜ ብሔራዊ የኤሌክትሪክ ተረዳሽነት ፕሮግራም ተቀርፆ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ከውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ ያመለክታል። ከዚህ አኳያ በምዕተ-ዓመቱ የልማት ግብ በሀገር አቀፍ ደረጃ የመብራት ኃይል አቅርቦትን ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ፕሮግራም ወጥቶ እየተሠራ ይገኛል።

አሁን በተጀመረው አካሄድ 200 ያህል በሚሆኑ ከተሞች ላይ አነስተኛ ኃይል የሚያመነጩ ግሪዶችን ለማዳረስ እየተሠራ መሆኑን መረጃው ጠቁሞ፣ 100 በሚሆኑ ከተሞች ደግሞ ግንባታ እየተካሄደ መሆኑን አመልክቷል። ቀሪዎቹ በጨረታ ሂደት ላይ መሆናቸውን ጠቁሟል። ሌሎች መቶ ያህል ከተሞች ደግሞ ለእዚሁ እየተዘጋጁ መሆናቸው ተገልጿል።

በባዮጋዝ መሠረተ ልማት ግንባታና በመሳሰሉት ላይ በሀገርም በክልሎች እንዲሁም በተቋማትና በግለሰቦች አቅም እየተሠራ ስለመሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ። የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ከማልማት ጎን ለጎን ሃይል ቆጣቢ ምድጃዎችን ለማህበረሰቡ ለማድረስም ዘርፈ ብዙ ተግባሮች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

**በዚህ ሥራም እስከ አሁን ወደ 20 ነጥብ 5 ሚሊዮን የተሻሻሉ የምድጃ ቴክኖሎጂዎች ተሠራጭተዋል። ይህንን አሃዝ እስከ 2030 ድረስ ወደ 31 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ለማሳደግ ይሠራል። ዘንድሮ ወደ ሁለት ሚሊዮን የተሻሻሉና ንጹህ የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን ለማሰራጨት እየተሠራ ነው**

በኤሌክትሪክ ሃይል ልማትና ተደራሽነት ማስፋፋት ላይ የሚሠራው የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር ሥራ አስፈጻሚ አቶ ብርሃኑ ወልዱ ሰሞኑን በተለይ ለኢፕድ እንደተናገሩት፤ ሚኒስቴሩ በእዚህ ልማትና ተደራሽነት ላይ ከአጋር አካላት፣ ከማህበራትና ከዘርፉ ባለሙያዎች ጋር ይሠራል።

ሰሞኑንም ይህን የተመለከተ መድረክ ተካሂዷል። ከመድረኩ ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ የማገዶ ቆጣቢ እና የንጹህ ምድጃ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ ነው። ሚኒስቴሩ በ2019 የወጣውንና 6085 የሚባለውን አዲስ የላቦራቶሪ ፕሮቶኮልንም አስተዋውቆበታል። ፕሮቶኮሉ በ2014 እንደገና መሻሻሉን አቶ ብርሃኑ ጠቅሰው፣ ከዓለም አቀፉ የአይሶ ስታንዳርድ ጋር ተዛማጅ እንዲሆን ተደርጎ መሻሻሉን አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ የገጠሩ ማህበረሰብ ቴክኖሎጂ ሲጠቀም በማገዶ ጢስ ለጉዳት እየተዳረገ ያለበት ሁኔታ እንደ ዓለም ጤና ድርጅት ባሉት ዓለም አቀፍ ማህበረሰቦችም ጭምር የተወገዘ ነው። ይህን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፤ ጥቅም ላይ የሚውሉት ቴክኖሎጂዎች ግን በላቦራቶሪ መፈተሽ ይኖርባቸዋል፤ በጣም የተሻሻሉትን ለማውጣት የሚያስችል የላቦራቶሪ ፍተሻ ፕሮቶኮል ሊኖርም ይገባል።

በሀገሪቱ ንጹህ የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን ከማስፋፋት አኳያ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ግዙፍ የጸሀይ ሃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶችን በገጠሩ አካባቢ እያስገነባ ይገኛል ያሉት አቶ ብርሃኑ፣ ባለፈውም ወደ 14 የሚሆኑ ሚኒ ግሪዶችን/ የሶላር ሃይል ማመንጫዎችን/ በመገንባት ለገጠር ትላልቅ ወይም አነስተኛ ከተሞች ሃይል ማቅረብ መቻሉን ጠቅሰዋል።

የእዚህ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች ንጹህ የማብሰያ ምድጃ ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ ግፊት እየተደረገ መሆኑንም ተናግረው፣ ለእዚህም ለገጠሩ ማህበረሰብ ዘመናዊ ወይም ንጹህ ቴክኖሎጂዎችን ማቅረብ አለብን። የገጠሩ ማህበረሰብ የዚህ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆን ሚኒስቴሩ ጥረት እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በሀገሪቱ ከፍተኛ የሆነ የመረጃ አያያዝ ድክመት አለ። ይህን ሊያርም የሚችል ሥራ ተሠርቷል። ይህም የሶላር ተጠቃሚዎች እንዲሁም ሶላር ግሪዱ የት ይገኛሉ? የት አካባቢ የተቋም ሶላር አለ? የሚሉ ጥያቄዎችን የሚመልሱ መረጃዎችን በደንብ መያዝ እንዲያስችል የተዘጋጀው ዲጂታል መተግበሪያ ተሠርቷል፤ መተግበሪያው በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ዌብ ሳይት ላይ ይጫናል። ማንኛውም አካል መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘት ይቻላል። በመድረኩ የቀረቡት ዋና ዋና ሃሳቦችም ይህን ይመስላሉ።

አቶ ብርሃኑ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ግሪዶችን በከፍተኛ ሁኔታ ለማስፋፋት እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፣ በዋናው ግሪድም/ የኤሌክትሪክ ሃይል ማስተላለፊያ/ የገጠሩን ማህበረሰብ ፍትሃዊ የኢነርጂ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ሀገሪቱ ከዋናው የውሃ ሃይል በተጨማሪ ብዙ የኢነርጂ ምንጮች አሏት። ከእነዚህ መካከል አንዱ ባዮ ማስ ነው። አብዛኛው የሀገሪቱ ሕዝብ የሚኖረው በገጠር እንደመሆኑ የኢነርጂ ምንጩ በአብዛኛው ማገዶ ነው። ይህን ማገዶ ግን በጣም በሠለጠነና ኢነርጂ ቆጣቢ በሆነ መንገድ፣ ጤናን እና አካባቢን በማይጎዳ መልኩ እንዲጠቀም ለማድረግ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጥረት እያደረገ ይገኛል።

እነዚህን ቴክኖሎጂዎች ለገጠሩ ሕዝብ ለማድረስ የተለያዩ ተግባሮች እየተከናወኑ ይገኛሉ። ከእነዚህ መካከል ሀገር በቀል ቴክኖሎጂዎችን ማውጣት፣ ቴክኖሎጂዎችን ከውጭ አምጥቶ ማላመድ ላይ በስፋት በመሥራት የገጠሩን ሕዝብ ኢነርጂ የመጠቀም ፍላጎት ለማርካት በስፋት እየተሠራ ነው።

በዚህ ሥራም እስከ አሁን ወደ 20 ነጥብ 5 ሚሊየን የተሻሻሉ የምድጃ ቴክኖሎጂዎች ተሠራጭተዋል ያሉት አቶ ብርሃኑ፣ ይህንን አሃዝ እስከ 2030 ድረስ ወደ 31 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ለማሳደግ ይሠራል ሲሉ ጠቁመዋል። ዘንድሮ ወደ ሁለት ሚሊዮን የተሻሻሉና ንጹህ የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን ለማሰራጨት እየተሠራ ነው ይላሉ።

ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በኩል በአብዛኛው የኤሌክትሪክ ምድጃዎችን ስናይ ሃይል ቆጣቢ ናቸው ተብሎ አይታሰብም ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፣ በሀገሪቱ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ሃይል ብክነት እንደሚታይ ጠቁመዋል። ይህ ችግር አሁን እየጨመረ ከመጣው የኤሌክትሪክ ሃይል ዋጋ ጋር ተያይዞ በህብረተሰቡ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያሳርፍ ገልጸው፣ ሃይል ሊቆጥቡ የሚችሉ የምድጃ ቴክኖሎጂዎች እንደሚያስፈልጉ አጽንኦት ሰጥተው አስገንዝበዋል።

እንደ አቶ ብርሃኑ ማብራሪያ፤ የሃይል ብክነቱ ለቤተሰብ ብቻም ሳይሆን ለሀገርም ትልቅ ሸክም ነው። ብዙ ፋብሪካዎች ሊጠቀሙበት የሚገባ ኢነርጂ ቤት ውስጥ እየባከነ ነው። ይህን ችግር ለመፍታት እነዚህን ቴክኖሎጂዎች በሀገሪቱ ማስፋፋት የግድ ይሆናል።

ኢነርጂ ማመንጨቱ ብቻውን ዋጋ የለውም፤ በቁጠባ መጠቀምም ያስፈልጋል ሲሉም አስገንዝበው፣ ይህን ብክነት ለመቀነስ የቤተሰብን የንጹህ ምድጃ አጠቃቀም እንዲሁም የቴክኖሎጂዎችን ብቃት ማሻሻል ወሳኝ ይሆናል ብለዋል።

ከዚህ አኳያ ሚኒስቴሩ ከኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ጋር በመሆን አዳዲስ ሃይል ቆጣቢ ምድጃዎችን በማስፈተሽና የተለጣፊ ምልክት በመስጠት እነዚያ ቴክኖሎጂዎች ብቻ ገበያ ውስጥ ገብተው እንዲሠራባቸው ለማድረግ እየተሠራ ነው። ለእዚህም የማህበረሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግም ጥረት እያደረገ ይገኛል።

የሚኒስቴሩ አንዱ ሥራ ቴክኖሎጂዎችን ከውጭ በማምጣት፣ የመጡትን ቴክኖሎጂዎች በማላመድ እንዲሁም በሀገር ውስጥ በመሥራት ማህበረሰቡን የዘመናዊ ኢነርጂ ተጠቃሚ ማድረግ መሆኑን አስታውቀዋል።

አቶ ብርሃኑ ከዚሁ ጎን ለጎንም በአሁኑ ወቅት አነስተኛ ወንዞችን ጭምር ለሃይል ልማት ለማዋል እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል። በተለይ ከዋናው ግሪድ የራቁ አካባቢዎችን የኢነርጂ ተጠቃሚ ለማድረግ ይህ አንዱ አማራጭ ተደርጎ እየተሠራበት ስለመሆኑም አመልክተው፣ በዚህም የተለያዩ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ እየተደረጉ ናቸው ይላሉ።

ባለፈው ዓመት በዚህ ላይ ወደ ሶስት ፕሮጀክቶች ሲካሄዱ እንደነበር ጠቅሰው፣ ከእነዚህ የአንዱ ግንባታና የኤሌክትሮ መካኒካል ሥራ መጠናቀቁን አስታውቀዋል። በዚህም ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገ ስለመሆኑ አቶ ብርሃኑ ተናግረው፣ ሁለቱ ፕሮጀክቶች ደግሞ በተለያየ የግንባታ ደረጃ ላይ መሆናቸውን አመልክተዋል።

እሳቸው እንዳሉትም፤ ሀገሪቱ ብዙ የውሃ ሀብት አላት፤ አስራ ሁለት ተፋሰሶች አሏት። በእነዚህ ውስጥ ያሉት አነስተኛ ወንዞች ሃይል ሊያመነጩ የሚችሉ ናቸው። የሀገሪቱ የመሬት አቀማመጥ ከወንዞቹ ሃይል ለማመንጨት የተመቸ ነው። በዚህ መሠረት በተለይ ከዋናው የኤሌክትሪክ መስመር ርቀው የሚገኙ አካባቢዎችን የሃይል ተጠቃሚ ለማድረግ እነዚህን ወንዞች ለሃይል ምንጭነት ለመጠቀም እየተሠራ ይገኛል። ይህ ሥራ ወደፊትም ተጠናክሮ ይቀጥላል፤ እስከ 2030 ድረስ የአነስተኛ ወንዞች ኢነርጂ ልማት ግንባታን በማከናወን በርካታ ዜጎችን የኤሌክትሪክ ሃይል ተጠቃሚ እናደርጋለን ሲሉም ጠቁመዋል።

ሀገሪቱ ለመስኖ ልማት ትኩረት ሰጥታ እየሠራች መሆኑ ይታወቃል። የመስኖ ልማቱ ከሚካሄድባቸው መንገዶች አንዱ በነዳጅ የሚሠሩ የውሃ መሳቢያ ሞተሮች /ዲዝል ፓምፓች/ በመጠቀም ነው። ለእዚህም ምናልባት በሀገሪቱ ከ500 ሺህ በላይ ሊሆኑ የሚችሉ ዲዚል ፓምፖች ለመስኖ ልማት ሥራ እያገለገሉ ናቸው።

እነዚህን በነዳጅ የሚሰሩ የውሃ መሳቢያ ሞተሮችን በሶላር በሚሠሩ የውሃ መሳቢያዎች ለመተካት አቅጣጫ ተቀምጦ እየተሠራ ይገኛል። እሳቸው እንዳሉትም በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ከእነዚህ ፓምፖች 50 በመቶውን በሶላር ቴክኖሎጂዎች ለመቀየር እየተሠራ ነው።

እሳቸው እንዳመለከቱት፤ ይህ እውን ሲሆን አርሶ አደሮች ነዳጅና ዘይት ፍለጋ አይንከራተቱም፤ ሶላር ቴክኖሎጂ በመጠቀም ከመሬት ውስጥም ይሁን ከመሬት ላይ ያለውን ውሃ በመጠቀም የመስኖ ልማት ሥራቸውን የሚያካሂዱበትን ሁኔታ ለመፍጠር እየተሠራ ይገኛል።

ይህ ብቻም አይደለም ለግብርና ምርቶች ማቆያ ማቀዝቀዣዎች እንደሚያስፈልጉ ይታወቃል። ለእዚህም የድህረ እና ቅድመ ምርት ሶላር ቴክኖሎጂዎች የሚጠቀሙ ማቀዝቀዣዎች /ኩለር/ አርሶ አደሩ እንዲጠቀም ለማድረግ የተለያዩ የሙከራ ሥራዎች እየተሰሩ መሆናቸውንም አቶ ብርሃኑ ጠቁመዋል።

# ስፖርት

## በበርሊን ማራቶን ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ለድል ይጠበቃሉ

ብርሃን ፈይሳ

ከዓለም ቁጥር አንድ የማራቶን ውድድሮች የሚመደበውና በርቀቱ በርካታ የዓለም ክብረወሰኖች የተሰበሩበት የበርሊን ማራቶን ነገ ይካሄዳል። የዓለም አትሌቲክስ የፕላቲንየም ደረጃ ከሰጣቸው ጥቂት የማራቶን ውድድሮች መካከል አንዱ የሆነው ይህ የበርሊን ማራቶን 50ኛ ዓመቱን የሚደፍን ቢሆንም፤ ከዚህ ቀደም ድምቀት የሆኑት ከዋክብት አትሌቶች አይሳተፉም።

ላለፉት 11 ዓመታት በርሊን ማራቶንን ገናና ያደረጉትና ረጅም ዓመታትን እርስ በእርስ በመፎካከር የሚታወቁት ኢትዮጵያዊው ጀግና አትሌት ቀነኒሳ በቀለ እና ኬንያዊው ኢሉድ ኪፕቾጌ ነበሩ። ይሁንና ሁለቱ አንጋፋ የማራቶን ከዋክብት ከፓሪስ ኦሊምፒክ መልስ በሚደረገው በዚህ ውድድር ላይ አይገኙም። ባለፈው ዓመት በሴቶች የዓለም ክብረወሰንን ከእጇ ልታስገባ የቻለችውና የፓሪስ ኦሊምፒክ በርቀቱ የብር ሜዳሊያ ያጠለቀችው ትዕግስት አሰፋም በተመሳሳይ በበርሊን ማራቶን የተሳታፊዎች ዝርዝር ውስጥ የለችም። ነገር ግን በርቀቱ ፈጣን ሰዓት ያላቸው ወጣት አትሌቶች የ50ኛው ዓመት የበርሊን ማራቶን ድምቀት ለመሆን ተዘጋጅተዋል።

የኢትዮጵያ እና ኬንያ አትሌቶች በወንዶች እአአ ከ1999 አንስቶ በሴቶች ደግሞ ከ2009 አንስቶ አንድም የሌላ ሀገር አትሌት ሳይቀላቅሉ እርስ በእርስ በመተካካት የበላይነቱን ይዘዋል። በዚህ ውድድር የሚካፈሉት አትሌቶች አብዛኛዎቹ ወጣት ቢሆኑም እንደተለመደው አዲስ ነገር ያሳያሉ ተብለው ይጠበቃሉ። ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች ታደሰ ታከለ እና ትዕግስት ከተማ ደግሞ ባላቸው ፈጣን ሰዓት በውድድሩ ከሚካፈሉ ታዋቂ አትሌቶች መካከል በቀዳሚነት ሊቀመጡ ችለዋል።




በዘንድሮው የበርሊን ማራቶን 50 ሺህ ተሳታፊዎች ይጠበቃሉ፣

ባለፈው ዓመት በዚሁ የበርሊን ማራቶን ሶስተኛ ደረጃን በመያዝ ማጠናቀቅ የቻለው አትሌት ታደሰ ታከለ በድጋሚ የጀርመኗ ከተማ ላይ ከትሟል። በ3ሺ ሜትር መሰናክል ሩጫዎች የሚታወቀውና ሀገሩንም በዓለም ከ20 ዓመት በታች እንዲሁም በአፍሪካ ቻምፒዮና በመወከል የብር ሜዳሊያ ማስመዝገብ የቻለው አትሌቱ በማራቶን የሁለተኛ ጊዜ ተሳትፎውን በበርሊን ያካሂዳል። የ22 ዓመቱ ወጣት ማራቶንን መሮጡ ጥያቄን ቢያጭርም ይበልጥ አስገራሚው ጉዳይ ግን በመጀመሪያ ተሳትፎው ስኬታማ መሆኑ ነው። በማራቶን የዓለም ፈጣኑን አትሌት ኪፕቾጌን ተከትሎ የገባበት 2:03:24 የሆነ ሰዓትም ፈጣን እና ከልምዱ አንጻር የማይጠበቅም ነበር። ይሁንና አትሌቱ ካለው ብቃት አንጻር በዚህ ውድድር አሸናፊ ሊሆን አሊያም ጠንካራ ተፎካካሪ እንደሚሆን እየተጠበቀ ነው።

በውድድሩ ከሚሳተፉ ታዋቂ አትሌቶች መካከል ፈጣን የሆነ ሰዓት ያላቸው አምስት ሲሆኑ በርቀቱ ያላቸው ፈጣን ሰዓትም ከ2 ሰዓት ከ05 ደቂቃ በታች ነው። ተጠባቂ ከሆኑት መካከል አንዱ ኬንዊው ኪብዎት ካንዳይ በተመሳሳይ የዘንድሮ የማራቶን ተሳትፎው ለሁለተኛ ጊዜ ነው። በግማሽ ማራቶን ውጤታማነቱ የሚታወቀው አትሌቱ ከዚህ ቀደም የርቀቱን ክብረወሰን መጨበጥ ችሎ ነበር። በቫሌንሺያ ግማሽ ማራቶንም ለተከታታይ ሶስት ዓመታት አሸናፊ መሆን ችሏል። በመሆኑም ይህ ውድድር በርቀቱ አዳዲስ በሆኑ አትሌቶች መካከል የሚደረግ መሆኑ ፉክክሩንም እጅግ አጓጊ አድርጎታል። ደማቁ የበርሊን ማራቶንም ከረጅም ዓመታት በኋላ አዳዲስ አሸናፊ አትሌቶችን ያገኛል በሚልም ይጠበቃል።

የሴቶቹ ምድብም በኢትዮጵያውያን አትሌቶች የሚመራ ሲሆን፤ ትዕግስት ከተማ እና ገንዘቤ ዲባባ ደግሞ አሸናፊ ይሆናሉ የሚል ቅድመ ግምት ያገኙ አትሌቶች ናቸው። የዘንድሮው የዱባይ ማራቶን አሸናፊዋ ትዕግስት የማራቶን ተሳትፎዋ ለመጀመሪያ ጊዜ ቢሆንም 2:16:07 በመሮጥ የቦታውን ፈጣን ሰዓት አስመዝግባለች። ከወራት በኋላ በተሳተፈችበት የለንደን ማራቶን ግን ሰባተኛ ደረጃን በመያዝ ነበር ያጠናቀቀችው። ሆኖም አትሌቷ ካላት ፈጣን ሰዓት አንጻር ለአሸናፊነት ከሚጠበቁት 10 የበርሊን ማራቶን የዘንድሮ ተሳታፊዎች መካከል ቀዳሚነቱን ልትይዝ ችላለች።

በሌላ በኩል በመካከለኛ ርቀት የመም ሩጫዎች ስኬታማዋ አትሌት ገንዘቤ ዲባባ ወደ ጎዳና ላይ ሩጫዎች ፊቷን ከመለሰች ወዲህ ብቃቷን የምታሳይበት መድረክ እንደሚሆን ይጠበቃል። በሪዮ ኦሊምፒክ የ1ሺ 500 ሜትር የብር ሜዳሊያ ባለቤቷ አትሌት ባለፈው ዓመት የቺካጎ ማራቶንን የሮጠችበት 2:21:47 የሆነ ሰዓት የግሏ ፈጣን በመሆን ተመዝግቦላታል። በኢትዮጵያ በኩል በርካታ አትሌቶች የሚካፈሉ ሲሆን፤ የብርጓል መለሰ፣ መስታወት ፍቅር፣ አዝመራ ገብሩ፣ ሲሳይ መሠረት፣ አባበል የሻነህ እንዲሁም ፍቅርተ ወረታ የአሸናፊነት ብርቱ ፉክክር እንደሚያደርጉም ይጠበቃል።